# የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞ፣ ተግዳሮቶቹና የመፍትሄ ሃሳብ

**ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ለመገንባት ምቹ የሆነ የሶሺዩ ፖለቲካ ሥርዓት ወደ መፍጠር**

ለአራተኛው የቪዥን ኢትዮጵያ ኮንፈረንስ የቀረበ ጽሁፍ

ገለታው ዘለቀ

መስከረም 2017

ዋሽንግተን DC.

የተባበረችው አሜሪካ

# ቢጋር

I. ረቂቅ

II. የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞ

III. የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ተግዳሮቶች

3.1. ማኅበራዊ ተግዳሮቶች

3.1.1. የሶሺዮ ፖለቲካችንን መሸርሸሩ

3.1.2. የግትርነትና ጽንፈኝነት ባህርያት መዳበሩ

3.2. ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች

3.2.1. ብዙሃን ይግዛ

3.2.2. ለማንነት ድምጽ በኀይል መጋለጥ

3.2.3. የማንነት ግጭት

3.2.4. የቡድንና የግለሰብ መብት እንዲጋጩ ማድረጉ

3.2.5. የፖለቲካ ሥልጣን ቀመር ችግር

3.2.6. የጋራ መሪ እንዳናፈራ ማድረግ

3.2.7. ሁለት አይነት አርበኞች መፍጠሩ

3.3. ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

3.3.1. የሀብት ክምችት ተስፋ መሆኑ ቀርቶ የግጭት መንስዔ ይሆናል

3.3.2. በብሔራዊ ሀብትና በብሔር ሀብት መሃል ግልጽነት አይኖርም

3.3.3. ያልተመጣጠነ እድገት ያመጣል

3.3.4. ሙስናን ያዳብራል

3.3.5. ለኮሚዩኒቲ ሞቢላይዜሽን የሚሆን ኀይል ያሳጣል

IV. ምን ይሻላል? የመውጫ ሃሳብ (EXIT)

4.1. የዓለም ማኅበራዊ ፖለቲካ ንድፈ ሃሳቦችና ሞዴሎች ቅኝት

4.1.1. ሜልቲንግ ፓት

4.1.2. ካልቸራል ሞዛይክ

4.1.3. ብዝሃነት

4.1.4. ሕገ-መንግሥታዊ አርበኝነት

## V. የመፍትሄ ሃሳብ

### 5.1. በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነት ፍሬም ወርክ

#### 5.1.1. የንድፈ ሃሳብ ይዘቶች

##### 5.1.1.1. አዲስ ኪዳን

##### 5.1.1.2. ሄራ

##### 5.1.1.3. የአገር አስተዳደር ቅርጽ

##### 5.1.1.4. የቋንቋ ማኔጅመንትና አጠቃቀም

#### 5.1.2. የአዲሱ ቃል ኪዳን ዋስትናዎችና ተግዳሮቶች

## VI. መደምደሚያ

# 1. ረቂቅ

የሰው ልጅ ማኅበራዊና ግላዊ ተፈጥሮ ስላለው ለማኅበራዊ ኑሮውና ለግላዊ ኑሮው የተለያዩ ጠገጎችን እያበጀ ይኖራል። እነዚህ የሚሰራቸው ጠገጎች ለግል ሕይወቱም ሆነ ለማኅበራዊ ሕይወቱ ወሳኝ ናቸው። ሰው የዚህን ዓለም ኑሮውን ለመግፋት ከሚያስችሉት መሳሪያዎች አንዱ እነዚህ ጠገጎቹ ናቸው። የሰው ልጅ በሕይወቱ የሚፈጥራቸው እነዚህ ጠገጎች ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ወይም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትርፍ ያስገኙለታል። ታዲያ ይህ የሰው ልጅ በዓለም ላይ ከሚፈጥራቸው ጠገጎች መሃል ከፍተኛውና ጠንካራው አገር የሚባለው ጠገጉ ነው። በርግጥ ከዚህ አልፎ ዛሬ ጊዜ ሌላ ከፍ ያለ የጋራ የዓለም ጠገግ ሕዝቦች አበጅተው ስያሜውን ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ብለውታል። ነገር ግን የሰው ልጅ ከቀን ተቀን ሕይወቱ ጋር በጣም የተሳሰረው ጠገግ አገር ሲሆን ለዚህ ጠገግ የተለያዩ ስምምነቶችን አስፍሮ በዚህ ጥግ ስር ይኖራል። አገር የሚባለው ጠገግ ጠባብ አይደለም። የሰው ልጅ በዚህ ጠገግ ስር ብዙ መለስተኛ ጠገጎችን ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ የባህል የሃይማኖት ወይም ሌላ ዓላማ ያለውን ጠገግ በዚህ ሰፊ ጠገግ ውስጥ ሊሰራ ይችላል። አገር የሚባለው ጠገግ እነዚህን ሁሉ አቅፎ መያዝ የሚችል ሰፊ አዳራሽና ከፍ ያለ ጠገግ ነው። እንደ ብሔር የሃይማኖት ስብስብ ያሉ ጠገጎች በተፈጥሯቸው ልዩነትን በውስጣቸው አይዙም። ልዩ ልዩ ቡድኖችን አቅፎ በውስጣቸው ለማስኖር የሚያስችል ተፈጥሮ የላቸውም። ከነዚህ ስብስቦች ከቡድናቸው ስምምነት ወይም ደንብ ውጭ የሆነ ቡድን ቢመጣ በውስጣቸው ያለ ቅራኔ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ነው አገር የሚባለው መዋቅር ከነዚህ የቡድን ጥጋጥጎች ተላቆ ሁሉን ማቀፍ የሚችል ጠገግ ሆኖ በዘመናዊቷ ዓለም የተሰራው።


ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ኢትዮጵያም በውስጧ ብዙ ቡድኖችን የያዘች ሰፊ ጠገጋችን ናት። ይሁን እንጂ በተለይ ባለፉት ሃምሳ አመታት ግድም በውስጧ ያሉትን ሌሎች ጠገጎች በተለይም ብሔርን ለማስተናገድ ይመረጣል ተብሎ የአገራችንን የፖለቲካ ሲስተም የተቆጣጠረውን የብሔር ፖለቲካ እያካሄድን ነው። በዓንድ አገር በተለይም ብዙህ በሆኑ ሕዝቦች ውስጥ በተለይ የፖለቲካው ለሂቅ የሚከተለው የሶሺዮ ፖለቲካ ፍልስፍና የዚያን አገር የፖለቲካ ውቅር በቀጥታ ተጽእኖ ይፈጥርበታል። አገር መስርተን እየኖርን ያለን ብዙ ብሔሮች ስለዚህ ስብስብ ያለን ፍልስፍናና ይህን ስብስብ ልናስተናግድበት የምንፈልገው መንገድ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወት ሁሉ ይለውጣል። ዛሬ በዚህ ጽሁፍ ስር በጥልቀት የምናየው ጉዳይም ይሄው የኢትዮጵያ የሶሺዮ ፖለቲካ ፍልስፍናና ያመጣውን ተጽእኖ እንዲሁም ይህንን ተከትሎ ከመጣው ችግር የመውጫውን መንገድ ነው። በአንድ አገር ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባትም ይሁን ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ለመገንባት የሶሺዮ ፖለቲካ አመለካከታችን ወሳኝ ነው። የዚህ ጽሁፍ ዓላማም ለዴሞክራሲ ሥርዓት የሚሆን ምቹ እርሻን ለመፍጠር የተሻለ የሶሺዮ ፖለቲካ አስተሳሰባና ሲስተም ለማሳየት ነው። ይህ ሲስተም በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነት የተሰኘ ፍሬም ወርክ ሲሆን በውስጡ የአዲስ ቃል ኪዳን ጥሪ፣ የሕገ-መንግሥት ለውጥ፣ የመንግሥት አወቃቀርና የቋንቋ ማኔጅመንትና አጠቃቀምን የሚመለከት ይሆናል። ፍሬም ወርኩ በነዚህ አራት ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ሃሳብና ሲስተም የተባበረች ኢትዮጵያን እንደገና ለማነጽ አማራጭ ሲስተም ይሆናል።

## II. የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞ

የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ፍልስፍና በጋራ በምንፈጥረው ጠገግ ውስጥ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ሕይወታችንን ተጽእኖ ይፈጥርበታል በሚለው ከተስማማን የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞ አጥንቶና መርምሮ የተሻለ አመለካከትና ሲስተምን ማምጣት የግድ ይለናል። በዚሁ መሰረት በዚህ ክፍል ውስጥ የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞ በጥቂቱ እናያለን።

ዘመናዊት ኢትዮጵያ ዘመናዊ አስተዳደር ማካሄድ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያ በተወሰነ የባህል ምስለት ውስጥ አልፋለች። የዘመናዊት ኢትዮጵያ መሃንዲሶች የሚባሉት አጼ ቴዎድሮስ አጼ ዮሃንስና አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን ዘመናዊ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የባህል ምስለት በተለያየ ደረጃ ተካሂዷል። በርግጥ በኢትዮጵያ ምድር ይህ የባህል ምስለት የተካሄደው በአማራና በሌሎች ብሔሮች መካከል ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ በኦሮሞ ብሔር መስፋፋት ጊዜም የባህል ምስለቶች ተካሂደዋል። ደቡብ አካባቢ ያሉትን እንደ ጌዲኦ ቡርጂ ኮንሶ የመሳሰሉትን ሕዝቦች ብናይ የኦሮሞ ባህልና ቋንቋ ተጽእኖዎችን እናያለን። የጌዲኦ ሕዝብ የገዳ ሥርዓትን የሚከተል ሕዝብ ነው። ኮንሶ የኦሮሞን ሃይማኖት የሚከተል ነው። በርግጥ ስለ ምስለት ስናወራ ቡድን የሚባለው በተለይም ብሔር በአንድ ቀን እንደ አዳምና ሄዋን ተፈጥሮ ምድር ላይ የተገኘ አይደለም። ብሔር የሚፈጠረው በመስፋፋት ምናልባትም በምስለት ነው። ስለሆነም ምስለቱን ጠለቅ ብለን እንይ ካልን ዛሬ ምስለት ተካሂዶብናል የምንል ብሔሮች እኛም ራሳችን በምስለት ውስጥ አልፈን ይሆናል እዚህ የደረስነው። የሆነ ሆኖ ግን አዲሲቷ ኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥትን ስታጠናክር በዚይን ወቅት የነበሩ ቡድኖችን ስታሰባስብ የሰሜኑ ባህል በተለይም በከተሞች አካባቢ ተጽእኖ ፈጥሮ ቆይቷል። ዓለምም ለነገሩ በአብዛኛው የተፈጠረችው እንደዚህ ነው። የሆነ ሆኖ ኢትዮጵያ ምስለት ባየለበት መንግሥት ስር ለብዙ ዓመታት ኖረች። በዚያን ጊዜ የነበረው የሶሺዮ ፖለቲካ አስተሳሰብ አንድን ሃይማኖትና ባህል በመጫን ላይ ያተኮረ ነበር ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታ ብዙ ዓመት ከቆየ በሁዋላ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የዓለምን የሶሺዮ ፖለቲካ አስተሳሰብና አተያይ የሚቀይር አንድ ፍልስፍና ብቅ አለ። የማርክሲስት ሌኒኒስት አስተምህሮ የዓለምን ወጣቶች ልብ ለተወሰነ ጊዜ ገዝቶ ነበር። ይህ አስተሳሰብ ከያዛቸው ትምህርቶች መካከል የብሔሮች ነጻነት፣ ራስን በራስ ማስተዳደርና የራስን እድል በራስ እስከመወሰን ድረስ መሄድ የፍትህ ጥግ መስሎ ታየ። ያለፈውን ሥርዓት ማንነትን የደፈጠጠ በመሆኑ በቀል ተያዘበት። በመሆኑም የብሔሮች ጥያቄ በዘመናዊት ዓለም የፖለቲካ መለዮ ለብሶ እሳት ጎርሶ መጣ። ቀላል የማይባሉ የኢትዮጵያ ተማሪዎችም በአስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹ በዚህ ትምህርት ከነፉ። የብሔሮች ጥያቄ መነሳቱ ሳይሆን የከፋው ብሔር የሚባለውን ስብስብ ወይም ጠገግ እንደ ሰው ልጆች ጠገግ የመጨረሻ ቅንጣት ወይም የማምለጫ አለት ተደርጎ መወሰዱ ነበር። በዚህ ጠገግ ስር ፍትህ የማይጎድልበት ይመስል፣ በዚህ ጠገግ ስር የማይርበው ይመስል፣ የማይጠማው ይመስል፣ ክፉ የማያገኘው ይመስል፣ ብሔር የሰው ልጆች የመጨረሻ ዞሮ መግቢያ፣ ተገንጥሎ ማረፊያ ጎጆ ተደርጎ በሶሺዮ ፖለቲካ ፈላስፎች ታየ። ኢትዮጵያም ይህንን ትምህርት መከተል ስትጀምር በሳህን በሳህን ለየብቻችን ፖለቲካንና ኢኮኖሚን እንድንጫወት ተደረገ። ኢትዮጵያ በምስለት ውስጥ አልፋልች ብሎ ቂም ይዞ የተነሳው አዲሱ የማኅበረ ፖለቲካ አስተሳሰብ ሥልጣን ሲይዝ ብሔሮች ያገግሙ ዘንድና ጠገጋቸውን ይጠግኑ ዘንድ የፖለቲካ ማልያ እንዲለብሱ የሚያደርግ ፍልስፍና ነው። ነገር ግን ይህ የሶሺዮ ፖለቲካ አስተሳሰብ የገጠመው ችግር አንደኛ ኢትዮጵያ ለብዙ ጊዜ በምስለት ውስጥ በማለፏ ወደ ሁዋላ ተመልሳ በየቤታችን እንደር የማትልበት ደረጃ ላይ መድረሷ ነው። ትልቁ ግጭት ይሄ ነው። እነዚህ ቡድኖች ለምእተ ዓመት አብረው ሲኖሩ እየተጋቡ የፈጠሩት ቅይጥ ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ብሔሮች በብዛት ወደ ሶስተኛ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የሚሆን ነው። ይህ አካል አገሪቱን የማትከፋፈል የማድረግ ኀይል በውስጡ ይዟል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለረጅም ዘመን አብረው ከመኖራቸውና ብሔሮች ራሳቸው ሲስፋፉ ሲንቃነቁ በመኖራቸው የውስጥ ድንበር አፍርሰዋል። በዓሁኑ ሰዓት ይህ መንግሥት ዘጠኝ ክልል ያደረጋት ኢትዮጵያ ስትፈጠር ዘጠኝ አይደለችም። ቡድኖች መሬታቸው ወሰኑ እስኪጣፋቸው አገር ሲመሰርቱም ሲስፋፉም ቆይተዋል። ሌላው ሶስተኛው ችግር ደግሞ እነዚህ ቡድኖች በጋራ ዘመናቸው የሰሩት ብዙ ታሪክ አላቸው። ይህም አዲሱን ሶሺዮ ፖለቲካ የሚቃረን ኀይል ነው። በሌላ በኩል የዓለምን አፈጣጠር ስናይ ዛሬ ከሞላ ጎደል የተረጋጋችው ዓለም ስትፈጠር በዚሁ በምስለት ጎዳና መሆኑ ነው። ኢትዮጵያ ለብቻዋ የመጣባት ችግር ባለመሆኑና ከሰው ልጆች ንቃተ ህሊና እድገት ጋር አብሮ መታየት ስላለበት ኢትዮጵያን እንደገና ወደ ሁዋላ መልሶ የተከፋፈለች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለማድረግ የዓለም ሶሺዮ ፖለቲካም በተቃርኖ የቆመ ኀይል ነው። በጋራ ያፈራነው ሀብትና

እሴቶቻችንም ይህን አዲስ የሶሺዮ ፖለቲካ የሚቃረኑ ወይም በተቃራኒ የሚስቡ ኀይሎች ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህን ኀይሎች ሁሉ እንደ ጠባብ ወይም እንደ ትምክህት እያየ አዲሱ የሶሺዮ ፖለቲካ ሃሳብ ስራውን ቀጠለ። በመሆኑም አገሪቱ የብሔር ፌደራሊዝምን በመመስረት የሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞዋን ከምስለት ወደ ልዩነት ወሰደው። ጉዟችን ከምስለት ወደ ልዩነት ነው ማለት ነው።



## ለመሆኑ ከምስለትና ከልዩነት የቱ ይከፋል?

በመሰረቱ በዘመናዊ የሶሺዮ ፖለቲካ አስተሳሰብ ስንመለከተው ሁለቱም ተገቢ አይደሉም። ምስለትም ልዩነትም አደጋዎችን ይዘዋል። ይሁን እንጂ ከሁለት ጥሩ ካልሆኑ ነገሮች አንዱን ምረጡ ብንባል ግን የትኛው ይሻላል? ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው። ይህ ጥያቄ የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞው ከምስለት ወደ ልዩነት መምጣቱ ያመጣውን ችግርና ያዘለውን አደጋ የበለጠ በምናብ ስለሚያሳይ ነው።

ምስለት ማለት በግድ እኔን ምሰል ማለት ነው። በቅኝ ግዛት ጊዜ ፈረንሳዩች እንግሊዞች ይህን ተጠቅመውበታል። እኔን ምሰል ማለት እኔ የምናገረውን ቋንቋ ቋንቋህ አድርግ፣ እኔ እንደምጨፍረው ጨፍር፣ እኔ የምበላውን አይነት ብላ፣ እኔ እንደማስበው አስብ ወዘተ ነው። በብዙ ቅኝ ግዛት አገሮችም ይህ ሆኗል። በሌላ በኩል ልዩነትን ስናይ ደግሞ እኔ የምለብሰውን ዓይነት አትልበስ፣ እኔ በምሄድበት አትሂድ፣ የእኔን አጨፋፈር አትጨፍር ወዘተ ነው። ይህ ልዩነትን መሰረት ያደረገ አገዛዝ ሲነሳ ደቡብ አፍሪካ ትጠቀሳለች። እንግዲህ ታዲያ ከምስለትና ከልዩነት የቱ ይሻላል የቱ ይከፋል? ካልን ምስለት ይሻላል፣ ልዩነት ይከፋል ማለት እንችላለን። እንዲህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ጉዞ ከድጡ ወደ ማጡ መምጣቱን ያመላክተናል። ወደ ባሰ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ የከተተንም ለዚህ ነው። ፍልስፍናው ራሱ ብዙ እምቅ ችግሮችን በመያዙ ነው።

ሶሺዮ ፖለቲካችን ከድጡ ወደ ማጡ ከመምጣቱም በላይ ጠቅላላ የዴሞክራሲ ባህልን የሚይጠፋና የከፋ ችግር ውስጥ የሚከተን ሆኖ ያታያል። የዚህን የልዩነት ወይም የብሔር ፖለቲካ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር በሚገባ በመተንተን ማየት ችግሩን በሚገባ ለመመርመርና አማራጭ መፍትሄውን ለመፈለግ ስለሚረዳ በተጨባጭ ያሉትን ችግሮች ዝቅ ሲል አንድ ሁለት እያልን እንመልከት።

# III. የኢትዮጵያ ሶሺዮ ፖለቲካ ተግዳሮቶች

## 3.1. ማኅበራዊ ተግዳሮቶች

### 3.1.1. ማኅበራዊ ካፒታላችንን መሸርሸሩ

የመተማመን መትነን (Trust evaporation) እና

የማኅበራዊ ድር መነዳት (broken social networks)

በማኅበራዊ ካፒታል ንድፈ ሃሳብ ውስጥ ሁለት ጉልህ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ። እነዚህም መተማመንና ኔትወርክ ሲሆኑ ኖርሞችንም ያጠቃልላል። ፖለቲካችን ብሔር ተኮር ሲሆንና "የራስ በራስ (self) " ጨዋታ ሲመጣ የቡድኖች አባላት ኦፖርቹኒስቲክ ጸባይ እንዲያዳብሩ ማድረጉ አይቀርም። በተለይ ደግሞ ሥልጣን ላይ ያለው ብሔር ጠመንጃና ደህንነቱን ስለተቆጣጠረው "የኔ" ለሚለው ቡድን የሚያደላ ሊሆን ይችላል ብለው ሰዎች እንዲጠረጥሩ ማድረጉ አይቀርም። ይሄ የሶሺዮ ፖለቲካው ራሱ የሚፈጥረው ከባቢ ነው። በዚህ መሰረት የአገራችንን መተማመን በሶስትአቅጣጫዎች ብናይ ጥሩ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ግን ማኅበራዊ ሀብት እንዴሌሎቹ ሃብቶች ሀብት ነው። የሚያድግ ለኑሮ ኢንቨስት የምናደርገው ኀይል በመሆኑ ካፒታል ነው። ከዚህ ሀብት ውስጥ የመተማመን ካፒታላችንን በሶስት አቅጣጫ ስንፈትሽ አንደኛ ብሔር ዘለል (cross cultural trust) መተማመናችንን የሚሸረሽር ሁኔታ ተፈጥሯል። ቡድን ከቡድን ሊተማመን የማይችልበትን የሶሺዮ ፖለቲካ መዋቅር ነው የምንከተለው። የአንድ ብሔር ቡድን አባላት ከሌላው ብሔር ጋር ያላቸው እምነት መውረዱን ማየት ይቻላል። በየዩኒቨርሲቲው ብንሄድ በተማሪዎች ዶርም በአጠቃላይ ካምፓስ ሕይወት ውስጥ የብሔር ዘለል መተማመን ደረጃችን ወርዶ እናያለን። በአጠቃላይ ስናይ የዚህች አገር እጣ ፈንታ በአንድ ብሔር ላይ ብቻ እስኪወድቅ አገሪቱ የመገንጠል መብትን ተቀብላላች። ለምሳሌ ኦሮሞ መገንጠል ቢያምረው ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ማለት ነው። ሁለተኛው የመተማመን መመልከቻ አውድ ደግሞ ቀጥታ ሲሆን ይህም በመንግሥትና በዜጎች መካከል የሚኖረው መተማመን ነው።

በተግባር እንደሚታየው ኦህዴድ ብአዴን የመሳሰሉት ድርጅቶች በገዛ ብሄራቸው አባላት በጥርጣሬ የሚታዩ ናቸው። ለሕወሓት አጀንዳ መሳሪያ ተደርገው ይታያሉ። ጥቅም አስጠባቂ ተቀርቋሪ ሳይሆኑ የመበዝበዣ መሳሪያ ተደርገው ይታያሉና በኀይል በመረረ ሁኔታ ይጠላሉ። በሌላ በኩል በብሔር ፖለቲካ ጊዜ የአንድነታችን መገለጫዎችና የጋራችን ቤቶች የሚባሉት የፌደራል ተቋማትም እንዲሁ በአንድ ኀይለኛ ዘውግ በሕወሓት ተጠልፈዋል ተብሎ ይታመናል። ዘውጎች በፍርድ ቤት ላይ በምርጫ ቦርድ ላይ ያላቸው መታመን ሲበዛ ወርዷል። ዘ ፈንድ ፎር ፒስ የተባለው ተቋም ባጠናው ጥናት ላይ

የኢትዮጵያውያን ስቴት ለጂትሜሲ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። በዚህ ዓመት በወጣው ሪፖርት ላይ እንደሚያሳየው ዴንማርክ 0.9 ኖርዌይ 0.8 ስዊድን 1.0 ያስመዘገቡ ሲሆን ጋና 4.2 አስመዝግባለች። በአንጻሩ ኢትዮጵያ ያስመዘገበችው 8.2 ሲሆን ይህ እጅግ የወረደ አሳሳቢ ውጤት የሚያሳየው በመንግሥትና በሕዝብ መሃል ያለው መተማመን መትነኑን ነው። በሶስተኛ ደረጃ ያለው መተማመን መለኪያ ደግሞ የዜጎች (interpersonal trust) ሲሆን ይህ የመተማመን ሀብታችንም ያለቅጥ በፍጥነት እንዲወርድ ካደረጉት ምክኖቶች አንዱ የሶሺዮ ፖለቲካችን መንሻፈፍ ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያውያንን የያዛቸው ሃይማኖትና ባህል ካልሆነ አገሪቱ ዜጎቿችን አንድ ለአምስት ጠርንፋ በያዘችበት አገር የዜጎች መታመን ማረፊያው አንጨቆረር ነው። በአጠቃላይ በአገራችን ኢትዮጵያ በከፍተኛ ሁኔታ የመታመን መትነን (trust evaporation) ይታያል። በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ማኅበረሰብን እንደ ማኅበረሰብ አጣብቆ የሚይዘው ዋና ኀይል መተማመን ሲሆን መተማመን ከዚህ መሃል መትነን ሲጀምር ያ ማኅበረሰብ ሰላም ያጣል፣ ለመፍረስም ያዘመመ ይሆናል።

ስለማኅበራዊ ሀብት ስናወራ አንዱ ትልቁ የማኅበራዊ ሀብት ዓለባ (element) ኔትወርክ በመሆኑ በዚህ ደረጃም የአገራችንን ወቅታዊ ይዞታ መቃኘት ተገቢ ነው። የብሔር ፌደራል ሥርዓት ሲመጣና ልዩነት እየጎላ አንድነት እየኮሰሰ ሲሄድ የሚፈጠረው ነገር ግንኙነት እየቀነሰ መሄዱ ነው። በተለይ ወደ ጎን ከሚያያይዙን መሳሪያ መሃል አንዱ ቋንቋ ሲሆን ዛሬ አዲሱ ትውልድ አማራውና ኦሮሞው ለመግባባት ይቸገር ጀምሯል። የፌደራል ስርዓቱ ግንኙነትን መልቲ ካልቸራሊዝምን የሚገድብ በመሆኑ በአገሪቱ ያለው የብሔሮች መስተጋብር ቀንሷል ማለት ይቻላል። ብሔሮች በመሬት አንድነትና በኢኮኖሚ በፖለቲካ ስለተበጣጠሱ ግንኙነታቸው ቀንሷል። ይህም የአገርን ማኅበራዊ ሀብት ይጎዳል።

### 3.1.2. የግትርነትና ጽንፈኝነትን ባህርያት ማዳበር

የዚህ ሶሺዮ ፖለቲካ ችግር በአገራችን ውስጥ ጽንፈኛ አስተሳሰብን ማዳበሩ ነው። በዜጎች መሃከል የሚደረገው ክርክርና ውይይት ሁሉ ከብሔር ማንነት ጋር ቶሎ ስለሚያያዝ አምክህኖታዊና ሳይንሳዊ ውይይት እየጠፋ ይሄዳል። መደገፍና መቃወም ግትር ይሆናሉ። ይሄ የሶሺዮ ፖለቲካው የሚፈጥረው ድባብ ነው።

አንድ ማኅበረሰብ ማኅበራዊ ሀብትን ለማፍራት ብዙ ጊዜ ይወስዱበታል። ሲጠፉና ሲፈርሱ ደግሞ ለመገንባት ከባድ ነው። በመሆኑም በዚህ ደረጃ አገራችን የገጠማት ተግዳሮት አደገኛ ነው። ማኅበራዊ ሀብታችን ፈርሶ ድንገት በሆነ ክስተት ሀብታም ብንሆን እንኳን ያንን ሀብት አንጠቀምበትም።

## 3.2. ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች

ፖለቲካ የአስተዳደርን ጥበብ የሚያጠና ሳይንስ ነው ይባላል። ታዲያ በአንድ የፖለቲካ ጠገግ ስር መኖር ያማራቸው ቡድኖች አብረው ሲኖሩ የሚኖራቸው የሶሺዮ ፖለቲካ አቅጣጫ ፖለቲካዊ ሕይወታቸውን በጣም ይወስነዋል። በተለይ እነዚህ ብዙ ሕዝቦች አብረው ሲኖሩ ለሕይወታቸው ዋስትና የሚመርጡት ዴሞክራሲን በመሆኑ የሚከተሉት የሶሺዮ ፖለቲካ ሳይንስ ወደ ዴሞክራሲ በሚያደርጉት ጉዞ ላይ ጉልህ ሚና አለው።

በዚህ መሰረት አገራችን ኢትዮጵያ የምትከተለው የማኅበረ ፖለትካ ፍልስፍና በፖለቲካ ሕይወታችን ላይ ያመጣውን ተጽእኖ መመርመር ያስፈልጋልና ዝቅ ሲል ይህንን ጉዳይ እንመልከት።

3.2.1. ብዙሃን ይግዛ (Majority rule)

የዘውግ ፖለቲካ አንዱ ዋና ችግር ይሄ ነው። በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሰማኒያ ሁለት በላይ በብዛታቸው እጅግ የተለያዩ ቡድኖች ባሉበት አገር የፕራይሞር ዲያሊዝም ፍልስፍና የሆነውን የብሔር ፖለቲካ ስንከተል የሚያጋጨን ከዴሞክራሲ መርህ ጋር ከማጆሪቲ ሩል ጋር ነው። በዴሞክራሲ ጊዜ በተለይም በምርጫ ጊዜ ማጆሪቲ ሩል ፍትሃዊ ተደርጎ በዴሞክራሲ ሃሳብ ይታያል። በምርጫ ጊዜ ብቻም ሳይሆን በተለያዩ ውሳኔውች ጊዜም ይህ ጽንሰ ሃሳብ ፍትሃዊ ነው። ይህ ሃሳብ በብሔር ፖለቲካ ውስጥ ግን ችግሮች ይገጥሙታል። ከችግሮቹ አንዱ ዘውጎች ቁጥራቸውን ይዘው በመምጣት የፌደራሉን ሥልጣን በቡድን ቁጥር ለመቃረጥ ይመኛሉ። ኦሮሞው አማራው ብዙ በመሆኑ ዋና ዋና ሥልጣኖችን ይመኛል። ዴሞክራሲ በተፈጥሮው በግለሰቦች ነጻነት ላይ አተኩሮ ቡድኖችን መንከባከብ ሲሆን የብሔር ፖለቲካ ዘውግን ጠቅልሎ እንደ አንድ ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ ስለሚያየው ይህ ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል። አገራችን ከዚህ ካልወጣች የዚህ ችግር ሰላባ ሆነን ስለምንኖር ወደ ዴሞክራሲ እንዳናድግ ያደርገናል።

3.2.2. ለማንነት ድምጽ በኀይል መጋለጥ (Identity vote)

አንዱ ዴሞክራሲን ከሚያቀጭጭበት መንገድ ዜጎችን ለማንነት ድምጽ ማጋለጡ ነው። እንደ አዲስ አበባ ያሉ ከተሞች መሪዎቻቸውን ለመ ምረጥ ሲወጡ የተወዳዳሪን ችሎታ ከማየት ዘውግን የመፈለግ አዝማሚያ ይፈጠራል። ይህ ነገር ደግሞ እያደገና ኔትወርክ እየፈጠረ ሊሄድ ይችላል። ይህ በራሱ የዴሞክራሲን መርህ ያጠፋብናል። ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማለት በሃሳብ መካከል ፍክክርና ሙግት ተደርጎ የማረከንን መደገፍ እንጂ የደም ሐረግን እያየን እንድንከተል አይደለም። ይህ ችግር የሚታየው በምርጫ ወቅት ብቻ ሳይሆን ሙስናን ስንዋጋ ሁሉ ኮታ ውስጥ እንድንገባ ያደርጋል። ስራ ስንቀጠር አድልዎን ያሰፋል። በዚህና በመሳሰሉት ሁነታዎች ዴሞክራሲን ይዋጋብናል።

### 3.2.3. የማንነት ግጭት

ሌላው አደገኛ ነገር ደግሞ ዜጎችን በአካባቢያዊ ማንነታቸውና በብሔራዊ ማንነታቸው መሃል ግጭትን መፍጠሩ ነው። ይህ ግጭት በሁለት መንገድ ይገለጻል። አንድ በግል ሕይወት ሁለት ከሌሎች ጋር በምናደርገው መስተጋብር ጊዜ። ዜጎች ብዙ ማንነት ያላቸው ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ፍክክር ውስጥ የገቡት የብሔር ማንነትና ብሔራዊ ማንነት ጉዳይ ናቸው። እነዚህን ሁለት ማንነቶች ሳይጋጩ የሚያኖር ጠገግ መሆን አለበት አገር። ኢትዮጵያ ውስጥ ልእልና ያገኘው የሶሺዮ ፖለቲካ ጉዳይ የፈጠረው ነገር እነዚህን ማንነቶች እርስ በርስ እንዲታገሉ ያደርጋል። ብሔራዊ ማንነት በተፈጥሮው የሚለብሰው ነገር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ነው። በአንጻሩ ብሔር እነዚህን ልብሶች ማሰፋት ሲጀምርና ፖለቲካዊ ጉዳይን ኢኮኖሚን ከብሔራዊ ማንነት ጋር መጋፈፍ ሲጀምር ያን ጊዜ ሁለቱ ማንነቶች እንደ ባላንጣ ይተያያሉ። የረጋ አገር አንመሰርትም። አካባቢያዊ ማንነት ብሔራዊ ማንነትን አንተ እኮ የኔ ጥርቅም ውጤት ነህ ከፈለኩ በማንኛውም ጊዜ ላፈርስህ እችላለሁ ብሎ ተወጣጥሮ አፍጦ ይመጣል። ብሔራዊ ማንነት በበኩሉ እነዚህ ልብሶች የእኔ ናቸው ፖለቲካዊ ማንነትንና ኢኮኖሚን አትግፈፈኝ ይላል። በእኔ ጥግ ስር ሆነህ ባህልህንና ቋንቋህን እየካደምክ ኑር ለመልካም አስተዳደር ፍላጎትህ የዴሞክራሲን መርሆዎች ተቀበል ይላል። በዚህ ጊዜ ግጭት ይፈጠራል። ከብሔራዊ ማንነትና ከብሔር ማንነቴ የቱ ይበልጣል? እያልን አተካራ ውስጥ እንገባለን። ገብተናልም። አካባቢያዊ ማንነታቸው ያሸነፋቸው አንድ ጥግ ይዘው ብሔራዊ ማንነት ያሸነፋቸው አንድ ጥግ ይዘው የአገሪቱን ፖለቲካ በሁለት ጽንፎች ሲጓተቱ ይኖራሉ። ይህ ችግር ውጥረትን እያሰፋ ልዩነትን እያሰፋ አገር ያፈርሳል።

### 3.2.4. የቡድንና የግለሰብ መብት እንዲረማመሩ ያደርጋል

የሶሺዮ ፖለቲካችን ሲንሻፈፍ የሚመጣው ችግር አገራችን ኢትዮጵያ ስንት ችግር እያለባት ከቡድንና ከግለሰብ መብት የቱ ይቀድማል? እያልን እንድንነታረክ ማድረጉ ነው። አንዱ የግለሰብ መብት ከተከበረ የቡድንም ተከበረ ማለት ነው ይላል። ሌላው የቡድን መብት ቅድሚያ ይሻል ይልና ዜጎችን በቁና እያፈሰ እንከባከባለሁ ይላል። ይህ ቡድን ራሱ በሰፋው ቁና በተለያየ ምክኛት ያልሰፈሩ ዜጎች ሕይወት ምንም አያስጨንቀውም። የግለሰቦች መብት በዚያ ቡድን ስም ቢጨፈለቁ ብዙ ግድ አይለውም። ዴሞክራሲ ሁለቱንም የሚንከባከብ የአስተዳደር ጥበብ ነው። ዋናው ጉዳይ የቡድን መብት የሚባሉት ምን ምን ናቸው? የግለሰብ የሚባለሉት ምን ምን ናቸው? የሚለውን መለየቱ ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሁዋላ በመፍትሄ አሳባችን ላይ እናነሳለን።

### 3.2.5. የፖለቲካ ሥልጣን ቀመር ችግር

ሌላው ችግር ዘውግን የሥልጣን መወጣጫ ካደረግን የሚገጥመን ችግር የጋራ የምንላቸው ተቋማት አካባቢ ተገቢ የሥልጣን ቀመር ማሳጣቱ ነው። ከሰማኒያ በላይ ለሆኑ ብሔሮች በምን ቀመር ነው ከፍተኛውን የስራ አስፈጻሚ ሥልጣን የምናካፍለው? የሚል ጥያቄ ይነሳል። ሥልጣን በጎሳ መካፈሉ ራሱ የዴሞክራሲ አስተሳሰብ ባይሆንም ነገር ግን ሥልጣን እኩል ተካፍለን ትንሽ እንዳንረጋጋ ተፈጥሯችን ለቀመር አይመችም። ቤልጂየም ከፍተኛውን የስራ አስፈጻሚ ማለትም የሚንስትሮች ምክርቤትን ያዋቀረችው ሰባት ከደች ተናጋሪዎች ሰባት ከፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች አድርጋ ነው። ቤልጂየም የሪሶርስ ችግር የሌለባት በመሆኑና ሕዝቡ የነቃ በመሆኑ የሥልጣን ክፍፍሉ እኩል በመሆኑ የማንነት ፖለቲካ ችግር ጎልቶ አልታየም። ወደ አገራችን ስንመጣ ግን ለቀመር አስቸጋሪ ነው ያለን ተፈጥሮ። ዜጎች በየቀያቸው የየራሳቸውን ብሔር ተወላጆች ተሹመው ቢያዩም ትልቁ ሪሶርስና የፖለቲካ ኀይል ተሰብስቦ ወዳለበት የፌደራል ተቋማት አካባቢ የወንዛቸውን ሰው ማየት ይመኛሉ። ይህ ስሜት በብሔር ፖለቲካ ድባብ ውስጥ ከባድ በመሆኑ አገሪቱን አለመረጋጋት ውስጥ ይከታታል።

### 3.2.6. የጋራ መሪ እንዳናፈራ ያደርገናል

አንዱ ትልቅ ችግር በየፖለቲካ ፓርቲው የሚያድጉ መሪዎች በዚህ የብሔር ፖለቲካ ድባብ ውስጥ ሲቆዩ በውስጣቸው አካባቢያዊ ማንነትን አሳድገው ስለሚመጡ ለሁላችን የሚሁኑ አባቶችን እንዳናፈራ ያደርገናል። የምንመርጣቸው መሪዎች በመጀመሪያ ለራሳቸው ብሔር አድልዎ ላለማድረጋቸው ዋስትና እናጣለን። ሲስተሙ ምቹ ስለሚሆን ሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎች የአካባቢ ኔትወርክ ፈጥረው አድልዎ ፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርግብናል። የፖለቲካ መሪዎቻችንን ተክለሰውነት ደባል ስለሚያደርገው የጋራ መሪ ጥም ያደርቀናል።

### 3.2.7. ሁለት ዓይነት አርበኞች መፈጠራቸው

ሌላው ትልቅ ችግር ደግሞ የያዝነው የሶሺዮ ፖለቲካ ድባብ የብሔር አርበኞችን የሚያበዛ መሆኑ ነው። በርግጥ የብሔር አርበኝነት በራሱ ችግር አይሆንም። ነገር ግን አርበኝነቱ የሚገለጸው በፖለቲካም በኢኮኖሚም፣ በግዛትም፣ በታሪክም ሲሆን ጤነኛ አርበኝነት አይሆንም። እነዚህ አርበኞች ደግሞ የአንድነት ኀይል ነን ከሚሉ ብሔራዊ አርበኝነት ስሜት ከያዛቸው ጋር ይጋጫሉ። ከፍ ሲል ሁለቱ ማንነቶች ካልነው ሃሳብ ጋር ይዛመዳል። በአንድ የፖለቲካ ጠገግ ስር እነዚህ ሁለት አርበኝነቶች እየበዙ

ሲሄዱ የአገሪቱን የለሂቃን ክፍፍል በኀይል ይመታዋል። በዛሬው ጊዜ ኢትዮጵያ በለሂቅ ክፍፍል ከፍተኛ ችግር ላይ ናት። ፌይልድ ስቴት ኢንዴክስ እንደሚያሳየው ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት በለሂቃን ክፍፍል ከስምንት ነጥብ በላይ አስመዝግባለች። እጅግ አስፈሪ ውጤት ነው።

## 3.3. ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

ሶሺዮ ፖለቲካችን ሲበላሽ የማኅበረ ኢኮኖሚ ሕይወታችን በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻችንን ሁሉ ተጽእኖ ይፈጥርባቸዋል። በብሔር ፖለቲካ ጊዜ ሊመጡ ከሚችሉ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

### 3.3.1. የሀብት ክምችት ተስፋ መሆኑ ቀርቶ የግጭት መንስዔ ይሆናል

አገሮች ወደ ኢኮኖሚ ጥርመሳ ሲያመሩ ሀብት በተወሰነ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ እንዲጠራቀም ያደርጋሉ። በርግጥ ይህ ሀብት ሲያፈራ ተመጣጣኝ ስርጭት ይደረጋል። እስከዚያው ግን አገሪቱ ለመስፈንጠር እንድትችል ጥሪት ለመያዝ ደፋ ቀና ማለቷ አይቀርም። ደቡብ ኮርያና ቻይና እንደዚህ ነው ያደጉት። ደቡብ ኮርያ በአስራ ዘጠኝ ሰባዎቹ ጊዜ እንደነ ሂወንዴ በመሳሰሉ ግዙፍ የንግድ ተቋማት ላይ ያላትን አፍሳለች። ዜጎች ያላቸውን ጉልበትና ገንዘብ መስዋእት አድርገዋል። ሴቶች ጌጦቻቸውን ሳይቀር ሰውተዋል። ዓለምም በተለይም የተባበረችው አሜሪካ፣ አውሮፓውያን፣ ካናዳና አውስትሬሊያም ደግፈዋቸዋል። ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ ጥሪታቸው ሲያፈራ ዜጎች ሁሉ ከፍሬው ያገኙ ዘንድ የሀብት ስርጭት ስራ ሰርተዋል። አሁንም እየሰሩ ነው። በኢትይዮጵያ ሁኔታ እንዲህ አይነቱን ያልተመጣነ እድገት ተገን አድርጉ ለመስፈንጠር (unbalanced growth strategy) ኢትዮጵያ ምቹ የሆነ የፖለቲካ ከባቢ ውስጥ አይደለችም። የነኮርያና ደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ወደ እድገት ሲገቡ ሀብትን አንድ ቦታ ሰብስበው ቢስፈነጠሩና ዛሬ ልማታዊ መንግሥት ብንላቸው በወቅቱ ከፍተኛ የሆነ የብሔራዊነት ስሜት አንዱ ሃይላቸው ነበር። አገርን መውደድ ለኮሚኒቲ ሞቢላይዜሽን ስራና የሚጠራቀመውን ሀብት ዜጎች በጥርጣሬ እንዳያዩ አድርጓቸዋል። የሚጠራቀመውን ሀብት ተስፋ አድርገው ቆይተዋል። ኢትዮጵያ ከፈጠረችው የብሔር ኢኮኖሚ ግንባታ አንጻርና በሕገ-መንግሥቷ ላይ ካስቀመጠችው የብሔር የመገንጠል መብት አንጻር የሀብት ክምችት ተስፋ መሆኑ ቀሮ ለግጭት መንስዔ ይሆናል። ለዚህ ነው ዛሬ እነ ኤፈርት በያዙት ሀብት ዙሪያ ኢትዮጵያውያን ሲጠረጥሩ ሲነታረኩ የሚታዩት። ይህ ሀብት አፍርቶ ይንቆረቆራል ብለው ተስፋ እንዳያደርጉ ያደረገው የፖለይቲካው ተፈጥሮ ነው።

### 3.3.2. የብሔራዊ ሀብትና የብሔር ሀብት መካከል ግልጽነት አይኖርም

ብሔሮች የተፈሮ ሀብትንና ኢኮኖሚን ሲከፋፈሉ በአጠቃቀሙ ዘንድ ግልጽነት ይጠፋል። በመሬት አጠቃቀመቸው ዙሪያ በተፈጥሮ ሀብት የማዘዝ ደረጃቸው ዙሪያ ብዙ ጥያቄዎች እየተመዘዙ ቢወጡም ምላሽ ግን አያገኙም። የልዩ ጥቅም ጥያቄዎች ፍትሃቸውን ይበላዋል።

3.3.3. ያልተመጠተነ እድገትን ያመጣል

በአንድ አገር ውስጥ ኢኮኖሚ በቡድን ሲያዝ ያልተመጣጠነ እድገት በቡድኖች መካከል መኖሩ አይቀርም። እንደ ሕወሓት አይነቱ ሥልጣኑን ተገን አድርጎ ንግዱ ትርፋማ ሲሆን እነ አፋርና ቤንሽንጉል በዜሮ ወጥተዋል። ይህ ችግር ከፍተኛ የእድገት ልዩነትን በአንድ አገር ይፈጥራል።

3.3.4. ሙስናን ያዳብራል

ሕወሓት በዚህ የፖለቲካ መሰረቱና በዚህ የፖለቲካ ስተሳሰቡ ሥልጣን ላይ እቆያለሁ ብሎ የሚያስበው የብዙሃንን ፈቃድ በማግኘት አይደለም። ነገር ግን ከየብሄሩ የተወሰኑ ጥቅመኞችን በመመልመልና በሙስና ነው ስርዓቱን ማዋቀር የሚችለው። ሙስና የስርዓቱ የሲስተሙ ህልውና ነው። በርግጥ ሙስናው በገንዘብ ብቻ ባይገለጽም ነገር ግን ዋናው የመንግሥት መሰረት ሙስና እንዲሆን ያደርገዋል። ለዚህም ነው ዛሬ አገራችን ውስጥ ድርጅታዊ ምዝበራ በሰፊው የተንሰራፋው። የሙስና ኔትወርክ ጠንካራ የሆነበት ምክኛት አንዱ የስርዓቱ ሕይወት በመሆኑ ነው። በብሔር ላይ ተመስርቶ በአንስተኛ ቁጥር ባለው ማኅበራዊ መሰረት ሕወሓት ሥልጣን ላይ እንደማይቆይ ስለሚያወቅ ሙስናን አማራጭ አድርጎ ስለሚኖር ነው ዛሬ ሙስና የአገራችን ዋና ችግር የሆነው።

3.3.5. ለኮሚኒቲ ሞቢላይዜሽን የሚሆንን ኀይል ያሳጣል

ከፍ ሲል እንዳልነው እንደነ ኮርያ ያሉ አገሮች ሴማእል ኡንዶንግ የተባለውን የኮሚኒቲ ልማት እንቅስቃሴ ሲጀምሩ አንዱ ሃይላቸው ብሔራዊነትን ማራገብ ነበር። በብሔር ከተበጣጠሰች የዛሬዮቱ ኢትዮጵያ ይህን የህብረተሰብ ኀይል ተጠቅሞ የልማት ስራዎችን መስራት ለማይቻል ለኢኮኖሚ ጥርመሳችን ጉልህ ችግሮችን ይዟል።

# IV. ምን ይሻላል? የመውጫ ሃሳብ (Exit)

ከፍ ሲል የሶሺዮ ፖለቲካችን ችግር ውስጥ በመውደቁ በዚህ ሳቢያ እንዴት መላ ሕይወታችንን እንዳወሳሰበው ተመልክተናል። ችግርን መለየቱ አንድ ነገር ሆኖ ነገር ግን ታዲያ ለችግሩ አማራጭ መፍትሄ ማምጣቱ ደግሞ ተገቢ ነው። ለችግር መፍትሄ ስናፈላልግና የተሻለ ሶሺዮ ፖለቲካ ሥርዓት ስንፈልግ ከዓለም ተመክሮ መማር መልካም ቢሆንም ነገር ግን ኮርጆን ሙሉ በሙሉ ገልብጠን ተግባራዊ ለማድረግ መሞከራችን ሁል ጊዜ ሳንካ አለው። በመሆኑም የዓለምን የሶሺዮ ፖለቲካ አተያዮችና ንድፈ ሃሳቦች ጥቂት እናይና በመቀጠል የራሳችን ለራሳችን ወደ ሆነው የሶሺዮ ፖለቲካ ንድፈ ሃሳብ እናልፋለን። እንግዲህ ብዙ ማንነት ይዘን በአንድ ጠገግ ስር መኖር ያማረን ሕዝቦች እኛ ብቻ አይደለንም። እጅግ ብዙው የዓለም ሕዝብ ብዙ ማንነቶችን ይዞ በአንድ ጠገግ ስር ረግቶ ይኖራል። ለመሆኑ ዓለም ይህን ልዩነቱን ወዴት እያደረገው? ይህን ማንነቱን ምን እያደረገው ነው በአንድ የፖለቲካ ጠገግ ስር ረግቶ የሚኖረው? የሚለውን ለመመለስ የሚከተሉትን የሶሺዮ ፖለቲካዎች ንድፈ ሃሳቦች እንቃኝ። በአንድም በሌላም መንገድ የዓለምን ሶሺዮ ፖለቲካ የተቆጣጥሩት አሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

## 4.1. የዓለም የማኅበራዊ ፖለቲካ ንድፈ ሃሳቦችና ሞዴሎች ቅኝት

### 4.1.1. ሜልቲንግ ፓት (Melting pot)



ሜልቲንግ ፖት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። አሳቡ የሚያበረታታው ስደተኞች (Immigrants) ከሚኖሩበት አገር ባህልና ቋንቋ ጋር መስለው እንዲኖሩ ነው። ስደተኛ ተቀባዩ ማኅበረሰብ ቀድሞ በሰራው የጋራ እሴት ውስጥ ፈጥኖ ጠልቆ መግባት ማለት ነው ሜልቲንግ ፖት ማለት። የተዘለሉበትን አገር ሕዝብ ባህልህ ባህሌ፣ ቋንቋህ ቋንቋየ ብሎ ባለው የተዋሃደ ማኅበረሰብ ውስጥ መስሎ መኖር ሲሆን የዚህ ቲየሪ ዓላማ ብዙህነትን ፈጭቶና አቅልጦ አንድ ነጠላ ሕዝብ አድርጎ የማውጣት የሶሺዮ ፖለቲካ ኤንጂነሪንግ ነው። ይህ ቲየሪ በጽናት ያመነው ነገር ሆሞጂንየስ መሆን የአንድነትና የጥንካሬ ጉልበት አድርጎ ነው። አንድ ነጠላ ባህል ፈጥሮ ስደተኞች ሲመጡ በዚያ ጋን ውስጥ እንዲገቡ እየገፉ ብዙህ ባህሎች እንዳይፈጠሩ እያደረጉ ቀድሞ የተፈጠረን ባህል ጠብቆ የማቆያ ዘዴ ነው። ይህ ቲየሪ በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው ብዙ ሰው ወደ ሚፈልስባቸው አገሮች በተለይም አሜሪካ ፣ ካናዳና ሌሎች አገሮችም ነበር።

ሜልቲንግ ፖት ቲየሪ ከክፉ ልብ የሚመነጭ ሳይሆን ወደዚህ አሳብ ያመጣው የአንድነት ትርጉም፣ የብሔራዊ ማንነት ትርጉምና የኮሙኒኬሽን ጉዳዮችን ለማስተካከል ነው። ብሔራዊ ማንነት የሚባለውን ነገር ብዙህነት ያጠፋዋል በተጨማሪም ብዙ ሆኖ አንድነት ወይም አንድ ወጥ የሆነ ብሔራዊ ማንነት አይኖርምና ባህሎችና ዘሮች እየተዋሃዱ አንድ አካል መፍጠር አለባቸው ከሚል ነው። ስደተኞች ወደነዚህ አገሮች በየጊዜው እየፈለሱ የየራሳቸውን ባህል እየጠበቁ ከሄዱ ብሔራዊ ማንነት እየኮሰሰ ቡድነኝነት ሊያብብ ይችላል ። ይህ ቡድነኝነት ደግሞ የፖለቲካ መልክ ይዞ ሊነሳና የአገሪቱን ፍትህ ሊጎዳብን ይችላል ከሚል ነው። በተለይ እንደ አሜሪካና ካናዳ ያሉ አገሮች በሰፊው ከመላው ዓለም ሰው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ስለሚተምባቸው ይህ እጅግ ብዙ ሕዝብና እጅግ ብዙ ቡድን የአገሪቱን ብሔራዊ ማንነት ስንገነባ ምን ሊፈጥር ይችላል ከሚል ስጋትም ነው። ሜልቲንግ ፖት ሊፈታው ያሰበው ማኅበራዊ ችግር አንዱ ከፍ ሲል እንዳልነው የተግባቦትን ችግር መፍታት ብሎም ተግባቦትን ከፍ ማድረግ ሲሆን ሌላው ብሔራዊ አንድነትን ማጉላት በተጨማሪም ባህላዊ ቡድነኝነትን ተገን አድርገው ሊከሰቱ የሚችሉ እምቅ ግጭቶችን መቀነስ ነው።

በርግጥ ይህ ቲየሪ ተግባራዊ ቢሆን ሄዶ ሄዶ የሚፈጥረው ማኅበረሰብ ተፈጥሮአዊ ሆሞጂንየስ ማኅበረሰብ ሳይሆን “አርቲፊሺያል” የሆነ ወይም የተሰራ ሆሞጂንየስ ማኅበረሰብ ነው ማለት ነው። ቲየሪው ግቡን ከመታ የሚፈጠረው ማኅበረሰብ ቀልጦ የተሰራ ይሆናል ማለት ነው።

ወደ ፍልስፍናዊ መሰረቱ እንሂድና ፍጹም ውህደት አንድነትን ያመጣል የሚለው አሳብ የመጣው ባህልን አንድ ዋና የአንድነት ኢለመንት አድርጎ ከማሰብ የመጣ እምነት ይመስላል። አገሮች ይህን ቲየሪ ተግባራዊ ማድረግ ከፈለጉ የተለያዩ ፖሊሲዎችን እየቀረጹ ስደተኞች ወደ አገራቸው ሲገቡ ባህል እንዳያስገቡ ወይም የነሱን ባህልና ቋንቋ ለማስተማር ወይም ለማስረጽ ሳይሞክሩ ዘለው ወደ ነበረው ባህል በመግባት የጋራውን ባህል እንዲያጠናክሩ ነው። ይህ ግን በተግባር ሙሉ በሙሉ የሚገጥም አይደለም በርግጥ።

ይህ ቲየሪ ኮሙኒኬሽንን ከፍ ሊያደርግ ቢችልም፣ የብሔራዊ ስሜት ቢያጎለብትም፣ ለማንነት ድምጽ እድል ቢያጠብም ነቀፌታዎችም አሉት። አንደኛው ጉዳይ ስደተኛውን በፖሊሲ ወይም እድሎችን በማጥበብ ቶሎ እንዲዋሃድ ማድረጉ በራሱ በዘዴ የተሞላ አስገዳጅ ውህደት እንደተደረገ ያስቆጥራል።

በሌላ በኩል የሚቀርብበት ትችት ደግሞ አለ። ለምንድነው ብሔራዊ ማንነትን ከባህል ጋር የምናያይዘው? ለምን ሌላ ማንነት በጃችን ሰርተን ያንን ማንነት የጋራ አድርገን አንሸምም የሚል ነው። ከዚህ በተጨማሪ በዜጎች ዘንድ የባህል አንድነት ስሜት መፍጠሩና ባለብዙህ ባህል የሚሆኑበትን ሁኔታ መስበክ አይሻልም ወይ የሚል ነው። ባለ ብዙህ ባህል መሆን በራሱ ከብሔራዊ አንድነት ጋር የሚጋጭ አይደለም። ይህንን ብዙህ ሀብት ዜጎች የሚያዩበትን መንገድ በማረቅ እንደ አንድ የጋራ ሀብት አድርገው ነው ሊያስቡ የሚገባው ። ብዙ ባህል መኖር የሀብትና የብልጽግና ምልክት ነው። ቁም ነገሩ ይህንን ሀብት ማስተዳደሩና የዜጎችን ስምምነት ማስተካከሉ ላይ ነው።

ባህል ስንል ታለንት፣ እውቀት፣ ስኪል ማለታችንም ነው። በመሆኑም ስደተኞች ወደ ስደተኞች ወደ አንድ አገር ሲሄዱ ያላቸውን ታለንት ጥለው ዘፋኞች አንድ ዓይነት ዘፈን እንዲዘፍኑ፣ የምግብ አሰራሩ ተመሳሳይ እንዲሆን፣ የባህል ጥበብ ችሎታ ያለው ያንን ጥሎ ወደ ካናዳ፣ አርጀንቲና ወይም ሌላ ተቀባይ አገር ሲሄድ ያንኑ አገር መስሎ እንዲኖር ከማድረግ ይልቅ ስደተኛው ባህሉን በአንድ በኩል እንደጠበቀ በሌላ በኩል ግን ከሌሎች ባህሎችም እንዲለምድ፣ እንዲቀምስ፣ ባለ ብዙህ ባህል ስሜት ኖሮት እንዲኖር ማድረጉ ብልጽግና ይመስላል። ይህ አይነቱ አቀራረብ አገሮችን የባህል ጥበቦችን አቅርቦት ስለሚያሰፉላቸው ለቫራይቲስ ጥሩ ነው።

በሜልቲንግ ፖት ጊዜ ስደተኞች ወይም ቡድኖች ቋንቋቸውን ጥለው አንድ ቋንቋ መናገራቸው ብሔራዊ ማንነትን ያጎላልኛል ከሚልና ከነባሩ ሕዝብ ዘንድ የሚመጣውን የስደተኞች አልግባባ አሉ ሮሮ ለመቀነስ ይመስላል። በርግጥ አንድ ቋንቋ በሚነገርበት አገር ያሉ ሕዝቦች አንድ ነጠላ ሕዝብ ባለበት አገር ያሉ ሕዝቦች ፍትህና ሰላም ካጡ ብሔራዊ ክብራቸውን ያጣሉ፣ ብሔራዊ ማንነታቸውንም አጥብቀው አይዙም። ይሄ የሚያሳየው የሰው ልጅ ብሔራዊ አንድነቱን የበለጠ የሚወደው በሕግ ፊት እኩልነቱን ሲያይ ነው።

በመሆኑም ምንም እንኳን የሜልቲንግ ፖት አሳብ ቸር ሆኖ የምበላውን እየበላህ ኑር፣ የምጠጣውን እየጠጣህ አብረኸኝ ኑር፣ የምለብሰውን ልበስ ወዘተ. ቢሆንም የሚያስበውን ብሔራዊ አንድነት ግን አይፈጥርም። ርግጥ ነው በቋንቋ በኩል ተግባቦትን ይጨምራል። በርግጥ ቋንቋን በተመለከተ ዜጎች ባይልንጉዋል እንዲሆኑ ከማበረታታት በተጨማሪ ኦፊሺያል ቋንቋ ወይም የጎንዮሽ ቋንቋ ላይ ጠንካራ ፖሊሲ መንደፉና ማስለመዱ ከብሔራዊ ማንነት ጋር ይያያዛል አይያያዝም ሳይሆን ተግባቦትን ይጨምራል አይጨምርም በሚለው አቅጣጫ ነው መታየት ያለበት። እንግሊዘኛን መናገር የአሜሪካ ብሔራዊ ማንነት መገለጫ አይሆንም። ምክንያቱም ዓለም ሁሉ እየተናገረው ነውና። ቸሩዋ እንግሊዝም ይህን ቋንቋ ለዓለም ሕዝቦች ያስረከበች ይመስለኛል። በመሆኑም የአሜሪካ ብሔራዊ ማንነት ሊያያዝ የሚችለው ከቋንቋና ከባህል ጋር ሳይሆን ከተፈጥሮዋ ከዜግነት ጋር ከግዛት ጋር ከባንዲራና ከብሔራዊ መዝሙር፣ከሕገ-መንግሥት፣ ከዜግነት ቃል ኪዳን ወዘተ ጋር ነው ። በአጠቃላይ እነዚህን ሁሉ ቋጥሮ የሚይዘው ደግሞ አሜሪካዊ የሚለው የባለቤትነት ማንነት ይሆናል።

ሜልቲንግ ፖት ስለ ሃይማኖት የሚያነሳው የለም። በዚህ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ በሚገባ እምነቱን አለመግለጹ ቲየሪውን ትልቅ ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል። እንደሚታወቀው የሚፈልሱ ሰዎች ይዘውት ከሚንቀሳቀሱት ማንነት መካከል አንዱ ሃይማኖታዊ ማንነታቸው ነው። ታዲያ ቲየሪውን ጥያቄ ውስጥ ከሚከቱት መካከል አንዱና ዋናው ጉዳይ በዛ የሚለው የሰው ልጆች ባህል አንድም ከሃይማኖቱ መርሆዎችና ልምዶች የሚመነጭ ነው ወይም ባህሉ በሃይማኖቱ ተጽእኖ ውስጥ የወደቀ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ሃይማኖታዊ ማንነት ምን ይሁን በሜልቲንግ ፖት ቲየሪ የሚለው ጉዳይ ይነሳል። ሃይማኖታዊ ማንነት ከባህላዊ ማንነት ይልቅ ጠንካራ መሰረት ያለው ነው። የአመጋገብ ባህልን የአለባበስ ባህልንም ሊጫን ይችላል። በመሆኑም ሃይማኖታዊ ማንነትን ሜልቲንግ ፖት እንዴት አድርጎ ሊያየው እንደሚችል መገለጽ ነበረበት።

ዋናው ጉዳይ ሜልቲንግ ፖት ቲየሪ ባህልንና ቋንቋን ዘርን በአንድ ማሰሮ ውስጥ አስገብቶ አንድ አዲስ ነገር ለመፍጠር ከመሞከር ይልቅ ከማንነቶች ውስጥ ሊቀልጡ የሚገባቸውንና በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ማሰሮው ሳይገቡ ራሳቸውን ጠብቀው የሚኖሩ ማንነቶችን ቢለይ ጥሩ ይመስላል። ከባህላዊ ፖለቲካ ማንነት ጋር የተያያዙትን ወደ ማሰሮው ከቶ ሌሎች ማንነቶችን ግን ተከባብረው ከሕግ በታች እንዲኖሩ እሴት እንዲለዋወጡ ማስተማሩ ይሻል ነበር ብለው የሚያስቡ ምሁራን ሊኖሩ ይችላሉ።

አንዱ የተቀባይ አገሮች ወይም ብዝሃነትን የሚፈሩ ስጋት ተመሳሳይ ባህል ያላቸው ቡድኖች መደራጀት ሲጀምሩ ይህ ድርጅት ፖለቲካዊ ይዘት ውስጥ እንዳይገባ ነው። ይሄ ያለ ጥርጥር የፖለቲካ ቅርጽ ያለውን ብሔራዊ አንድነት ይጎዳል። በምርጫ ጊዜም ማህበሩ በሚያምነው ተመራጭ ወይም እጩ ላይ አባላትን የመግፋት ነገር ሊመጣ ይችላል። የግለሰቦችን መብት አሳልፎ መስጠት ሊመጣ ይችላል። በዘር ወይም በባህላዊ ማንነት ወይም በመልክዓ ምድር ላይ የሚመሰረቱ ማኅበራት በፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ተሳትፎ ማድረጋቸው ፖለቲካዊ ቅርጽ የሚይዘውን ብሔራዊ ማንነት ይከፋፍላል።

በሌላ በኩል ስለ ብሔራዊ ማንነት ስናወራ ማንነት አንጻራዊ ነው። ብዙ ጊዜ ይህቺ ዓለም የምትጠይቀው ማንነት ከዜግነት አኳያ ነው። በአብዛኛው የዓለም ጥያቄ ከማንነት አንጻር ሲታይ ከዜግነት ጋር የተያያዘ ከሆነ ዜግነት የብሔራዊ ማንነት ዋና መገለጫ በመሆኑ ያ ሊበቃ ይችላል። ከዚህ በላይ ግን የሜልቲንግ ፖት አንዱ ጭንቀቱ የአገሮችን መንፈሳዊ ምንነት ከመጠበቅ አንጻርም ሊሆን ይችላል። የአንድን አገር መንፈሳዊ ዳራ ሳይለወጥ ለማቆየት ይረዳል ከሚል ሊሆን ይችላል። ይህ ጉዳይ ደግሞ የአገሮች መንፈሳዊ ዳራ (spiritual realm) ነው።

በአጠቃላይ ሜልቲንግ ፖት ዋናው የተፈጠረበት አጀንዳ ከውጭ የተለያዩ ማንነቶችን ይዘው የሚመጡ ስደተኞችን እንዴት እናስተናግድ? ከሚል የመጣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እሳቤ ሲሆን በሆነ የታሪክ አጋጣሚ ለተገናኙና በተፈጥሮ ብዙህ ለሆኑ አገሮች ይህ ፍልስፍና ችግር ፈቺ አይሆንም። በስደተኞች ደረጃ እርግጥ ነው በተለይ የስደተኛው ቁጥር አንዳንድ እያለ የሚንጠባጠብ ከሆነና አናሳ ቁጥር ካለው ከመዋሃድ ሌላ እድል የለውም። በዛ ባለ ቁጥር ግን በስምምነት ላይ የተመሰረት ባህላዊ ምስለት (conventional cultural assimilation) የሚሻል ይመስላል። በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ ምስለት ማለት ስደተኞች በሁለት አቅጣጫ እንዲያድጉ የሚያደርግ ነው። አንዱ የገቡበትን ማኅበረሰብ ባህል እንዲለምዱ፣ እንዲቀምሱ የሚያበረታታ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸውን ባህል እንዲያቀምሱ ማበረታታት ነው። በስምምነት ላይ የተመሰረት ባህላዊ ምስለት እንደ ቡፌ ሊመሰል ይችላል። ሁሉም የእጁን ጥበብ በገበታ ላይ አውጥቶ ያስተናግዳል። አንድ ቡፌ ሆኖ ግን ሁሉም የተሳተፈበት ነው። በአመጋገብ ወቅት ሰው የፈለገውን ያነሳል። ያመነበትን ይጣፍጣል ያለውን ይመገባል። ሁሉንም ላይበላ ይችላል።

በስምምነት ላይ በተመሰረተ ምስለት ጊዜ ከዚያም ከዚህም ተጋጭቶና ቀልጦ የሚፈጠር አዳዲስ ባህልም ብቅ ሊል ይችላል። ባህሎች ወደ ጎን ሲነካኩ የሚፈጥሩት አዲስ ባህል ይኖራል። ያለውን እየጠበቁ፣ አዲሱንም እየተደሰቱ፣ የሚመጣውን እየተቀበሉ የመኖር ስምምነት ነው በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ ምስለት እምነት።

አሜሪካ በዚህ የተሻለችና ምሳሌ ትመስላለች። በመሆኑም ከሜልቲንግ ፖት ይልቅ በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ ምስለት ይሻል ይመስለናል። የሆነ ሆኖ መነሻችን ሜልቲንግ ፖት ሲሆን ይህ ቲየሪ የኢትዮጵያን ማኅበራዊ ፖለቲካ አይፈታም። በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ ምስለት ወደ ባህላዊ ቡድኖች የባህል አንድነት አድጎ መፍትሄ ያመጣል የሚል እምነት ያለኝ ሲሆን ወደ ኋላ በዚህ ላይ እንወያያለን።

ብዙህ የሆኑ አገራት በተለይም ኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ስለ ሜልቲንግ ፖት ማውራት የሚያስችል ከባቢ የላትም። ከሁሉም በላይ ተፈጥሮዋን ያገናዘበ፣ ለሰላምና ለልማት የሚመች የተሻለ ምክር ያስፈልገናል። በሌላ በኩል ሜልቲንግ ፖት ከፍ ሲል እንዳልነው የብሔሮችን ብሔር ዘለል ጋብቻ ያበረታታል። ይህ ግን አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። ጋብቻ የግለሰቦች ምርጫ ነው። በሕግ ብሔርን ከብሔር የሚያጋባ ወይም እንዳይጋቡ የሚያደርግ ፖሊሲ ማውጣት በዚህ ዘመን አይቻልም። በመሆኑም ቲየሪው ይህን ጉዳይ ጨምሮ ወደ ወደ ማሰሮ የሚከተው ከሆነ ተግባራዊ ሳይሆን አሳባዊ የሆነ ነገር ብቻ ይሆናል። በሌላ በኩል ግን እንደ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ሰው ስናስብ እንደ ሰለጠነ ሰው ስናስብ ጋብቻና ፍቅር የግለሰቦች ምርጫ ነው። ምርጫቸውን እናከብራለን።

በሌላ በኩል ሜልቲንግ ፖትን የምንረዳው የተለያየ የቆዳ ቀለም ያላቸው በአንድ የፖለቲካ ቅርጽ ባለው አገራዊ ማንነት ስር ተሰባስበው ተቻችለውና ተከባብረው መኖራቸውን ለማሳየት ከሆነ እኔ እደግፈዋለሁ። ሜልቲንግ ፖትን ለረጅም ጊዜ እንዲገባኝ የምፈልገውም በዚህ መንገድ ነበር። በርግጥ የ2008 እ. አ. አ. ብሔራዊ ምርጫም ይህንን ያሳያል ብየ ጽፌም አውቃለሁ። ይህን ችሎታ ሜልቲንግ ፖት ብንለው ይሻላል። ነጩ ጥቁሩ ሌላውም የሰው ዘር ፕሬዚደንት አባማን በአብላጫ ድምጽ መምረጡ የሚያሳየው አሜሪካ ወደ ተሻለ ማኅበራዊ ፖለቲካ ምህዳር መሻገሩዋን ነው። ይህ ችሎታ ሜልቲንግ ፖት ብለው ወይም ሜልቲንግ ፖት በዚህ መንገድ ተሻሽሎ ከቀረበ የሚደገፍ ነው ።

### 4.1.2. Cultural mosaic theory (Salad Bowl Theory)

ይህ ቲየሪ በካናዳ Cultural mosaic በመባል የሚታወቅ ሲሆን በአሜሪካ ደግሞ salad bowl ቲየሪ በመባል ይታወቃል። ይህ ጽንሰ ሃሳብ ከስሙ እንደምንረዳው በጣም በቀላሉና ስእላዊ በሆነ መንገድ የተገለጸ ሲሆን ዓላማው እነዚህ በባህል የተለያዩ ቡድኖች ከልዩነት ጋር አብረው መኖር መቻላቸውን ለማሳየት የቀረበ አሳብ ነው። የተለያዩ ባህላዊ ቡድኖችን ኑሮ ለማሳየት የሚሞክር ነው። አገላለጹ ምናባዊና ቀላል በመሆኑ ቶሎ ብንረዳውም ወደ ተግባር ሲገባ የሚነሱ ብዙ ጥያቄዎችን መመለስ ይጠበቅበታል። የጽንሰ ሃሳቡ መሰረቱ የሚደገፍ ነው። ልዩነትን፣ ብዙነትን መልቲ ካልቸራሊዝምን አይፈራም። አይፈራም ብቻ ሳይሆን እንደ ሀብት ማየቱ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይ ያደርገዋል።

ይህ ቲየሪ ባህላዊ ማንነትን ከብሔራዊ ማንነት ጋር ለማያያዝ አይሞክርም። ባህላዊ ማንነትን ለየባለ ባህሎቹ የተወ ሲሆን ምን አልባት ብሔራዊ ማንነትን የሚያየው ከዜግነት አንጻር ነው ማለት ነው። ዜግነት ዋና ጥላ ሆኖ በዜግነት የሚገኙ መብቶች ሁሉ የአንድነት መገለጫ ሆነው በፖለቲካ ጠገግ ውስጥ ያሉ ቡድኖች ሁሉ የራሳቸውን ባህል እየካደሙ ይኑሩ የሚል ነው። በአብዛኛው ለቀጥታ እድገት የተጨነቀ ሲሆን በዚህ ቲየሪ በሚገባ እንደገና ሊታይ የሚገባው ተዋረዳዊ ስለሆነው ግንኙነት ነው። የሰው ልጅ በአንድ የፖለቲካ ጠገግ ውስጥ ሲኖር በአንድ መልክዓ ምድራዊና አስተዳደራዊ ክልል ውስጥ ሲኖር እሴት መጋባቱ አይቀሬ ነውና ይህንን እውነት ተገንዝቦ ተዋረዳዊ የቡድኖችን እሴት መጋባት ጉዳይ መተንተን ያስፈልጋል። አሜሪካ የሳላድ ቦልን ቲየሪ ሙሉ በሙሉ ብትቀበልና በፖለቲካ ፖሊሲዋ ብታስገባ የስደተኞች አሰፋፈርን ጉዳይ ልታስብበት ነው ማለት ነው። ይህ ማለት በብሄራቸው መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ለማድረግ ልትገደድ ነው። ይህ አይነቱ አሰፋፈር ደግሞ ወደ ራስ ማስተዳደር ሊያመራ ይችል ይሆናል።

የሳላድ ቦል እሳቤ ባህላዊ ማንነትን ከስቴት ማንነት የመነጠሉ ስራ ለብዙህ አገራት ብሔራዊ ማንነት ጥሩ ምሳሌን ይሰጣል። የሜልቲንግ ፖት ትልቁ ችግር ባህላቸውን መጠበቅ የሚፈልጉትን መብት መጋፋቱ ሲሆን ሳላድ ቦል መብትን አክብሩዋል ይሁን እንጂ ወደ ጎን ደግሞ ከዚህኛውም ከዚያኛውም የሚማሩ ባለ ብዙህ ባህል መሆን የሚፈልጉትን ሊያበረታታ ይገባዋል። ስለ ባህል ስናወራ ዋናው ጉዳይ የሰባዊ መብት ጉዳይ በመሆኑ ዜጎች ወደ ጎንም ወደ ላይም ባህልን የሚያሳድጉበትን መንገድ ማሳየትና ይህን በመንግሥት ተቀባይነት እንዳለው መስበኩና ለዚህም የሚሆኑ ፖሊሲዎችን መቅረጽ ተገቢ ይመስላል።

ሳላድ ቦል ከፖለቲካ አንጻር የተሻለ አማራጭ ሆኖ ከተገኘ ከፍ ሲል እንዳልነው ለምሳሌ አሜሪካንን እንደ ቦል ብንቆጥር በውስጥ የሚኖሩት ቡድኖች ለዚህ የሚመች መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈርን ይጠይቃል። በሌላ በኩል የተባበረችው አሜሪካ በዳይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪዋ ከመልክዓ ምድር አንጻር ስታሰባጥር ይታያል። ይሄ የሚያሳየው የባህል መካፈልን አጥብቃ ታምንበታለች ማለት ነው። ሳላድ ቦልን ወደ ኢትዮጵያ በቀጥታ እናምጣው ብንል ወደ ብሔር ፌደራሊዝም የሚያመራ ይሆናል። ምን አልባት ፖለቲካውን ከማንነት ፖለቲካ አውጥተን በአንድ ብሔራዊ ፖለቲካዊ ማንነት ጥላ ስር አድርገን ግን ፌደራሊዝሙን በቋንቋ ላይ እንድናደርግ ይገፋናል። ከፍ ሲል እንዳልነው በተለይ የተለያዩ ብሔሮች ላሏት አገር ኢትዮጵያ ይህ ቲየሪ ተመራጭ ከማይሆንበት መንገድ መካከል ለተዋረዳዊ ግንኙነት ባለመጨነቁ የአገራችንን ትስስር አያጠነክረውም። ከዚህ በላይ የቡድኖች አቀማመጥ፣ ብዛት፣ እንዲሁም ደግሞ የተቀየጠው ማኅበረሰብ መብዛት፣ የተለየ መልክዓ ምድር የሌላቸውና የተበተኑ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ቡድኖች የሚያቅፍ አይደለም። ከሁሉ በላይ የብሔራዊ ስሜትን ለማዳበር አይጠቅመንም። ከዚህ ቲየሪ በባህሎች መካከል ሊኖር የሚገባን መከባበርና አብሮ መኖርን (coexistence) እንወስዳለን።


# Salad Bowl Theory




According to the Salad Bowl Theory there are times when newly arrived immigrants do not lose the unique aspects of their cultures like in the melting pot model, instead they retain them. The unique characteristics of each culture are still identifiable within the larger American society, much like the ingredients in a salad are still identifiable, yet contribute to the overall make up of the salad bowl. It is this theory that also accounts for the retention of the "something-American" hyphenation when identifying cultural identity. This theory is also referred to as pluralism.

MyShared

Cultural Mosaic



### 4.1.3. ብዝሃነት (Pluralism)



ብዙህነት (Pluralism) ከመነሻው አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ባህላዊ ቡድኖች በብዙሃን በተደጋጋሚ ሲዋጡ የመታየቱ ጉዳይ ያሳሰበው ፍልስፍና ነው። በመሆኑም እነዚህ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ባህላዊ ስብስቦች በብዙሃኑ መካከል በጽናት መቆም እንዲችሉ፣ ማንነታቸውን ባህላቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ የሚያበረታታና የሚታገል አስተምህሮ ነው። ባህሎች ሁሉ እኩል ናቸው ከሚል ሁሉ ከሚቀበለው የሞራል ትምህርት ጀምሮ በተግባር እነዚህ ዝቅተኛ ተዋንያን ያላቸው ቡድኖች መኖር እንዲችሉ ማገዝንም ያጠቃልልና ለጋራ ህልውና በጋራ መስራትን የሚጠቁም ነው። ። መልቲ ካልቸራሊዝምና ብዙነት የሚጋሩት ጉዳይ በባህል ቡድኖች መካከል መከባበር እንዲኖር መስበክ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ብሔራዊ ማንነትን ከአንድ ነጠላ ባህላዊ ማንነት አውጥቶ ብዙነትን እንደ አንድ የጋራ ማንነት መገላጫ ወይም ባህላዊ ማንነትን ከብሔራዊ ማንነት መገለጫ ማላቀቅ ነው።

በብዙነት የሚያምኑ ሰዎች በባህላዊ ቡድን ብዙነት ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ብዙነትን፣የኀይል ብዙነትንም ያምናሉ። መድብለ ፓርቲ ሥርዓትን ብቻ ሳይሆን ሥልጣንን ወደ ተለያዩ ሲቪክ፣ የሙያ ወዘተ ድርጅቶች ማውረድና ማካፈልን የሚያበረታታ እምነት ነው። በፖሊሲ ቀረጻ ጊዜ ዝንባሌ ያላቸው ቡድኖች ምክራቸው ተሰሚነት እንዲያገኝ የሚያሳስብ ነው። ብዙሆች በኀይል ስርጭት የሚያምኑ ሲሆን ከዚህ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚመነጨው አንዱ ሌላው እምነት ደግሞ ባህላዊ ብዙህነት ነው። ከፍ ሲል እንዳልነው ባህላዊ ብዙነትን ከሚፈታተኑ ጉዳዮች መካከል ዋናው ደግሞ ገዛፋው ቡድን አነስተኛውን ሲውጠው ማየት ነው። ይህንን መጠበቅና ብዙነትን ማበረታታት ከሰባዊ መብት ስጦታው በተጨማሪ ለሁለንተናዊ እድገትም ጠቃሚ እንደሆነ ስለተደረሰበት ነው።

ብዙነት የማኅበረሰባዊ ፖለቲካ ሳይንስ ዋና ጉዳይ የሆነውን ማን ይግዛ? (Who rule?) የሚለውን ጥያቄ የሚያየው ብዙ ይግዛ (let many rule) በሚል ነው። ብዙ ሲገዛ የተሻለ ጥራት ያለው ውሳኔ ይኖራል፣ የተሻለ ፍትህ ይበየናል፣ ልማት ይፋጠናል፣ ሰስቴነብሊቲን ያመጣል። በርግጥም ይህ አቀራረብ የዓለምን ሕዝብ የሳበና በአጠቃላይ እምነቱ በብዙሃን ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የቻለ አሳብ ነው። የጥቂት ሌሂቃንን አመራር በመቃወም በፖሊሲና በውሳኔ አሰጣጥ ዙሪያ ብዙዎች ዝንባሌ

ያላቸው መሳተፋቸው የአገርን ፍትህ ያሳልጣል። በርግጥም ኦሊጋርኪያዊ ሥርዓትን አምባገነናዊነትን የሚዋጉ ሕዝቦች ብዙነትን ከመፈለግ ነው።

ብዙነት ቀድሞ የታሰበው ከፖለቲካዊ አገዛዝ ማን ይግዛ? ጥያቄ የመጣ ቢሆንም ይህ አስተሳሰብ ቀስ እያለ ወደ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ብዙነትም ተሸጋግሯል። በጣም ዳይቨርስ የሆኑ ሕዝቦችን አብረው እንዲኖሩ የሚረዳ ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ መከባበርን እኩልነትንና በአንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ውስጥ አንዱ አንዱን ሳይጫነው የሚኖርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ምርጥ የፖለቲካና የባህል አቀራረብ ነው ይባላል። አገሮች በአንድም በሌላም መንገድ ይህን ትምህርት ያራምዳሉ። በሌላ በኩል ሃይማኖታዊ ብዙነትን የሚያራምዱ ኀይሎች ደግሞ እንዲሁ በሃይማኖቶች መካከል ተቻችሎ መኖርን፣ አብሮ ለመኖር አብሮ ማሰብንና መስራትን፣ የሃይማኖት ዲያሎጎችን የሚያበረታታ ነው።

መልቲ ካልቸራሊዝምም ይሁን ብዙነህት በአብሮ መኖርና አብሮ ለመኖር አብሮ መስራትን ቢያበረታቱም፣ ርስ በርስ አክብሮትን ቢሰብኩም የባህላዊ ሬለቲቪዝምን አስተምህሮ የሚቀበሉ አይደሉም። ብዙነት ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው የባህል ቡድኖች እንዳይዋጡ ሲደከም ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ባህላዊ አንጻራውያን (cultural relativst) አይደለም። ካልቸራል ሞዛይክ ግን ወደ ካልቸራል ሬለቲቪስቶች የተጠጋ አመለካከት አለው ።

ብዙሆች ባህላዊ ቡድኖች በጉርብትና ሲኖሩ ወይም በአንድ ላይ ተጠጋግተው ሲኖሩ በአንዳንድ ባህሎች ላይ ትችት ወይም ተቃውሞ ሊያሰሙ ይችላሉ። ይህ ተቃውሞ አንዱ ባህላዊ ልማድ ለአንዱ ትክክል ሆኖ ለሌላው ትክክል ስላልሆነ አይደለም። በዚህ ደረጃ በቀጠነ መልክ አይታይም። ይልቁን ባህላዊ ልማዱ ከዓጠቃላይ የሰባዊ መብት አንጻር ጫፍ የወጣ ባህርይ ካለውና ለጋራ ኑሮ ጠንቅ ከሆነ ብዙሃን ይቃወሙታል። ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ባህሎች የሚከወኑት ጫት በመቃም ወይም ሌላ አደንዛዥ እጽ በመውሰድ ቢሆን ፕሉራሊስቶች ይህንን ድርጊት ሊቃወሙ ይችላሉ። ይህን የሚያደርግ ባህላዊ ቡድንም እንዲያስተካክል ይመከራል ወይም ይወገዳል። የህጻናት ጋብቻ ባህላቸው የሆነ ቡድኖች እና ሌሎችም ከሰባዊ መብት አንጻር የማይሄዱትን ብዙሆች አይቀበሉትም።

ስለ ሃይማኖታዊ ብዙህነት ስናወራም ብዙሆች ምንም እንኳን በሃይማኖታዊ ልዩነት ቢያምኑም፣ ለአንዱ ትክክል የሆነው ለሌላው በስነምግባር ትክክል ባይሆንም አብረው እንዲኖሩ የሚያበረታታ ቢሆንም ሃይማኖታዊ ጽንፈኝነትን፣ ኢሰባዊ የሆኑ ሃይማኖታዊ ድርጊቶችን ያወግዛል።

በአጠቃላይ አብሮ ለመኖር የመቻቻሉ ጉዳይ ገደብ ያለው ሲሆን ይህ ገደብ ግን ልበ ሰፊ ነው። ትልቁ የሁሉንም ቡድኖች ትክክል መሆንና ያለ መሆን የሚፈርደው የሰባዊ መብት አለማቀፋዊ ኖርም

ይመስላል። በዚህ ከባቢ ስር ትናንሽ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የአጨፋፈር፣ ወዘተ ባህሎችን ልዩነት ያከብራል።

ፕሉራሊዝምን በሙሉ ልብ የተቀበለ መንግሥት ከሞራል አኳያ ብቻ ሳይሆን በተግባር ይህንን አሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የቡድኖችን አሰፋፈር የሚጠይቅ የቦታ ጉዳይ አያስነሳም ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ነው ወይስ በአጋጣሚ የተገኘውን ቡድን ተከባብሮ እንዲኖር መምከር ብቻ ነው የሚል ነገር ይጨመራል። የሚመስለው የሁለተኛውን ነው። ባህል በአብዛኛው የቡድን ስራ በመሆኑ ቡድኖች ደግሞ በአንድ የተወሰነ አካባቢ ተጠጋግተው ካልተገኙ ባህል አለ ለማለት አይቻልም። ይሁን እንጂ የሚመስለው ስደተኛ የሚቀበሉ አገራት በአጋጣሚ ቡድኖች በአንድ አካባቢ ሲገኙና አነስተኛ ቁጥር ያለው ቡድን ሲያቆሙ ያ ቡድን እንዲኖር ጥረት ይደረጋል ማለት ነው። በርግጥም ከዚህ ሌላ ያለው አማራጭ ማለትም ሁሉንም ብሔር በየ ብሄሩ የተለያየ ቦታ ማስፈር አስቸርጋሪ ስለሚሆን በፈቃዳቸው የተመሰረቱትን ቡድኖች መጠበቁ ጥበብ ይሆናል።

ይህን የብዙህነት ትምህርት ተገቢውን የሞራል ስንቅ በመሰነቁ ደረጃ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ብዙህ አገራት ያለው አስተዋጾ በጣም ጉልህ ነው። ብዙ ሰው የሚቀበለው ጉዳይ ነው። ከሁሉ በላይ ለምናመጣው ማንኛውም አይነት የማኅበራዊ ፖለቲካ አስተምህሮ መሰረት ይሆናል።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ይህን የሞራል ጉዳይ በልባቸው ከያዙ በኋላ ወደ ተግባር ለመግባት ከራሳቸው ተፈጥሮ ጋር ማገናዘብና የተሻለ ሲስተም መቅረጽ ያሻል። ቅድም እንደተነጋገርነው የብዙነት ምንጩ ከፖለቲካ ብዙነት አስተሳሰብ ነው። በመሆኑም ፖለቲካን የበላይ አድርጎ ባህልን ደግሞ በፖለቲካ ስር የሚተዳደር አድርጎ እንዲያየው አድርጎታል። ባህሎችን የሚያደራጀው፣ የሚንከባከበው የፖለቲካ ሥልጣን ያለው መንግሥት ነው። የመንግሥት ዘርፍ የባህል አሳላፊነትን ስራ እንዲሰራ የሚያበረታታ ነው። መንግሥት በየጊዜው ፖሊሲ እያወጣ እያደራጀ፣ ፌስቲቫሎች እንዲካሄዱ እያደረገ፣ ሙዚየሞችን እያደራጀ ባህልን ሊንከባከበው ይፈልጋል።

በሌላ በኩል ብዙነት የማንነት ፖለቲካን የሚቀበል አይደለም። ባህላዊ ብዙነት ሲል በአንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩትን እኩል የመኖር መብት እንዳላቸው ከማሳየት በላይ በማንነት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴን የሚያበረታታ አይደለም። አንዳንድ የግዛት ብዙሃን (territorial pluralists) አማኞች ወደዚያ ያደላ አሳብ ቢኖራቸውም በአጠቃላይ በመንግሥት እንክብካቤ ስር ብዙ ባህሎች እንዲኖሩ የሚያበረታታ ነው። ይሄ ጉዳይ በተለይ ፖለቲካዊ ማንነትና ባህላዊ ማንነት ተጣብቆ ለመጣባቸው ወገኖች ከባድ ነው። ስለ ብዙነት ሲያስቡ ስለ ራስን በራስ ማስተዳደር፣ ስለ ፖለቲካ አሰላለፍ መናገራቸው ነው። ይህ ጉዳይ ቸር የነበረውን የብዙነትን መንፈስ የሚያበላሽ ይመስለኛል። ብዙነት በተፈጥሮው ከቸርነት ከመካፈል አብሮ ከመኖር የተቀራኘ ሲሆን በአንጻሩ የብሔር ፖለቲካ እኔነት ይበዛዋል። ራስን በራስ ማስተዳደር፣ የራስን እድል በራስ የመወሰን፣ የራስ ባህል፣ የራስ ቋንቋ (me ... me ... me ...) ይበዛዋል። ይሄ ተፈጥሮው አብሮ በመኖር ላይ ሥነ- ልቡናዊና አልፎም ተግባራዊ አሉታዊ ተጽእኖዎች አያመጣም ማለት አይቻልም። አገር የሚቆመው በ “እኛ” በጋራ ስሜት ልእልና (national sovereignty) ነው። ይሄ የኔ ... የኔ ... ጉዳይ በርግጥ በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ዜጎችን ለአገራቸው ያላቸውን ታማኝነት (loyality) መሸማቱ አይቀርም።

ኢትዮጵያ በተለያየ የቦታ አቀማመጥ የሰፈሩ ብዙ ቡድኖች ያሏት አገር ሆና ግን ደግሞ በአንድ አገር ጥላ ስር ወይም በዜግነት ስር ለብዙ ብዙ ዓመታት ኖራለች። ይሁን እንጂ በተለይ ሁዋላ ላይ ከዘውዳዊ አገዛዝ ወደ አዲስ ሥርዓት ስትሻገር የባህል ማነጅመንቷ አካባቢ ችግሮች አሉባት። ከዚህም አልፎ ባህላዊ ቡድነኝነትን የፖለቲካ ጥብቆ ልብስ አልብሳው የብሔር ፌደራሊዝምን ተግባራዊ አድርጋ በመኖር ላይ ነች። ኢትዮጵያ ልኳ ያልሆነ የባህል ፖለቲካ ጥብቆ ልብስ አልብሰዋት የእናትነት ግርማዋን እያሳጣት ነው።

መንግሥት የብሔር ፖለቲካ ውስጥ የገባነው የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት ነው ቢልም የማንንት ጥያቄዎች አሁንም ሳይፈቱ ያሉ ሲሆን ከሁሉ በላይ አገሪቱ የሥልጣን ክፍፍሉ ሳይመቻት እንዲሁ ትኖራለች።

የዚህ የብሔር ፖለቲካ አንዱ ችግር ለብዙህ የፖለቲካ ሥርዓት አለመመቸቱ ነው። ፖለቲካዊ ብዝሃነት ወይም (political pluralism) ተግባራዊ ለማድረግ እውነተኛ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የፖለቲካው አሰላለፍ ራሱ የሚመች አይደለም። የብሔር ፖለቲካ በተፈጥሮው ነጠላ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓትን የሚደግፍ ዓይነት በመሆኑ ፖለቲካል ፕሉራሊዝም ችግሮች አሉበት። ፖለቲካዊ ብዙህነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መኖር ነው። በአንድ የፖለቲካ መዋቅር ውስጥ የተለያየ አይዲዮሎጂ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊቋቋሙ ይችላሉ። እነዚህ ፓርቲዎች ግን አንዱ ለአንዱ የቆመ ሆነው ነው የሚመሰረቱት። በሌላ አነጋገር አንዱ ስለራሱ ብቻ ሳይሆን ስለሌላውም ይኖራል ማለት ነው። አሜሪካ ውስጥ ያሉ ሁለቱ ግዙፍ ፓርቲዎች ማለትም ሪፐብሊካንና ዴሞክራት የሚከራከሩት ለሁለታችንም፣ ለአገራችንም የሚሆን እኔ የተሻለ አሳብ አለኝ የለም እኔ ነኝ የተሻለ አሳብ ያለኝ በሚል ነው። ሪፐብሊካን አሳባቸው ቢያሸንፍ ዴሞክራቶችም እንዲጠቀሙላቸው ነው። ዴሞክራቶች አሳባቸው ቢያሸንፍ ሁለቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ አገራቸውን እንዲጠቅሙ ነው። በመሆኑም በዴሞክራሲ ጊዜ

ፖለቲካዊ ፕሉራሊዝም ማለት በአሳብ መፋጨት ሆኖ ግን አንዱ ለሁሉም ጥቅም የሚቆምበት የፖለቲካ ባህል ነው። ወደ ብሔር ፖለቲካ ስንመጣ ግን ፖለቲካዊ ብዙህነት ብዙ መሰናክል ይገጥመዋል። አንዱ ችግር በብሔር ላይ የሚቆመው ፖለቲካ የሚኖረው ለሌላው ሳይሆን ለራሱ በልዩነቱ ላይ በመሆኑ የፕሉራሊዝምን እምነት ያበላሸዋል። በብሔር ፖለቲካ ጊዜ አንዱ ቡድን ስለሌላው አይኖርም። ቡድኖች የሚኖሩት ስለራሳቸው ነው። አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ የዚህ ፖለቲካ እምነት ተግባራዊ መገለጫ ነው። አንድ ቡድን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ከፈለገ መገንጠል ይችላል ሲባል ለመገንጠል ድምጽ የሚሰጠው ራሱ ነው፣ ከፈለገ ይሄዳል ካልፈለገ ይኖራል። ምክንያቱም የሚኖረው ስለ ራሱ ብቻ ነውና። የኦሮሚያ መገንጠል ሌላውን ብዙ ቡድን ጠቀመ ጎዳ የሚያሳስብ አይሆንም። በዚህ የብሔር ፖለቲካ እምነት ምክንያት ኦሮሚያ መኖር ያለበት ለራሱ ሲል ብቻ ነው። አማራው መገንጠል ቢያምረው የአማራ መገንጠል ለኦሮሞና ለሌሎች ክልሎች ችግር አለው የለውም ብሎ አያስብም ማለት ነው። ብድግ ብሎ በፈለገው ጊዜ ይሄዳል። ይህ ዓይነቱ የፖለቲካ እምነት ጉራጌው ስለ ራሱ ብቻ ሳይሆን ስለ ኦሮሞውም እንዲኖር፣ አደሬው ስለ ራሱ ብቻ ሳይሆን ስለ ኦጋዴኑም እንዲኖር ስለማያበረታታ አገር የሚባለውን ትልቅ ማንነት አጥፍቶ ግራ አጋባን። አንዱ ስለ አንዱ ስለማይኖር ራስ፣ ራስ፣ራስ (me ... me ... me ...) የሚል ስሜትን እያነገሰ “እኛ”ን ጎዳ። ስለ ፕሉራሊዝም ስናወራ አንዱ ትልቁ የፖለቲካ ፕሉራሊዝም ምሰሶ በአንድ ግዙፍ ብሔራዊ ማንነት ስር የተሰባሰቡ የተለያዩ የፖለቲካ ኀይላት አንዳቸው ስለሌላውም እያሰቡ ለጋራው ቤታቸው መሻሻል የሚሰሩበት ሥርዓት ነው። ይሄ ጉዳይ በብሔር ፖለቲካ ጊዜ በጣም አደጋ ላይ ይወድቃል። የብሔር ፖለቲካ በተፈጥሮም የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት አራማጅ አይደለም። በተፈጥሮው ነጠላ የፖለቲካ ሥርዓት አራማጅ ነው። ብዙ የብሔር ፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈጠሩ ማለት መድብለ ፓርቲ ተፈጠረ ማለት አይደለም። ሁሉም የየቡድኑን ፓርቲ ስለመሰረተ እንጂ አገሪቱ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን

በትክክል እየተደሰተችበት አይደለም። መድብለ ፓርቲ ሥርዓት በአሳብ የተለያዩ ፓርቲዎች አንዱ ለአንዱ ጭምር

የሚታገልበት ሥርዓት ማለት ነው። አንዱ ቡድን ስለሌላው ግድ የሚልበት በአብሮ መኖር (coexistence) አጥብቆ የሚያምን ነው።

4.1.4. የconstitutional patriotism ንድፈ ሃሳብ ታሪካዊ አመጣጥና የፍልስፍና መሰረቶቹ

ነገሩ እንዲህ ነው። ጀርመን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በምሥራቁ ክፍል ያለውን ግዛቷን በቀድሞዋ ሶቪየት ዩኒየን በመነጠቋና ቀጥሎም ቀዝቃዛውን የዓለም ጦርነት ተከትሎ በመጣው የዚህ ዓለም አተያይ ሳቢያ ጀርመን ለሁለት ጽንፍ አመለካከቶች ተዳረገች። ይህንኑ ቀዝቃዛውን የዓለም ጦርነት ተከትሎ ምዕራቡ ክፍል የምዕራቡን ዓለም አመለካከት ሲያስተናግድ ምሥራቁ ክፍል አጥባቂ የኮሚኒስት ደጋፊ በመሆን በወቅቱ ተፎካካሪ ለነበሩት ሶቪየት ዩኒየንና ምእራባውያን ሁለቱ ጀርመኖች ለሁለቱ ጎራዎች ደጋፊ በመሆናቸው ተለያይተው ለየብቻ ጎጆ ወጥተው መኖር ጀመሩ።

ሁለቱ ጀርመኖች ቋንቋቸው አንድ ይሁን እንጂ ይከተሉት የነበረው የዚህ ዓለም አተያይ ሁለት የተለያዩ ሰዎች እስኪያደርጋቸው ድረስ ልዩነታቸው ሰፋ። ምሥራቁ ክፍል የኮሚኒዝምን የሕይወት ፍሬዎች እያፈራ ቆየ። በአንጻሩ ምዕራቡ የካፒታሊስቱን ፍሬ እያፈራ ቆየ። ሁለቱ ወንድማማቾች ይከተሉት የነበረው የዚህ ዓለም የፖለቲካ ትምህርት በሕይወታቸው የተለያየ ፍሬ እንዲያፈሩ ስላደረጋቸው የማንነት ልዩነቶችን አመጡ።

የማርቲን ሉተር ሃይማኖታዊ ሰው መነሻ የነበረችውና የፕሮቴስታንት እምነት መነሻ የሆነችው ምሥራቅ ጀርመን ሃይማኖትን አራክሳ የነበረ ሲሆን ሌላው ቀርቶ አሁን ከተዋሃዱ በሁዋላ በ2012 OSW (Center for Eastern studies) ባደረገው ጥናት ካላት ሕዝብ ከሃያ ስድስት በመቶ በታች የሚሆነው ሕዝቡዋ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄድባት አገር ሆና ስትገኝ በአንጻሩ ምዕራብ ጀርመናዊያን በግልባጩ ሰባ ሶስት በመቶ የሚሆነው ሕዝቡዋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል። ይህ የሚያሳየው በሃይማኖት ዝንባሌያቸው ምን ያህል ተራርቀው እንደነበር ነው። በአጠቃላይ በዴሞክራሲ አረዳድ፣ በማህራዊ ሀብት ክፍፍል፣ ወዘተ የተራራቀ መረዳትን ከመያዛቸው የተነሳ ያፈሩት ስብእና ነው የተለያየ ማንነትን ያመጣው።

እንግዲህ ሁዋላ ላይ በአለም ላይ የኮሚኒዝም ሥርዓት መንኮታኮት ሲጀምር ምሥራቅ ጀርመንም በእጇዋ ያለውን የኮሚኒዝም ፍሬ ለማየት የጽሞና ጊዜ አገኘች መሰለኝ። ለምሥራቅ ጀርመን የለውጥ እንቅስቃሴ ያደረገው የውስጡ የሕዝቡ በኮሚኒዝም ፍሬ ያለመርካት ዋናው ጉዳይ ሲሆን የሶቪየት

ዩኒየኑ መሪ ሚካዔል ጎርቫቾቭ ሁዋላ ላይ ያመጡት የክፍትነት (openness) አሳብና ሶቪየትን እንደገና የማዋቀር ዓላማ እና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለውጦች እንደ ውጪያዊ ተጽእኖ የሚታዩ ናቸው።

የምሥራቅ ጀርመን ሕዝብ በወቅቱ በነበረው አስተዳደር አዝኖ ውስጥ ውስጡን ለለውጥ ራሱን ማዘጋጀት ጀመረ። ሁዋላ ላይ እነዚያ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የፕሮተስታንት እምነት ተከታዮች ቤተክርስቲያን ውስጥ ተሰብስበው አገራችን ውስጥ ምን እየሆነ ነው? የሚል ውይይት ከፍተው መወያየት ጀመሩ። የጽሞና ጊዜ አምጥተው ያለፉበትን የሕይወት ልምድ መገምገም ጀመሩ። በርግጥ ባፈሩት ፍሬ አልተደሰቱም ነበርና በቤተክርስቲያን ውስጥ የጀመሩት ተቃውሞ እየሰፋ-እየሰፋ ሄዶ እልፎች ተቀላቀሉት። በየሳምንቱ ሰኞ ሰኞ አንድ አመት የዘለቀ ተቃውሞ ተሰማ።

እኛ ነን ሕዝብ ማለት! (We are the people)

እኛ ነን ሕዝብ ማለት! (We are the people)

እኛ ነን ሕዝብ ማለት! (We are the people)

እያሉ መዘመር ሲጀምሩ በጣም መሰረታዊ የዴሞክራሲ ወይም የሕዝቦች ልእልና ጥያቄ ያነሱ መሆኑ ታወቀ። የአንድ ፓርቲ የበላይነትን በመንቀፍ የሕዝቦችን የበላይነት ጥያቄ ይዘው ታገሉ። ይህ የሚያሳየው ምሥራቅ ጀርመናዊያን ዴሞክራሲን መጠማታቸውን ብቻ ሳይሆን የማንነት ለውጥ ለማምጣት መዘጋጀታቸውንም ነበር።

የለውጡ ግፊት እየበረታ መጣና 1990 የሁለቱ ጀርመኖች ውህደት አሳብ መጣ። የሕዝቡ ንቅናቄ ያስደነገጣቸው የምሥራቅ ጀርመን መሪዎች የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ለማድረግ ደፍ ደፍ ሲሉ ውህደቱ ቀደመና ያሻሻሉትን ሕገ-መንግሥት ወዲያ ጥለው ሁለቱ ጀርመኖች እነሆ ለዳግም ውህደት በቁ።

ታዲያ ሁለቱም ወንድማማች ሕዝቦች ያለያያቸውን የበርሊን ግንብ አፍርሰው ይገናኙ እንጂ ባለፈው ግማሽ ምእተ ዓመት የሚጠጋ ጊዜ ያፈሩት የሕይወት ፍሬ የተለያዩ አድርጉዋቸው እንደነበረ ዛሬስ ይበልጥ ሳይገነዘቡ አልቀሩም። ለማናቸውም ውህደቱ ተሳካና የተባበረችውን ጀርመን ወጥ በሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ለመምራት ፖለቲከኞቹ ሲነሱ የብሔራዊ ማንነት ጥያቄ ተነሳ። ምንም እንኳን አንድ ቋንቋ ብንናገርም የተለያየን ሆነናልና ብሔራዊ ማንነታችን እንዴት ሊሆን ነው? ጀርመን ነን ስንል ምን ማለታችን ነው? ምንድነው አዲሱን ማንነታችንን የሚገልጸው? ሁለቱም ጀርመኖች የባህላዊው ብሔራዊ ማንነት (Traditional national identity) አልተመቻቸውምና እንዴትስ ነው ብሔራዊ ማንነታችንን የምንገነባው? የሚሉት ጥያቄዎች በወቅቱ ለነበሩ የጀርመን ፖለቲከኞች መከራከሪያና ዋና የመወያያ ጉዳይ ሆኖ ነበር። በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ ሃበርማስ የተባለ ጀርመናዊ የሶሲዮሎጂ ፈላስፋ የሕገ-መንግሥታዊ ቀናዒነትን ንድፈ ሃሳብ ይዞ ብቅ ያለው። እንደ ሃበርማስ እነዚህን የተለያየ ማንነቶች ያዳበሩ ሕዝቦች ሊያገናኝ የሚችል፣ በቅድመ ማንነታቸው ወይም (traditional national identity) ላይ ምቾት

ያልተሰማቸው ሕዝቦች ዘንድ ሌላ ድህረ ብሔራዊ ማንነት (post national identity) ሊመጣ የሚችለው ጀርመኖች ለሕገ-መንግሥታቸው ቀናዒ ሲሆኑ ነው። ሑላችን ለሕገ-መንግሥቱ ተገዢ ስንሆንና ለሊብራል ዴሞክራሲ ሕገ-መንግሥት እሴቶችና ኖርሞች ታማኝ ስንሆን የሰው መብት ስናከብር ስናስከብር በተቋማት ላይ መታመን ሲኖረን ያ የብሔራዊ ማንነታችን መገለጫ ይሆናል ማለት ነው የሚል ቁም ነገር አመጣ። በመሆኑም ሕገ-መንግሥታዊ ቀናዒነት (constitutional patriotism) የብሔራዊ ማንነታችንን ጥያቄ የሚፈታው ነው ብሎ ፖለቲከኞችን መጫን ጀመረ።

በወቅቱ የማንነት ጉዳይ ትልቅ ጥያቄ ሆኖባቸው ለነበሩት የጀርመን ፖለቲከኞችና በባህላዊው ማንነት ምቾት ያልተሰማቸው ጀርመኖች አዲስ ሊፈጥሩት ላሰቡት ማንነት ይህ የሃበርማስ አሳብ በርግጥም ልብ አሳራፊ ሆኖ በዚያን ጊዜ ተገኘ።

ለሁለቱ ጀርመኖች የመገናኛ መስመር ሕገ-መንግሥቱ ሆኖ ሊብራል በሆነ ዴሞክራሲ ውስጥ ብሔራዊ ማንነታቸውን እንዲጥሉ ሃበርማስ መምከሩ በርግጥ ጥበብ የተሞላና ወቅታዊም ነበር ማለት ይቻላል። ይህ የሃበርማስ አሳብ የጀርመንን ፖለቲከኞች ስሜት ያረጋ በመሆኑ እንደዚሁ የተለያየ ማንነትን ይዘው ብሔራዊ ማንነት ለመገንባት የተነሱ አገሮችም ለውስጥ ችግሮቻቸው መፍትሄ ይሰጣል ብለው ሞክረውታል። ቦስኒያ ለዚህ ተጠቃሽ ናት። ቦስኒያ ውስጥ በተለይ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ ይህ የሃበርማስ አሳብ በጣም የተቀነቀነ ነበር። የአውሮፓ ህብረትም ይህንን የሃበርማስን አሳብ እንደተጠቀመበት ይታያል።

ሃበርማስ ለሕገ-መንግሥቱ ቀናተኛነት ሲል ለፍትህ ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነት፣ ለሶሻል ዌልፌር መቆም እንደማለት ሲሆን እነዚህ ማንነቶች በርግጥ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ናቸው። አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት የሃበርማስ አሳብ አንድን የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የተነሳ ስለሆነ አገራዊ የሆነ ሰፋ ያለ ሶሊዳሪቲን ለማምጣት በጣም ይቀጥናል ይላሉ። በርግጥም አገር የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ፣ ፖለቲካዊ ይዘት ብቻ እንዳለው አድርጎ ማየቱና ብሔራዊ ማንነትን ከስቴት ጋር ብቻ ማጣበቁ ቀጣይነት ያለው ማኅበረሰብ (sustainable community) ለመመስረት አይሳሳም ወይ የሚል ትችትም ሊቀርብበት ችሉዋል ። ያም ሆኖ ግን በወቅቱ የጀርመኖች ልዩነት ፖለቲካ የወለደው በመሆኑ የሃበርማስም አቀራረብ ፖለቲካዊ እንዲሆን ተጽእኖ አድርጎበት ነውና አሳቡ የሞራልና የሲቪሊቲ ጉዳዮችን አንስቶ የሚገጥሙትን የኮሙኒከሽን ችግሮች በትእግስት በማየት ተቻችሎ ለመኖር ጥሩ ምክር ነበር ማለት ይቻላል። ሃበርማስም በወቅቱ ይህንን በሚገባ ያውቃል። የሃበርማስ ትልቅ ስጋት በውህደት ጎዳና ላይ ላለችው ጀርመን ይሄ ማንነት የሚባል ነገር ችግር እንዳይፈጥር ነገሮችን ማርገብ ነበርና በጣም ማስተዋል የተሞላበት አቀራረብ ነበር ማለት ይቻላል።

ነገሩ ግን ሁለቱ ጀርመኖች ወደ ውህደት እየመጡ የነበሩት የማንነት መራራ ጥያቄ ይዘው አልነበረም። ለሁለቱ ሕዝቦች ውህደት ትልቅ አስተዋጾ ያደረገው የምሥራቅ ጀርመን ሕዝብ የማንነት ለውጥ ለማድርግ ፍላጎትና ጥማት በማሳየቱ ወይም እጅ በመስጠቱ ነው። ምዕራብ ጀርመን ከነበራት ፖለቲካዊ ማንነት ንቅንቅ ሳትል ምሥራቅ ናት ለውጥ እያመጣች ወደ ምዕራቡ አሰተሳሰብ መቀላቀል ያማራት። በመሆኑም የሃበርማስ አሳብ የፖለቲከኞቹን ጥያቄ ወዲያ ያርግብ እንጂ ውህደቱን ያሳለጠው ግን አብዛኛው

የምሥራቁ ሕዝብ የማንነት ለውጥ በማምጣቱ ነው። ለዚህ ዋቢ የሚሆነን ጉዳይ ሁለቱ አገራት ወደ ውህደት ከመጡ በሁዋላ የጋራ ሕገ-መንግሥት ሲያረቁ የምሥራቁን ሕገ-መንግሥት ወዲያ ጥለው ከጥቂት ማሻሻያዎች ውጭ ምዕራብ ጀርመን ትጠቀምበት የነበረውን ሕገ-መንግሥት ነው እንዲቀጥል ያደረጉት። ይህ ማለት እነዚህ ሕዝቦች ለመዋሃድ መሃከለኛ የሆነ የሁለቱን ቅይጥ ሕገ-መንግሥት አላስፈለጋቸውም ነበር ማለት ነው።

ከፍ ሲል እንዳልኩት ምሥራቅ ጀርመን የማንነት ለውጥ ለማድረግ በመወሰኑዋ ስትጠላው የነበረውን ያንኑ የምዕራቡን አመለካከት እንደገና የሕይወቱዋ መሪ ለማድረግ መወሰኑዋ ነው የውህደቱ መሰረት። መሬት ላይ ያለው ሃቅ ይህ ከሆነ የሃበርማስ ሃሳብ በውስጠ ተዋዋቂ ምሥራቅ ጀርመን የጀመረችውን ወደ ምዕራቡ አስተሳሰብ የመዋሃድ (assimilation) እንቅስቃሴ ገፍታበት ሁለቱም ሕዝቦች ቀድሞ ምዕራብ ጀርመን እያሳደገችው የመጣችውን ፖለቲካዊ ማንነት የጋራ ድህረ ብሔራዊ ማንነት መገለጫ እንዲያደርጉት የሚገፋፋ ነው ማለት ይቻላል።

የሆነ ሆኖ ግን የሃበርማስ አሳብ ከፍ ሲል እንዳልኩት በፖለቲካው ለሂቅ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ ከስሜት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጉዳዮችን በማብረድ ለጀርመኖች ውህደት ትልቅ አፋጣኝ ሚና ተጫውቱዋል።

በአንዳንዶች ዘንድ ደግሞ ሃበርማስ ያመጣው ይህ አሳብ አዲስ ተደርጎ አይወሰድም። ቀድሞውንም ቢሆን አገሮች ሕገ-መንግሥት አውጥተው ሲተዳደሩ እንደ ሃበርማስ Constitutional patriotism ብለው አይሰይሙት እንጂ ዞሮ ዞሮ በውስጠ ተዋዋቂ ያው ለሕገ-መንግሥቱ ተገዢ በመሆን ሕዝቦች በአንድ የፖለቲካ ጥላ ስር ታምነው እንዲኖሩ ነው የሚፈልጉት። በመሆኑም አሳቡ በመጀመሪያ ደረጃ አዲስ አሳብ ሆኖም የቀረበ አይደለም። እንዴውም ሊብራል ዴሞክራሲ የሚባለው አመለካከት ይውጠዋል። ይህ ማለት የ Constitutional patriotism ተግባራዊ ገጽታው ያው ዞሮ ዞሮ ሊብራል ዴሞክራሲ ነው የሚሆነውና ምንም አዲስ ነገር አልመጣም እየተባለ ይተቻል። ቲየርው ይዞ የመጣው ጉዳይ የሞራል፣ የምክር፣ ስሜትን የመቀስቀስ አይነት ነው። ሌላው የሃበርማስን አሳብ ስናይ በርግጥ ሕገ-መንግሥታዊ ቀናኢነት የሚመጣው በሕገ-መንግሥቱ ላይ በመታመን፣ ተቋማትን በማፍቀር ከሆነ ማፍቀርና መደገፍ ከመነሻነታቸው በላይ ውጤትነታቸው ነው ጎልት የሚታየው። ዜጎች ለሕገ-መንግሥቱ አርበኞች እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? አርበኛ ለመሆን ውጤት ሊጠብቁ አይችሉም ወይ? የፖለቲካ ተቋማቱን ፍሬ እያዩ ነው እያደር የሚያፈቅሩዋቸው። ሌላው ደግሞ የሃበርማስ አሳብ ጠበብ ያለ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በመፍጠር ብሔራዊ ማንነትን የመገንባት አሳብ የያዘ በመሆኑ ቁርጠኛ የፖለቲካ መሪዎች ከጠፉና ተቋማት መርከስ ከጀመሩ ዜጎች አርበኛ ስለማይሆኑ አገር ሊፈርስ፣ ብሔራዊ ማንነት ሊደመሰስ ነው ማለት ነው። በርግጥ የሃበርማስ ቲየሪ ቀጭን ቲየሪ (thin theory) ነው የሚሉትም ለዚህ ነው። ወደ ዋናው አሳባችን ስንመጣ የሃበርማስን አስተያየት ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣትበመጀመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የማንነት ጥያቄ መረዳት ያስፈልጋል።

ጀርመኖች ያነሱት የማንነት ጥያቄ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ሲሆን የኢትዮጵያው ግን የተለየ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የማንነት ጉዳይ የመጣው የባህላዊ ቡድንን ማንነት ለብሶ የመጣ ሲሆን ቡድኖች በራሳቸው አባላት ራስን ማስተዳደር ይችላሉ የሚል አይነት አስተዳደርንና ስተዳደራዊ ችሎታን ከባህላዊ ማንነት ጋር አደባልቆ ብቅ ያለ የማንነት ጥያቄ ነው ያለው። ከዚህ የምንረዳው ሃቅ የኢትዮጵያ የማንነት ፖለቲካ ጥያቄዎች ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን አደባልቆ የመጣ በመሆኑ ችግሩ ሊፈታ የሚችለው በሶሲዮ ፖለቲካል ቲየሪ ነው። ማንነቶችን ማደባለቅና ለብሔራዊ ማንነት የጠራ መልክ ማጣት የኢትዮጵያ ዋና ችግር ነው። እንዲህ ከሆነ ታዲያ የሃበርማስ አሳብ የሚጨነቀው ቨርቲካል ለሆነውና ፖለቲካዊ ለሆነው ማንነት ብቻ በመሆኑ የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካል ችግር ሊፈታው በጣም ይቀጥናል። ላሉብን ማኅበራዊና ፖላቲካዊ ችግሮች የግድ የሶሺዮ ፖለቲክስ ንድፈ ሃሳብ ነው የሚያስፈልገንና የሃበርማስ አሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠረው የማንነት ጥያቄ መፍትሄ ሊሰጥ አይችልም። ከዚህ በተጨማሪም ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ ይህን የሃበርማስን አሳብ ይዘን ሕገ-መንግሥታዊ ታማኝነትን ብናውጅ በርግጥ በራሱ በሕገ-መንግሥቱ ላይ ሰዎች ጥያቄ አላቸው። አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ብቻዋን ብዙ ሰው አስኮርፋለች። በዚህ ሁኔታ ሕገ-መንግሥታዊ አርበኝነትን መፍጠር አንችልም።

ሌላ ምሳሌ እንይ። ካናዳን። ካናዳን ብናይ የኮቤኮችን የቡድን ማንነት ጥያቄ የሃበርማስን ቲየሪ በመጠቀም በሊብራል ዴሞክራሲ ሕገ-መንግሥት ሊፈታ አልቻለም ወይም ኮቤኮች በዚህ ልባቸው አርፎ አልታየም። ከፍ ሲል እንዳልነው የኮቤኮች ጥያቄ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ጉዳዮችን ይዞ ስለመጣ ሃበርማስ እንደሚለው በሊብራል ሕገ-መንግሥት የሚፈታ አልሆነም።

ኮቤኮች በርግጥ ካናዳ አገራቸው ባላት ሊብራል ዴሞክራሲ ውስጥ በፖለቲካ የመሳተፍ መብታቸው ተረጋግጧል። የካናዳ ዜጋ የሆነ ሁሉ በሃገሩ ፖለቲካ ለመሳተፍ ይችላል። የመጣበት ዘርና ቀለም ወይም ባህል አይከለክለውም። ስለዚህ የኮቤኮች የውስጥ ጥያቄ የሚመስለኝ የባህልና ቋንቋ ማንነትን ለመጠበቅ ነው። እንዳይዋጡ ከመስጋት ሊሆን ስለሚችል ትክክል ናቸው። ይህን ተገቢ ጥያቄ በቀጥታ የሚመልሰው ባህላዊ መንግሥትን ማቋቋም ይመስላል። በአገራቸው በካናዳ ውስጥ በኢኮኖሚና በፖለቲካ በግዛት ጉዳይ እንደማንኛውም ዜጋ እየተሳተፉ በሌላ በኩል ግን ባህላዊ ማንነታቸውን የሚጠብቅ ጠንካራ አስተዳደር ማቋቋም ይችላሉ። የቋንቋ ትምህርት ቤቶችን ከፍተው ማስተማር፣ ባህላቸውን መጠበቅ ማስተማር መንከባከብ ይችላሉ ይመስለኛል። ይህን በማድረጋቸውም በታላቋ ካናዳ ውስጥ ሳይዋጡ ባህላቸውና ቋንቋቸው ይኖራል።

በአገራችን ኢትዮጵያ በተለይ በ1960ዎቹ የተነሳው የብሔር ነጻነት ጉዳይ ሲነሳ ድንገት የተደባለቀው የቡድን ማንነትና የፖለቲካ ማንነት እንዲሁም መልኩ የደበዘዘው ብሔራዊ ማንነት ሳይጠራ እስካሁን ቀርቱዋል። ከቀዝቃዛው ጦርነት በሁዋላ የጽንፈኝነት ፖለቲካ የከሰመ ቢሆንም ኢትዮጵያ ግን የራሱዋን አለም ሰርታ አሁንም በቀዝቃዛው ጦርነት ውስጥ ትገኛለች። እጅግ በሰፋና ጽንፈኛ በሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ውስጥ ያለን በመሆኑ ዴሞክራሲ ሌላው አለም ላይ እያደገ ሲሄድ እኛ ጋር ቁልቁል ሲያድግ ይታያል።

የሃበርማስ አሳብ አንዱ ለኢትዮጵያ የማይሆንበት መንገድ ፖለቲካዊ ብቻ በመሆኑ ሲሆን ከሁሉ በላይ አንድ ቤት ሲሰራ ዋልታና ማገር ያስፈልጋል። ዋልታውንና ማገሩን እንደ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ልንመስለው እንችላለንና የጠነከረች መሰረት ያላትን ኢትዮጵያን ለመገንባት የሃበርማስ አሳብ አይበቃንም ሃበርማስ አሳቡን ያመጣውም ለጀርመን ነው። በመሆኑም እኛው ራሳችን አገር በቀል የሆነ

አንድ የሶሺዮ ፖለቲካል ቲየሪ ልናመጣ ያስፈልገናል ከሚል ነው ሁዋላ ላይ በመፍት ሄነት የማቀርበው የ CCU (Conventional cultural unity) አሳብ የቀረበው።

Constitutional Patriotism



## V. የመፍትሄ ሃሳብ

### 5.1. በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነት ፍሬም ወርክ



ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው ሁለት የተራራቁና የተቃረኑ ሶሺዮ ፖለቲካዎች ጽንፈኞች በመሆናቸው አንዱ አንዱን በመደፍጠጥ ላይ ኖረዋል። ባለፈው ጊዜ ብሔራዊ አንድነት ዘውጋዊ ማንነትን እየረመረመ የመጣ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ዘውጋዊ ማንነት ብሔራዊ ማንነትን እየረመረመ ሲሄድ ይታያል። እነዚህ ማንነቶች ተቻችለው እንደመኖር አንዱ ባንዱ ላይ ተረማምዶ ጠንካራ ሆኖ ለመውጣት የሚያደርጉት ጥረት የአገሪቱን ሶሺዮ ፖለቲካ ውጥረት ውስጥ ከቶታል። እነዚህ ሁለት ጽንፈኛ የፖለቲካ ስርአቶች ትልቁ ችግራቸው የቡድኖችን ፈቃድ አለማግኘታቸው ነው። ቡድኖች ያላቸውን ሁሉ መስዋእት አድርገው ብሔራዊ ማንነትን አጥብቀው ይዘው አካባቢያዊ ማንነትን ችላ እንዲሉ አልተስማሙም። አይስማሙምም። ወይም ደግሞ ብሔራዊ አንድነታቸው ኮስሶ የአካባቢ ማንነታቸው እንዲጎለብት አልተስማሙም። አይስማሙምም። ይህ የአገሪቱ ሶሺዮ ፖለቲካ እንዲሻሻል ካስፈለገ ኢትዮጵያ የግድ ወደ አዲስ ኪዳን መሻገር ይኖርባታል። የግድ አንድነትንና ልዩነትን ማስትዳደር የሚችል ሥርዓት ያሻስታል። ያለፈችበት የሕይወት ልምድና አሁን ያለችበት ሁኔታ ተደማምረው አዲሱን ሕይወቷን እንድትጀምር ለማድረግ አዲስ ኪዳን ያሻታል። ይህ የምናስተዋውቀው የአዲስ ኪዳን ፍሬም ወርክ እነዚህ ሁለት ማንነቶች እርስ በርስ ሳይረማረሙና ሳይጋጩ የሚኖሩበትን መላ የሚያመጣ ነው። አዲስ ኪዳን የሚያሰኘን ኢትዮጵያ በማኅበራዊ ጉዳዮች በተፈጥሮ ሀብት ጉዳዮች በፓለቲካ አሰላለፍ ጉዳዮች ግራ አጋቢ ምእራፍ ላይ ስለሆነች ነው። ቡድኖች ኪዳን አድሰው በተሻለ ቃል ኪዳንና ውሳኔ የአገር ዋልታና ማገር የሆኑ ስምምነቶችን ለመጣል ነው። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ይህ የአዲስ ኪዳን ንቅናቄ በአንድ ንድፈ ሃሳብ ተጠቅልሎ የቀረበ ሲሆን ጽንሰ ሃሳቡ በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነት ይባላል (Conventional Cultural Unity) ወይም CCU ይባላል። ። ይህ ሃሳብ የያዛቸው ጭብጦች አራት ጉዳዮች አሉ። እነዚህ አራት ጉዳዮች አዲሱን የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካ ቤት ለመስራት ዋልታና ማገር ይሆናሉ።

CCU መሰረቶች

ኪዳን (Covenant)

ሄራ (Basic Law)

አስተዳደራዊ መዋቅር

የቋንቋ ማኔጅመንትና አጠቃቀም

እነዚህ ከፍ ሲል የተነሱት አራት ጉዳዮች አዲሱን የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካ ቤት እንደገና ለማነጽ የመሰረት ድንጋዮች ዋልታና ማገር ናቸው።

በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነት የሚለውን አገር በቀል የሶሺዮ ፖለቲካ ሞዴል ስናስተዋውቅ ይህ ጽንሰ ሃሳብ የሚይዛቸው እነዚህ ከፍ ሲል የተነሱት ጉዳዮች ሲሆኑ እያንዳንዳቸውን ዝቅ ሲል ለማብራራት እንሞክር።

### 5.1.1. አዲስ ኪዳን

ኪዳን ስንል ሕገ-መንግሥት ማለታችን አይደለም። የቡድኖች ወይም የዘውጎች ኪዳን የምንለው የቡድኖችን አዲስ ቃል ኪዳን (Covenant) ነው። አዲሲቱ ኢትዮጵያ አዲሱን ሶሺዮ ፖለቲካዋን አሃዱ ብላ ከዚህ ብትጀምር እንዳለ የማኅበረ ፓለቲካዋን መሰረት ይለውጠዋል ። አዲስ ኪዳን የፖለቲካዋና የአስተዳደሯ መሰረት ቢሆን ወደ ተሻለና ግልጽ ወደ ሆነ ሶሺዮ ፖለቲካ ለመወርወር የማእዘን ድንጋይም ይሆናታል። ኪዳኑ የሚያስፈልግበት ሌላው ምክንያት ኢትዮጵያን ዘላለማዊ አገር አድርጎ ከትውልድ ትወልድ የሚተላለፍ ሰነድ ለማውረስ ነው። ይህ ሰነድ መጪውን ትውልድ ግልጽ በሆነ የሶሺዮ ፖለቲካ ሲስተም ውስጥ ስለሚከተው ኢትዮጵያን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሳለፍ ብሎም ደግሞ አዲሱን ትውልድ አገሪቱ ከገባችበት የብሔር ጥያቄ አዙሪት አውጥቶ ስለሚያራምድ ነው። አጠቃላይ የፖለቲካ መሰረታችንን ግልጽ በሆነ መሰረት ላይ ለመጣል ይህ አዲስ የቡድኖች ኪዳን መሰረት ስለሚሆነን ነው። ቡድኖች አዲስ ኪዳን ሲያደርጉ ብሔራዊ ፈውስና መግባባትም ስለሚመጣ ነው። አዲስ ኪዳን ስንል ታሪክ የለም ማለት አይደለም። ኢትዮጵያን ማፈርስና እንደገና መጀመር አይደለም። እንደገና ለማነጽ ነው። የተንሻፈፈውን ለማስተካከል፣ የፈረሰውን ለመጠግን ነው። ኢትዮጵያን እንደገና ለማነጽ ስንነሳና የአገር ቤታችንን ስንሰራ ከላይ ሞገስ የሚሆነንን አንድ የቡድኖች ሁሉ ኪዳን እንቅረጽ ከሚል ነው። እንግዲህ ኪዳኑ ቡድኖች ተማምለው የሚያቆሙት ሃውልት የሚያጸድቁት ሰነድ ሲሆን የዚህ ኪዳን ዋና ይዘት ምንድነው? ካልን ዋናው ጥሪ የመስዋእትነት ጥሪ ነው። ይዘቱ <u>መስዋእትነት</u> ነው። እንደሚታወቀው በአገራችን ታሪክ ውስጥ ዘውጋዊ ማንነት በተደፈጠጠበት ዘመን ባህልና ቋንቋ የሚያድግበት ሁኔታ አልነበረም። ኢትዮጵያ ስትመሰረትም በቡድኖች ኪዳን ሳይሆን በኀይል ነበር። አሁን ደግሞ በኀይል ተሰብስበናልና እንደገና አይነት በኀይል ተበታተንን። በዚህ ጊዜ ባህልና ቋንቋ እንዲያድግ ተደረገና ብሔራዊ ማንነት ደግሞ ተደፈጠጠ። ቡድኖች ኢትዮጵያን ተቀራመቱ። መሬት፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ ፖለቲካዊ ማንነት፣ ቋንቋና ባህል ሁሉ ለየብቻ ተኮለኮሉና ጨዋታው በየቤትህ እደር ሆነ። በዚህ መሃል የጋራ የምንለው ነገር ከእይታችን ተሰወረ። ኢትዮጵያ ሁሉን አጣች። አገር ሊመሰርቱ የሚችሉ ካስማዎችን ሁሉ ነቃቅለን በየብሄሩ በየሰፈሩ ተከልን። ስለዚህም ብሔራዊ ማንነት ኮሰሰ ብቻ ሳይሆን ጨርሶ ጠፋን። በዚህ ያዘኑ ኢትዮጵያውያን አያሌ ናቸው። ሁል ጊዜም ያዝናሉ። በመሆኑም አዲሱ ኪዳን የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ቡድኖች ተሰባስበው ተወያይተው ቀላል በሆነ ቋንቋ አንድ ኪዳን ይገባሉ። ይህ ኪዳን ደግሞ ያላቸውን ባህል፣ ቋንቋ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ ፖለቲካዊ ማንነት ሁሉ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት እንሰዋለን የሚል ቆራጥ የአገራችን ከፍተኛ ኪዳን ነው። አንዱ የኪዳኑ መሰረት የኢትዮጵያውያን የቸርነት ባህልም ነው። ሁለተኛው የኪዳኑ መሰረት ይህቺ አገር በኀይል ከተመሰረተች በኋላ ቡድኖች ሁሉ በጋራ የሰሩት ብዙ አለምን ያስደመመ ታሪክ አላቸው ብዙ የጋራ እሴት ገንብተዋል ደማቸውን ተካፍለው ተዋልደዋል። አገራቸውን ኢትዮጵያን ይወዳሉ አንድነትን ይሻሉ የሚል ነው። እንግዲህ ቡድኖች አዲስ ኪዳን ሲገቡ በኪዳኑ ጊዜ ቡድኖች ሁሉ ያላቸውን ሁሉ መስዋእት ካደረጉ በሁዋላ ፖለቲካዊ ማንነትን አደባልቀው

ይቀጥላሉ። አንድ ሰፊ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ይፈጥራሉ። ነገር ግን ባህላዊ ማንነትን ከመስዋእቱ ኪዳን በሁዋላ ቡድኖች ሁሉ መልሰው የሚወስዱበትንና የሚንከባከቡበትን ረቂቅ ስምምነት ይስማማሉ። ይህ ማለት ቡድኖች ባህላዊ ማንነታቸውን ከፍ ላለው ኢትዮጵያዊነት ቢሰውም ነገር ግን ዘውጋዊ ማንነት የኢትዮጵያ ማንነትም የቡድኖች ማንነትም ሆኖ ዘላለም እንዲኖር የራሱ አስተዳደር ይበጅለታል። ፖለቲካዊ ማንነትና ባህላዊ ማንነት ለየብቻ በተለያየ ሲስተም ያድራሉ። ኪዳኑ ሁሉን መስዋእት አድርጎ ባህልና ቋንቋን መልሶ ለየቡድኖቹ ያከፋፍላል። ቡድኖች ሁሉ የኢትዮጵያም የነሱም ንብረት የሆነውን ቋንቋና ባህል በሚፈጠረው ሲስተም ዘላላም ሲጠብቁት ይኖራሉ። ይህ ነው የኪዳኑ ዋና መሰረት። የኪዳኑ ዋና ይዘትም ኑ ያለንን መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህሎች እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንሰዋ የሚል ነው።

የኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን ዋና ማእከላዊ ይዘት መስዋእትነት ነው። እኛ የኢትዮጵያ ቡድኖች ያለንን ሁሉ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሰውተናል የሚል ኪዳን ማለት ነው። በአጠቃላይ አዲስ ኪዳን የምንለው ሪፈረንደም አይደለም። ኑ የፈረሰውን ቅጥራችንን እናድስ ኑ አገራችንን እንደገና እናንጽ። ኑ አገራችንን ግልጽ በሆነ ስምምነት እናንጻትና ሰነድ ይዘን ኪዳን ገብተን ተማምለን ወደ ፊት እንሂድ የሚል ጥሪ ያዘለ ነው። አዲስ ኪዳን የነፍስን ጽዳት ለማምጣት ለብሔራዊ መግባባት መንገድ ነው። አዲስ ኪዳን የምንለውም ያለፈውን ለመርገም ሳይሆን ወደፊት ለመራመድ ለቡድኖች ሁሉ መሳጭ የሚሆን ኪዳን ገብተን ወይም ስምምነት ተፈራርመን የፈረሰውን ቅጥር አድሰን ወደ ፊት እንራመድ ማለት ነው። ቡድኖች የሚገቡት ኪዳን ግልጽ ነው። ያለንን ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል ቋንቋና የተፈጥሮ ሀብት ሁሉ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሰውተን እየተንከባከብን ለመኖር ቃል ገብተናል የሚል ከፍተኛ ኪዳን ነው። ኢትዮጵያውያን ይህን ኪዳን ፈጽመው ሃውልታቸውን ሰርተው ወደ አዲስ ኪዳን ሲገቡ የመስዋእትነትን ሚስጥር ድራማቲክ በሆነ መንገድ ለዓለም ያሳያሉ። የኪዳኑን ማእከላዊ ጉዳይ የሆነውን የዚህን የመስዋእትነት ጉዳይ ሲያሳዩ የፍቅርን ታላቅ ሚስጥር ይገልጻሉ። ቡድኖች ወደ ጎን ለሚኖራቸው መተሳሰርና ህብረት የሚፈጽሙት መስዋእትነትና ወደ ላይ ማለትም በሥልጣናትና በሕዝቡ መካከል በሚኖረው ግንኙነትም እንዲሁ በቡድኖች የመስዋእቱ ኪዳን ላይ የሚቆመውን መንግሥት በመመስረት መስቀለኛ ሥርዓት ፈጥረው አዲሲቱን ኢትዮጵያን እንዲገነቡ ነው የCCU ጥሪ።

በአጠቃላይ ይህ ከሕገ-መንግሥት ሰነዱ በላይ የሚውለው የዜጎችና የቡድኖች ኪዳን የሚከተሉት ይዘቶች ቢኖሩት ጥሩ ነው።

# የኢትዮጵያውያን ኪዳን

**1.** እኛ ኢትዮጵያውያን ብሄሮች ያለንን የተፈጥሮ ሃብት ክህሎትና
እውቀት ሁሉ ለኢትዮጵያ ሃገራችን ሰውተናል:: የእኔ የእኔ የምንለው የውስጥ የብሄር ድንበር የለም።
ኢትዮጵያ የእኛ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ናት።

**2.** እኛ ኢትዮጵያውያን የማትከፋፈል የተባበረች ኢትዮጵያን ለትውልድ ለማሳለፍ ቃል
ገብተናል:: በየዘመናቅቱ ታሪክ እየሰሩ አገራችንን ከዚህ ላደረሱ አባቶችና እናቶች ልዩ ክብር አለን። ታሪካቸውንም
እንዘክራለን።

**3.** እኛ ኢትዮጵያውያን ብዝሃነታችንን እንንከባከባለን እናከብራለን;; ትውልዶች ባህላዊ ተቋሞቻችንን
እናከብራልን፣ እንጠብቃለን።

**4.** እኛ ኢትዮጵያውያን ከዓለም ህዝቦች ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በምንገባው ኪዳን መሰረት ለዓለም ሰላምና
ልማት በጽናት እንታገላለን።

**5.** እኛ ኢትዮጵያውያን ለተባበረችው ኢትዮጵያ ልማትና ሰላም ዘወትር ሳንታክት ለመስራት ቃል ገብተናል

**6.** እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ ለመረዳዳት ቃል ገብተናል:: ትውልድ ኣልፎ ትውልድ ሲተካ ቅርስ እየተውን
የሚቀጥለው ትውልድ የተሻለ ህይወት እንዲያይ ለማድረግ እንሰራለን። ያሉንን የተፈጥሮ ሃብቶች በትውልዶች
መካከል ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንጠቀማለን። እኛ ኢትዮጵያውያን በሃገራችን ኢትዮጵያ ሰማይ ስር ያሉ ግኡዛንና
ህያዋን ፍጥረታትን ሁሉ እንንከባከባለን እንጠብቃለን።

**7.** እኛ ኢትዮጵያውያን ለነጻነት ለፍትህ ለህግ የበላይነት ዘወትር እንተጋለን።

**8.** እኛ ኢትዮጵያውያን በህግ በምንወስነው የጊዜ ገደብ በአንድ ሰው ለአንድ ድምጽ መርህ መሰረት
ተወካዮቻችንን እየመረጥን መንግስት እየመሰረትን ስንኖር መንግስታችን ለሚያወጣቸው የሰላምና የልማት
ፖሊሲዎች በንቃት እንሳተፋለን። እኛ የህዝብ ተወካዮች የመረጠንን ህዝብ በታማኝነትና
በትጋት ለማገልገል ቃል ገብተናል።

**9.** እኛ ኢትዮጵያውያን ለተገፉ መጠጊያ እንሆናቸዋለን። እንግዶችን በፍቅርና
በደስታ እንቀበላለን። ጽንፈኝነትን ሽብርተኝነትን እንዋጋለን:: ለደካሞች ለተጨቆኑ
ሁሉ እንቆማለን።

**10.** እኛ ኢትዮጵያውያን ይህንን ቃል ኪዳናችንን ለመጠበቅ ዘወትር ዘብ እንቆማለን። አምላካችን እግዚአብሄር
ሃገራችንን ይባርክ።


### 5.1.2. አዲስ ሄራ

ሁለተኛው የዚህ ሃሳብ መሰረት ደግሞ ሄራ ነው። ሄራ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን በእንግሊዘኛው constitution የሚለውን ቃል በምልዓት የሚገልጽ ነው። ሕግ-መንግሥት የሚለው ስያሜ constitution የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በሙሉ ሃይሉ አይገልጸውምና ነው ሄራ የሚለውን የአገራችንን ቃል የተጠቀምነው። በመሆኑም ከለውጥ ባሻገር አገራችን ኢትዮጵያ ከአዲስ ኪዳኗ በሁዋላ በሰፊው የምታጸድቀው ጉዳይ ሄራችን ነው። ይህ ሰነድ የአገሪቱ የመውጫና መግቢያ ሕግ ነው። የባህልና የመንግሥት አስተዳደርን ሥልጣን የሚወስን ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ ለሕዝቦች ልእልናን የሚሰጥ፣ ቼክ እና ባላንስ ያለው፣ የፌደሬሽኑን ጉዳይ ከኪዳኑ አንጻር የሚቀርጽ፣ የመንግሥትን ሥልጣን የሚወስን፣ የኀይላትን ክፍፍል የሚያሳይ ሰነድ ማለት ነው። አገሪቱ በአጠቃላይ የምትቆመው በኪዳኑ ከዚያም በዚህ ሰነድ ላይ ይሆንና ሶስተኛው የCCU ጽንሰ ሃሳብ ይዘት ደግሞ አስተዳደራዊ ሲስተሙን በሁለት ክንፍ ማዋቀር ነው።

### 5.1.3. አዲስ የአገር አስተዳደር ቅርጽ

ኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን ካደረገች በኋላ የአገር አስተዳደሯን በሁለት ትከፍለዋለች። አንደኛው የባህል አስተዳደር ሲሆን ሁለተኛው ፖለቲካዊ ሥልጣን ያለው ሁል ጊዜም በሕዝቦች ተወካዮች የሚመሰረተው አስተዳደር ነው። ባህላዊ አስተዳደር የምንለው ቡድኖች ሁሉ የባህል ተወካዮቻቸውን አዋጥተው የሚመሰርቱት የባህል አርበኞች ቤት ይኖራል። ይህ ቤት ወደ ታች ይደራጅና የቡድኖችን ባህልና ቋንቋ ሲንከባከብ ይኖራል። በዚህ መሰረትም ተጨባጭ የሆኑና ያልሆኑ ባህሎችን ይንከባከባል፣ የሰላምና እርቅ ጉዳዮችን ይሰራል፣ ብሔራዊ ሙዚየሞችን ይንከባከባል። የኬር ቴከር ሃላፊነትን ይወስዳል። አስፈላጊ ከሆነ የአገሪቱን ብሔራዊ ምርጫ ድግስ የሚደግሰው ይሄው አስተዳደር ሊሆን ይችላል። የፍትህ አካሉ በሁለቱ አስተዳደር የጋራ ተሳትፎ የሚቆም ነጻ የሆነ ተቋም ይሆናል። በሌላ በኩል ያለው ፖለቲካዊ መንግሥት ደግሞ የኢኮኖሚ፣ የትምህርት አጠቃላይ የአገሪቱን የውጭ ግንኙነትን ንግድና ልማት በሚመለከት ይመራል። የሁለቱም አስተዳደር ስራዎችና ሃላፊነት በሄራው ላይ በግልጽ ስለሚቀመጥ ችግሮች አይኖሩም። ይህ ሲስተም ለአገሪቱ ልማትና ኢኮኖሚም ትልቅ አስተዋጾ ይኖረዋል። የባህል አስተዳደሩ የራሱ ፌደሬሽን የሚኖረው ሲሆን ፌደሬሽኑ በመሬት ላይ የሚነበብ አይሆንም። የባህላዊ ቡድኖች ባሉበት ሁሉ የባህል ፌደሬሽኑ ስራዎቹን ይሰራል። በአንጻሩ የፖለቲካ ሥልጣን ያለው መንግሥት ግን መሬት ላይ የሚነበብ ፌደሬሽን ይሰራል። ይህ የፌደራል አወቃቀር ደግሞ ከሕዝቦች ኪዳን አንጻር ይሆናል። ቡድኖች መሬታቸውን መስዋእት ስለሚያደርጉ ፌደራሊዝሙ ለአስተዳደር አመቺነትን መሰረት ያደረገ ይሆናል ማለት ነው። እንግዲህ የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካ መሰረት በአዲስ ኪዳን ላይ ስናቆም ከዚህ በሁዋላ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችና ህጎች ሁሉ ከፍ ብሎ ከተቀመጠው የቡድኖች ኪዳን የሚቀዳ ይሆናል። አገሪቱ ግልጽ በሆነና በቆረጠ ኪዳን ላይ ስትቆም ከዚያ የሚቀዱ ህጎች ሁሉ ለግጭት መንስዔ አይሆኑም። ከሁሉ በላይ በአገሪቱ ሰላምና

ልማት ይሳለጣል። አጠቃላይ ከላይ ያነሳናቸው የ CCU መሰረቶች በስእላዊ መንገድ እንደሚከተለው ሊገለጹ ይችላሉ።



ሌላው ስለ ሶሺዮ ፖለቲካችን ጉዳይ ስናነሳ የዘውጎች ዋና መገለጫ የሆነው የቋንቋ አያያዛችንና አጠቃቀማችን ጉዳይ በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት እንዴት ይሆናል? የሚለው ጉዳይ ይታወሳል። በ CCU ንድፈ ሃሳብ መሰረት ኢትዮጵያ ከኪዳኗ የሚቀዳ አዲስ የቋንቋ ማኔጅመንትና አጠቃቀም ተግባራዊ ታደርጋለች ይህ አጠቃቀምና ማኔጅመንት የሚከተለውን ይመስላል።

5.1.4. አዲስ የቋንቋ ማኔጅመንትና አጠቃቀም ዘዴ

በቀጥታ ወደ CCU የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴ ከማምራታችን በፊት በዚህ በቋንቋ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አንዳንድ ምሁራን የተለየ አሳብን እያራመዱ ይገኛሉ። እነዚህ ጥቂት ምሁራን የሚሉት ኢትዮጵያ ከሰማኒያ በላይ ቋንቋዎችን ይዛ መቀጠል የለባትም ነው። እንዴውም ቶሎ ቶሎ ብላ እያረገፈች ሄዳ ሁለትና ሶስት ቋንቋዎች ይበቃሉ ይላሉ። ቋንቋን ከመሳሪያነቱ በላይ ዋጋ አይሰጡትም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሁለት ቋንቋዎች ይዘው ሌላውን ማርገፋቸው የሚጠቅመው ለተግባቦት፣ ከዚያም ደግሞ የቋንቋ ልዩነትን ተገን እያደረገ የሚመጣን እምቅ ግጭቶች ይቀንሳል የሚል ስሌትም ያላቸው ይመስላል። ብቻ የቋንቋን ብዛት እንደ ሀብት እንደ በጎ ነገር አያዮትም። የዚህ አሳብ ችግር የኢትዮጵያን ፍላጎት አለመረዳት ነው። ምን አልባት አሳቡ እንደተባለውም ጥሩ ይሆን ይሆናል። ነገር ግን የመፍትሄ አሳቦች ሁሉ መፍትሄ ይሆናሉ ማለት ግን አይደለም። ፍላጎት መታየት አለበት። የኢትዮጵያ ቡድኖች ቋንቋቸው እንዲጠፋ ስምምነት ውስጥ አይገቡም። ቋንቋቸውን ለኢትዮጵያ ሰውተው ግን ተጠብቆ እንዲኖር ነው የሚሹት። እንዴውም ይልቁን በቋንቋቸው በምልአት እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ሲስተም ነው የሚሹት። እነዚህ ቋንቋን ቀንሰን እንቀጥል የሚሉ ወገኖች የሜልቲንግ ፖት ትምህርት ተከታይ መሆናቸው ነው። ብዙህነትን ያለ መቀበል አዝማሚያ ይዟቸው ነው። ይህ ግን ችግሮች አሉት። በመሰረቱ ልማት የሚፈጥነውም ቡድኖች በቋንቋቸው ሲጠቀሙ ነው። ቋንቋ ደግሞ አንድ የቡድኖች ትልቅ የፈጠራ ውጤት ነው። ከሁሉ በላይ የዘውጎች ዋና መገለጫ ነው።

ሌላ በኩል የወቅቱን የመንግሥትን የቋንቋ አያያዝ በተመለከተ በተለይ ዜጎችን ወደ ጎን በሚያስተሳስረው የማህበር ቋንቋ ላይ አይጨነቅም። ይሄ ደግሞ አገራዊ ትስስር እንዳይጠነክር የሚያደርግ ግዙፍ ችግር ነው።

በCCU ማእቀፍ ውስጥ ስንገባና ቡድኖች አዲስ ኪዳን ሲያደርጉ መጀመሪያ ላይ በገባነው ኪዳን መሰረት ቋንቋዎች ሁሉ የኢትዮጵያዊነት ናቸው። አንድ ቡድን የኔ የብቻየ የሚለው ሀብት የለም ማለት ነው። ባህል፣ ታሪክ፣ መልክዓ ምድር፣ ቋንቋ ሁሉ ሀብትነታቸው የኢትዮጵያ ሆኖ ግን ቡድኖች ደግሞ የማሳደግ ሃላፊነት አለባቸው። ከዚህም በላይ ደግሞ የቡድኖች ኪዳን ቀጥታና ተዋረዳዊ ግንኙነትን የሚያጠናክር መሳሪያ ቋንቋ ነው።

በአጠቃላይ ግን ኢትዮጵያ ኦፊሺያል ቋንቋ እዴት ልትመርጥ ትችላለች? ብሔራዊ ቋንቋስ ሊኖራት አይገባም ወይ? የሚል ጥያቄ ስላለ በሚከተለው ዘዴ ብንጠቀም የተሻለ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ከአለም አሰራር ትንሽ እንማር። አገሮች ሁሉ የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ፖሊሲዎች አሏቸው። በዚህ ቋንቋ አጠቃቀም ዙሪያ ውይይት ሲነሳ በተደጋጋሚ የሚነሱ ስያሜዎች አሉና በመጀመሪያ ስለነዚህ ስያሜዎች መግለጫዎችን እንመልከት ።

ብሔራዊ ቋንቋ

ብሔራዊ ቋንቋ ሲባል አዘውትሮ የሚሰጠው ትርጉም በአንድ የአገር ግዛት ውስጥ መግባቢያ ሆኖ ከማገልገሉ ባሻገር የብሔራዊ ማንነት መገለጫ ተደርጎም ይታያል። ለምሳሌ ያህል ስዊዘርላንድን ብንወስድ አራት ቋንቋዎቿ ማለትም ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛና ሮማንኛ ብሔራዊ ቋንቋ ናቸው። በአንጻሩ ብዙ አገሮች በዓለም ላይ ብሔራዊ ቋንቋ የላቸውም። ይህ ማለት ብሔራዊ ማንነታቸውን ከቋንቋ ጋር አያጣብቁም ማለት ነው። ቋንቋን እንደ መግባቢያ መሳሪያ ከማየት ውጭ የብሔራዊ ማንነት መገለጫ አድርገው አያራግቡትም። በሕገ-መንግሥቶቻቸውም ላይ ብሔራዊ ቋንቋ የሚል አያስገቡም። አሜሪካንን ብናይ ብሔራዊ ቋንቋ የምትለው የለም። እንግሊዝ ራሷ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈጣሪ ብትሆንም እንግሊዘኛ ብሔራዊ ቋንቋዩ ነው ብላ አላወጀችም። በአጠቃላይ ያለው ሰፊ ብያኔ ግን ብሔራዊ ቋንቋ የሚባለው በአንድ አገር ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረው ተደርጎ ይወሰዳል። ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ ወጥ የሆነ ዩኒቨርሳል ብያኔ አናገኝም።

ኦፊሺያል ቋንቋ

በዓለም ላይ ብዙዎቹ አገራት አንድ ኦፊሺያል ቋንቋ አላቸው። ይህ ቋንቋ የመንግሥት ቋንቋ ሲሆን በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥበት ቋንቋ ነው። በዓለም ላይ ወደ ሃምሳ አራት አገሮች ኦፊሺያል ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ሆኗል።

የስራ ቋንቋ

በአንዳንድ አገሮች ኦፊሺያል ቋንቋ ብሔራዊ ቋንቋና የስራ ቋንቋ የተደባለቀ ትርጉም ነው ያላቸው። በተባበሩት ሕዝቦች ድርጅት ውስጥ ግን እነዚህ ሁለት ስያሜዎች የተለያየ ትርጉም አላቸው። በUN ውስጥ ኦፊሺያል ቋንቋ የሚል ደረጃ ያገኙት ቋንቋዎች ስድስት ሲሆኑ እነዚህም ቻይንኛ፣ አረብኛ፣ ሩሲያኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽና ፈረንሳይኛ ናቸው። እነዚህ ቋንቋዎች ኦፊሺያል ናቸው ማለት በዚህ

ድርጅት ውስጥ ስብሰባዎች ሲኖሩ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ናቸው ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪም የድርጅቱ ዶክመንቶች በነዚህ ቋንቋዎች እየተተረጎሙ የሚሰራጭበት አሰራር ነው ያለው። እንግሊዘኛና ፈረንሳይኛ ደግሞ የስራ ቋንቋ ሆነው በሰፊው መስሪያ ቤቱ ይጠቀምባቸዋል።

ዲፋክቶ ቋንቋ

ህጋዊ ባይሆንም በአገሪቱ ቋንቋው እየተሰራበት ያለ ሲሆን ዲፋክቶ ይባላል።

የማህበር ቋንቋ

ህንድ በነገራችን ላይ የማህበር ቋንቋ የሚባል ያላት ሲሆን ይህ የማህበር ቋንቋዋ ሂንዱ ነው። አንዳንድ አገሮች ብሔራዊ ቋንቋ እንደሚሉት አይነት ነው። ህንድ የራሷ የሆነ ስያሜ ፈጥራ ነው ብሔራዊ ቋንቋ የሚባለውን የህብረት ቋንቋ ያለችው። መስፈርቱ አብዛኛው ሰው ስለሚናገረው ነው። በአጠቃላይ አንዳንድ አገሮች ብሔራዊ ቋንቋ የሚባል ያላቸው ሲሆን ሌሎቹ ግን ኦፊሺያል ቋንቋ ነው ያላቸው።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ አማርኛ የፌደራል ቋንቋ ሲሆን ኦፊሺያል ቋንቋም ሆነ ብሔራዊቋንቋ የሚባል ወጥ የሆነ የለንም። ክልሎች በራሳቸው ቋንቋ የሚጠቀሙ ሲሆን አንዳንድ ክልሎች አማርኛን መርጠው እንደሚጠቀሙ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ውስጥ የብሔራዊ ቋንቋ ጉዳይና የኦፊሺያል ቋንቋ ጉዳይ ሲነሳ ኦሮምኛ ብዙ ይሰማበታል። ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኦሮምኛ ተናጋሪ ሆኖ ሳለ ለምን ኦፊሺያል ቋንቋ ወይም የፌደራል ቋንቋ አይሆንም? የሚል ክስ ይሰማል። በርግጥ ጥያቄው ፍትሃዊ ነው። አሁን ስናስበው ግን ኦሮምኛ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የቋንቋ አጠቃቀማችንን ብናሻሽል አይሻልም ወይ? ሌሎቹስ ብዙ ሕዝብ የማይናገራቸው ቋንቋዎች በተሻለ ደረጃ እንዴት መጠቀም እንችላለን? በሚለው ላይ መወያየት ጥሩ ነው። የቋንቋ ጉዳይ ሲነሳ የአንድ የሁለት ቡድንን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁሉን ቡድን ቋንቋዎች ከፍ የሚያደርግ አሰራር በማምጣት የሁሉን ጥያቄ መፍታት መልካም ነው።

ኢትዮጵያ የቋንቋ ሃብቶቹዋን በተሻለና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም ትችላለች። ይህ ዘዴ የቋንቋ ሃብቶቿን ለመጠበቅና ጎናዊ የቡድኖችን ግንኙነት ለማዳበር ይረዳታል። በመሆኑም በስባአ ኪዳን መሰረት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ማንነቷን ከቋንቋዎቿ ጋር ልታገናኝ ትችላለች። እንዴውም ጥሩ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሃብቶች ሁሉ በላይኛው ኪዳን ጊዜ ለኢትዮጵያዊነት ስለተሰው የአንድነት መገለጫ ይሆናሉና የሁሉም ቡድኖች ቋንቋዎች በሕገ-መንግሥት ተመዝግበው የብሔራዊ ቋንቋነት ስያሜ ሊሸለሙ ይገባል። የብሔራዊ ቋንቋነት ስያሜ ጉዳይ የረቀቀ የብሔራዊ ማንነት መገለጫ በመሆኑ ይህን የማንነት ምልክትነት ለምን ለሁሉም ቋንቋዎች አንሰጥም? ይህ ሲምቦሊክ የሆነ አንድነትንና ብዙነትን የሚያሳይ በመሆኑ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋዎቿ ብዙ ቢሆኑ መልካም ነው። ቋንቋዎች ሁሉ የኢትዮጵያ በመሆናቸውና

ለዚህም ስለተስማማን ሁሉም ቋንቋዎች የብሔራዊነት ቋንቋ ደረጃ ሊጎናጸፉ ይችላሉ። በኢትዮጵያ ሁኔታም ብሔራዊ ቋንቋ የሚለው አሳብ በዚህ አቅጣጫ ብያኔ ቢሰጠው ጥሩ ነው። ኢትዮጵያ ባለ ሰማኒያ በላይ ብሔራዊ ቋንቋዎች ያሏት አገር ትባላለች። ይህም ያስከብረናል። የብሔራዊ ቋንቋ ጉዳይና የኦፊሺያል ቋንቋ ጥያቄም አርኪ መልስ ያገኛል። ቋንቋው ከመሳሪያነት አልፎ ፖለቲካዊ አንድምታ ይዞ ለመጣው የብሔራዊ ማንነት ጉዳይም መልስ ይሰጣል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከድህነት ለመላቀቅ ኮሙኒኬሽናችንን ለማስተካከል ቋንቋዎቻችንን በሚገባ መጠቀም ያሻልና ኢትዮጵያ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የህብረት ቋንቋ ቢኖራት መልካም ነው። ይህ ቋንቋ ደግሞ አማርኛ ቢሆን ጥሩ ነው። የህብረት ቋንቋ አማርኛ መሆን ያለበት በጽሁፍ የዳበረ ብዙ ሰው የሚናገረው በመሆኑ ነው። በአንጻሩ ኦሮምኛም አንዱ የህብረት ቋንቋ ሆኖ ከአማርኛ ጎን ለጎን የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንችላለን። ከዚህ በፊት ሌሎች ቋንቋዎች ጨምሮ ለምን ኦፊሺያል አናደርግም ብየ ብዙ አስቤ አውቃለሁ ይሁን እንጂ ሁሉንም ኦፊሺያል ማድረግ እስከቻልን ድረስ፣ ሁሉንም ብሔራዊ ማድረግ እስከቻልን ድረስ የብሔራዊ ቋንቋነት ስታተስ ጉዳይ አሳሳቢ ጥያቄ አይሆንም።

የፌደራሉ ወይም የህብረቱ ቋንቋ በአራቱም ማእዘናት የሚገኙ የመንግሥት መስሪያቤቶች አገልግሎት የሚሰጡበት ቋንቋ ይሆናል። የህብረት ቋንቋው ለብቻው እንደ ብሔራዊ ማንነት መገለጫ ግን አይታይም። ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር አብሮ ብሔራዊ ቋንቋ የሚለውን ረቂቅ የፖለቲካና ማኅበራዊ ማንነት መገለጫነት ቀድሞ ያገኘ ቢሆንም አሁን በዚህ በማህበር ቋንቋነቱ ግን እንደ መሳሪያ የጋራ መግባቢያ ይታያል።


ይህ በእንዲህ እንዳለ በማዘጋጃ ቤት ወይም በወረዳዎች አካባቢ አንድ ተጨማሪ ኦፊሺያል ቋንቋ ይኖራል። ይህ ማለት እያንዳንዱ ወረዳ ወይም ማዘጋጃ ቤት በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋና የህብረቱን ቋንቋ በአንድነት የኦፊሺያል ቋንቋ ያደርጋል ማለት ነው። በወረዳና ቀበሌ ደረጃ ዜጎች ከሁለት አንዱ ቋንቋ በመረጡት አገልግሎት ያገኛሉ ማለት ነው። በዚህ መሰረት ሁሉም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኦፊሺያል ቋንቋና ብሔራዊ ቋንቋ ይሆናሉ ማለት ነው። ይህ አሰራር የሚኖረው ጠቀሜታ የቋንቋ አሰራራችንን ማሻሻል ብቻ ሳይሆን ቡድኖችን በብሔራዊና በአካባቢ ደረጃ ከፍ የሚያደርግ፣ የእኩልነት ተምሳሊት ይሆናል። ቡድኖች ይኮራሉ፣ አገራቸውን ይወዳሉ። መዋጥ አይሰማቸውም።

ይህ አሰራር ቋንቋዎችን ሁሉ ወደ ቢሮዎች፣ ወደ ሲስተም ስለሚወስዳቸው ከቴክኖሎጂና ከሰዎች ንቃተ ህሊና ጋር እያደጉ እንዲሄዱ ያደርጋል። የመግለጽ ችሎታቸው ይጨምራል። የቃላት ምህዳራቸው ይሰፋል። ሌላው ጉዳይ በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አካባቢ ልጆች ትምህርታቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ማድረጉ ለቋንቋው እድገትና ለተማሪዎቹ ትልቅ ሚና ያለው ሲሆን እዚሁ ጋር መረሳት የሌለበት ጉዳይ የማህበሩን ቋንቋም በማካተት ልጆቹ ባለ ሁለት ቋንቋ ባለቤት (bilingual) ሆነው እንዲያድጉ መደረግ አለበት። በሁለቱም ቋንቋዎች የመጻፍ፣ የማንበብ፣ የመናገር፣የማዳመጥ ክህሎቶቻቸው ከፍተኛ እንዲሆን መስራት አስፈላጊያችን ነው። በሌላ በኩል ሁሉንም ያገራችንን ቋንቋዎች ተረባርቦ የጽሁፍ ቋንቋ እንዲኖራቸው ፊደል እንዲቀረጽላቸው ያስፈልጋል። እነዚህ የጽሁፍ ቋንቋ የሌላቸው ቋንቋዎች ማኅበረሰብ አባላት የቡድኑን ታሪክ በአብዛኛው ያቆዩት በስነ-ቃል አማካኝነት እየተቀባበሉ ነው። አንዱ ትውልድ ለአንዱ በቃል እያቀበለው የሚቆይ ታሪክ ደግሞ በቅብብሎሹ መሃል መዛባቶች ሊገጥሙት ስለሚችሉ እነዚህን ሰነ-ቃሎች ወደ ጽሁፍ በመቀየር ታሪክን የማቆየት ስራ ለመስራትም ይረዳል።

በሌላ በኩል ስለቋንቋ ስናወራ ኢትዮጵያ ትልቅ ትኩረት ልትሰጥበት የሚገባው ጉዳይ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ጉዳይ ነው። ዓለም በጣም እየተቀራረበች ከመሄዷም በላይ አብዛኛው መረጃ በዓለም መረብ ላይ ያለው በእንግሊዘኛ በመሆኑ ትውልዱ ከአፍ መፍቻው ቋንቋና ከማህበሩ ቋንቋ በተጨማሪ እንግሊዘኛን ጠንክሮ መማር ያስፈልገዋል። አገሪቱ ያላትን ራእይ ለመፈጸም፣ በአለም ኮሙኒኬሽን ጉዳይ ብቁ እንድትሆን ዜጎችን እንግሊዘኛ ማስተማር ተገቢ ነው።

ዛሬ በዓለም ላይ የእንግሊዘኛ ተናጋሪው ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ የመጣ ሲሆን ኢትዮጵያም በዚህ ርምጃ ውስጥ ፈጣን መሆን አለባት። የእንግሊዘኛ አካዳሚዎችን መክፈት፣ የእንግሊዘኛ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን፣ ዘዴዎችንና ስርዓተ ትምህርቱን ማስተካከል፣ መምህራንን ብቁ ማድረግ፣ የፒስ ኮር አገልግሎቶችን ማስፋትና ማጠናከር በጣም ወሳኝ ነው። ብዙ ጊዜ የእንግሊዘኛ ትምህርት ችግር ሆኖ የሚታየው ራሳቸው አስተማሪዎቹ እንግሊዘኛ በሚገባ መናገር ሳይችሉ ማስተማራቸው ነው። ስለዚህ ኮሌጆች በተለይም የእንግሊዘኛ ቋንቋ አስተማሪዎችን የሚያመርቱቱ በጣም ሊጠነክሩ ይገባል። ለመነሻ ኔቲቭ መምህራንን ጨምረው እንግሊዘኛ ተናጋሪ አስተማሪዎችን ማፍራት ያስፈልጋል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የብሔራዊ ቋንቋ፣ የኦፊሺያል ቋንቋና የህብረት ቋንቋን በሚመለከት የራሷ የጠራ ትርጓሜና አጠቃቀም ኖሯት የቋንቋ ሃብቶቿን ፍትሃዊ በሆነና ለአገልግሎት በሚመች መንገድ አደራጅታ ልትጠቀም ትችላለች። ይህ አሰራር ትንሽ የኢኮኖሚ ዋጋን ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ነገር ግን አንድ ማየት ያለብን ነገር በትምህርት አሰጣቱ ሂዳት ቡድኖች ወደ ማህበሩ ቋንቋ ሊያዘነብሉ ይችላሉ። ከዚህ በላይ ግን ዜጎች ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ እየሆኑ ሲመጡ ዋጋው እየቀነሰ ይመጣል። ከሁሉ በላይ ግን የቡድኖች መብት ነውና ከሚኖረው ጥቂት የኢኮኖሚ ውድነት በላይ የዘውጎች ህልውና እንዲሁም ዜጎች በቋንቋቸው ፍትህ የማግኘታቸው ነገር ትልቅ ዋጋ አለውና አገራችን ይህንን የቋንቋ አሰራር መጠቀም አለባት። ቡድኖች በቋንቋቸው መገልገል ካለመቻላቸው የሚመጣው አንዱ ኪሳራ የኢኮኖሚ ችግር ነው። አምራች ዜጋ ለማፍራት ቋንቋ ወሳኝ ነው። ስለሆነም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ስናየው የቋንቋ አጠቃቀማችን በዚህ መንገድ ሲሻሻል አገራችን የተሻለ መረጋጋትን ስለምታመጣ በኢኮኖሚያችን ላይ እንዴውም መልካም ተጽእኖ ያመጣል።

የቋንቋ አጠቃቀም ማሳያ



ክልል ወይም ስቴቶችወይም

5.1.2. የአዲሱ ቃል ኪዳን ዋስትናዎችና ተግዳሮቶች

የዋስትና ጥያቄ

በመጀመሪያ ወደ ኪዳኑ ለመግባት ዋስትናዎቻችን ምን ምን ናቸው? በሚለው ላይ እንወያይ። ስለዚህ ስለ አዲሱ ኪዳን ወይም በስምምነት ላይ ስለተመሰረተ ባህላዊ አንድነት ጉዳይ ስናወራ የሚነሱ ጥያቄዎች ይኖራሉ። አንደኛው ጉዳይ የዋስትና ጥያቄ ነው። ቡድኖች ወደዚህ ከፍተኛ ኪዳን ይገቡ ዘንድ የሚነሳው የዋስትና ጥያቄ የሚመነጨው መጀመሪያ ላይ ያነሳነው ጉዳይ ተመልሶ እንዳይመጣ ነው። ይህም የቡድኖች ማንነት እንዳይጨፈለቅና ሁለተኛ ደግሞ በቡድኖች እውቅና ስም ብሔራዊ ማንነታቸው እንዳይጨፈለቅ ነው። በመሆኑም ቡድኖች ኪዳን ሲገቡ አንዱ ትልቁ ዋስትናቸው የሚፈጠረው ሲስተም ራሱ ነው። ሲስተሙ ባህላዊ አስተዳደርንና ፖለቲካዊ አስተዳደርን መለየቱ ሁለቱንም ማንነቶች እየተንከባከቡ ለማኖር ስለሚያስችል ዋስትና ይሆናል። የቡድኖች ሁሉ ቋንቋ ኦፊሺያልና ብሔራዊ መሆኑ አንዱ ዋስትና ነው። የቋንቋው ሲስተም ለቡድኖች መኖር ዋስትና ነው። ቡድኖች ያላቸውን ሁሉ አዋጥተው አገራቸውን ለመገንባት ዋስትና ሲሹ ይህ ሲስተም ዋስትና ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ኪዳኑ ራሱ የቡድኖች ዋስትና ነው። የማይናወጥ ኪዳን ስለሆነ። ሄራው ማለትም መሰረታዊ ህጉ የመሻሻል እድል አለው። ኪዳኑ ግን ሃውልት ተቀርጾለት የሚቀመጥ ጉዳይ በመሆኑ ቡድኖች ይህንን ኪዳን እንደ ብሔራዊ ማንነት መገለጫና ዋስትና ያዩታል። በየአመቱም የኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን ቀን እየተባለ ይከበራል። ስለዚህ በአጠቃላይ ዋስትናችን የቋንቋ አጠቃቀማችን፣ አዲሱ የአገር አስተዳደር መዋቅርና ራሱ የምንገባው ኪዳን ይሆናል ማለት ነው።

## ያለፈ የታሪክ ትዝታዎች ጉዳይ (Past bad memories)

በዚህ በCCU አመለካከት ወደ አዲስ ኪዳን ለመግባት ያለፉ የታሪክ ትውስታዎቻችንን ሁሉ በጋራ መግባባት (mutual understanding) ነው የምንፈታው። በመሆኑም ወደ አዲስ ኪዳን ለመግባትና ቡድኖች ያላቸውን ሁሉ መስዋእት ለማድረግ ባለፈ ታሪክ ጠባሳዎቻቸው ላይ ከፍ ያለ መረዳት ውስጥ እንዲገቡ ይመክራል። አጠቃላይ የአለምን ተመክሮ ማየት፣ ኢትዮጵያን ከዓለም ነጥሎ አለማየት፣ እስካሁን ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን ለመፍታት መስማማት ወሳኝ

ነው። ከሁሉ በላይ በታሪክ አጻጻፍ በኩል አገራችን ውዝግብ ውስጥ መግባቷንና ታሪክን ለፓለቲካ ፍጆታ ሲባል የተሰሩ ስራዎችን ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በአጠቃላይ ስለ አለፈ ታሪክ ስናወራ የዓለምን ታሪክ እናያለን። ለምሳሌ ምዕራብ ጀርመንና ምሥራቅ ጀርመን ልዩነት ሲያምራቸው ታሪክን ለፖለቲካ ፍጆታ ማዋል ጀምረው ነበር። አንዱ የጀርመኖችን ፖለቲካ ያራራቀውም ይሄው ነበር።

በተለይ በናዚ ወቅት የተፈጸመውን የሆልኮስት ዘር ማጥፋት ወንጀል በተመለከተ ታሪኩን ሁለቱ ጀርመኖች በተለያየ መረዳት መተርጎም ከመጀመራቸው አልፎ በርሊንና ቦን ሁለት ሙዚየሞች ቆመው የተለያየ ነገር ማስተማር ጀምረው ነበር። ያለፈውን ታሪክ ለማስታወስ የፈለጉበት ሞቲቭና ታሪኩን ወደ ትውልድ ለማሳለፍ የሞከሩበት ዘዴ ይለያይ ነበር።

ባለፈው ጊዜ ዶክተር መረራ ጉዲና ጥሩ ነገር ተናግረዋል። ታሪክን ለፖለቲካ ፍጆታ አናውለው ብለዋል። በርግጥ ጀርመን ከታየው በላይ የኢትዮጵያን አጠቃላይ የታሪክ መሰረት የሚያምስ ሁኔታ ተፈጥሩዋል። ይህ የሆነው የማንነት ፖለቲካን ለማራገብ ታሪክ መሳሪያ ሆኖ በመቅረቡ ነው። በርግጥ አንድ አገር ሲቆም ያለፈን ትውስታ ወዴትም አንጥለውም። ነገር ግን ትውስታችንን የምናይበትን መንገድ ማስተካከል አስፈላጊ ነው።

ስባአ አመለካከት በኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥት በመመስረቱ ሂደትና ከተመሰረተ በሁዋላ የተፈጸሙ በጎም ሆኑ መጥፎ ታሪኮች ሁሉ የኢትዮጵያ ትውስታዎች ናቸው። ኢትዮጵያ እንደ አገር ትውስ የሚላት ታሪክ ነው። በጎ በጎውን መርጠን የመታሰቢያ ቀን አቁመን የጋራ ታሪካችን እያልን እየሞቅን መጥፎውን ነቅሰን አውጥተን ለአንድ ቡድን አናላክክም። ሁሉም የኢትዮጵያ ታሪክ ነው። የሚያሳዝነው ያሳዝነናል፣ የሚያስደስተው ያስደስተናል። ባለፉት ጊዚያት በግልም ይሁን ቡድንን እየለየ የተፈጸመ በደል ሁሉ የኢትዮጵያ ትውስታ እንጂ ያ በደል የተፈጸመበት ቡደን ቋንቋ ተናጋሪና አባል ብቻ አይደለም። በዳይና ተበዳይ በሕይወት የሉም። ይሁንና እኛ ዛሬ ላይ ያለን ዜጎች ህማምንም ደስታንም እንካፈላለን።

ሌላው ታሪክን በሚመለከት የዓለም ሕዝብ ኢትዮጵያን እንዴት እንደሚያያትም መታወቅ አለበት። ከአጠቃላዩ የዓለም ሕዝብ ወደ 54.9 በመቶ የሚሆነው የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖተኛ ሲሆን ኢትዮጵያን የሚያያት በረጅም ጊዜ ታሪኳ ነው። ክርስቲያኑ በሃዋርያት ስራ ላይ የተገለጸውን ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ዋቢ በማድረግ ክርስትናን የተቀበለች ከዓለም ቀደምት አገር ናት ብሎ ያከብራታል። በብሉይም ስሙዋ የተጠቀሰ ተስፋ ያላት አገር አድርጎ ስለሚያምን ተስፋዋን ይጠብቃል። ። ሙስሊሙ ህበረተሰብ ደግሞ ለመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች መጠጊያ ለመሆን የበቃች አገር ብለው ስለሚያምኑ እንደዚሁ በሙስሊሙ ሕዝብም ዘንድ ታዋቂ ናት። ይሄ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ታሪክ ሲሆን ከግማሽ በላይ የሚሆነው የዓለም ሕዝብ እንዲህ እንደሚያያት መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ሌላው ያሉን ቁሳዊ ባህሎች እንደ ላሊበላ፣ አክሱም በደቡብና ኦሮሚያ የሚገኙ ሃውልቶች ሁሉ የኢትዮጵያን እድሜ ይናገራሉ። እነዚህ ታሪኮች ሁሉ

የጥንታዊቱን ኢትዮጵያን ትውስታ እየሰጡን እንኖራለን። ኢትዮጵያ በረጅም ጊዜ ታሪኳ ስትሰፋና ስትጠብ ብትቆይም ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያዊነቷ ግን ብዙህ ሺህ ዘመን ታሪክ ያላት አገር ናት። በአጠቃላይ በዚህ ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ያለፈውን ታሪክ እንደ ወል ታሪክ የሚያይ ይሆንና የሚከተሉትን ጉዳዮች በጥብቅ ይመረምራል። ይህም ታሪኩ ታሪክ ሆኖ መቅረት ብቻ ሳይሆን አሁን ድረስ ይጎተታል ወይ? የሚለውን ያያል። በተለይ መጥፎ የምንለው ታሪክ አሁንም ካለ ይህን ታሪካዊ ዳራ ያለውን ችግር በሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ እና በተለያዩ ማስተካከያ ርምጃዎች ይፈታል።

በአጠቃላይ ያለፈውን ታሪክ የምናስታውሰው የወል ታሪክ አድርገን ሲሆን ይህንን የወል ታሪካችንን እንደ የወልነቱ ስናየው ትውስታችንን በጥሩ ሚዛን ላይ ያስቀምጠዋል። ከዛሬ መቶ አመት በፊት የነበረውን ታሪካችንን ስንተነትን ኢትዮጵያን ለብቻዋ ንጥል አድርገን በዓለም ሳለች ከዓለም አውጥተናት ሳይሆን ከአለም የሰው ልጆች ታሪክ ጋር እያገናዘብን መፍረድ አለብን። ሌላው አሁን ያለንበት ከባቢስ ምን ይመስላል? በምን አይነት የፖለቲካና ማኅበራዊ ከባቢ ውስጥ ሆነን ነው ታሪክን የምንተነትነው? ብለንም መጠየቅ አንዱ ለፍርድ በተሻለ የሞራል ደረጃ ላይ የሚያስቀምጠን ነው። ሌላው ማየት ያለብን የትውስታችን ፍላጎት ምንድነው? በታሪክ መረዳታችን ምን ልናደርግበት ነው? ብለን መጠየቅም መልካም ነው። በርግጥ ያለፉ ታሪኮችን አንስተን በቀልን ልናቅድ ነው? ወይስ የተሻለ አሰራር ለማምጣት መልካም እልህ ውስጥ ሊከተን ነው? ብለን መጠየቅ አለብን የሚል ምክር ይህ የባህላዊ ውህደት አሳብ አዝሎአል። የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በርግጥ አገሪቱን ወደ ተሻለ ልማትና ሰላም ለመምራት ከፈለጉ መጀመሪያ ማስተካከል ያለባቸው ያለፈ ትውስታን ነው። አሁን የምንመራውና የፖለቲካ ርእዮቶቻችን የቆሙት በባለፈ መጥፎ ትውስታዎች ላይ ነው። ይሄ ደግሞ ሚዛናዊ አይደለም። የብሔር ፌደራሊዝም ያለፈ ትውስታን ለመበቀል የመጣ ፖለቲካ ነው እንጂ ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል አይደለም። ያለፈ መጥፎ ትውስታዎችን የምናይበትና የምንገመግምበት አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን መለወጥ ያለበት የወደፊቱን አቅጣጫ ለመተለም ያለፈን መጥፎ ትውስታ ኀይል አድርጎ መታጠቁንም ነው። ያለፈው ትውስታ በጎውን የጋራ እንደምንለው ሁሉ ክፉቶችንም የጋራ አድርገን የተሻለ ሥርዓት ለመዘርጋት መነሳት ይኖርብናል። ብዙው ጊዜ ያለፈው አይደለም። የሚመጣው ጊዜ ነው ብዙው ጊዜ። ስለዚህ ስባአ ትውስታዎቻችንን ሚዛናዊ እንድናደርግ ነው የሚመከረው። ፖላቲካችንን በመጥፎ ትውስታዎች ላይ ማቆም ጥሩ አይደለም። ከሁሉም በላይ መጥፎ ትውስታዎችን ይዘን ወደ ብሔር ፖለቲካ ስንገባ ደግሞ እነዚህን መጥፎ ትውስታዎች ከአንድ ባህላዊ ቡድን ወይም ብሔር ጋር አጣብቀን እንድናይ ስለሚያደርግ ሊወገዝ ይገባዋል። ፖለቲካ በአብዛኛው በአገር ጥሩ ትዝታዎች ላይ ነው ሊቆም የሚገባው። አንዱ ለሶሻሊዝም ሥርዓት መውደቅ ምክንያት የሚመስልው በበቀልና በመጥፎ ትዝታዎች ላይ በመመስረቱ ነው። ዓለም ሁሉ በታሪኩ በውጣ ውረድ ውስጥ አልፏል። አንዱ አንዱን በድሏል። ግን የሆነ ዘመን ላይ አስተዋይ መሪዎች እግዚአብሔር የሰጣቸው ሕዝቦች ያለፈ መጥፎ ትውስታን ለበጎ ይለውጣሉ። ይቅርታንና መረዳዳትን ያስቀድሙና የነፍስ ጽዳትን ያመጣሉ። እንዲህ ያደረጉ መሪዎች አገራት በፍጥነት ወደ ዴሞክራሲ አድገው አገራቸውን ሲለውጡ ይታያል። በአንጻሩ በአለፈው መጥፎ ትውስታዎች ዙሪያ ሲዞሩ የሚኖሩ መሪዎችና ፖለቲከኞች በበዙበት አገር ደግሞ እንዲሁ ሲነታረኩ ይኖራሉ። በመሆኑም እኛ

ኢትዮጵያውያን ለመልካም ትውስታዎች መጠበቂያ እየሰራንላቸው መጥፎዎቹን ደግሞ እንዳይደገሙ እየጣርን ሲንከባለሉ ለመጡት ደግሞ መፍትሄ እየሰጠን ካልሄድን ከገባንበት ችግር መቼም አንወጣም።

ብሔራዊ እርቅ በኢትዮጵያ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ብሔራዊ እርቅን የምንረዳው ግን በሌሎች አገር ሲደረግ የሰማነውን በቀጥታ ወስደን አይመስለኝም። በኢትዮጵያ ሁኔታ ብሔራዊ እርቅ ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ መወያየት አለብን ይመስለኛል። በብሔራዊ እርቅ ጊዜ አንዱ የማስታረቂያ ጥበብ ከፍ ሲል ያልነው ታሪክን ደስታንና ህማምን የጋራ አድርጎ ማየት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የዓለምንም ታሪክ መዳሰሱ መልካም ነው። ይህን በተመለከተ ከዚህ በፊት የጻፍኳትን ጦማር ትንሽ ከርከሜ እንደሚከተለው ላቅርብ።

ብሔራዊ እርቅ በአለማችን ታሪክ ውስጥ በብዙ አገሮች የተፈጸመ ሲሆን የእርቁ ትርጓሜና አፈጻጸም እንዲሁም ግቦች ሁሉ ሊለያዩ ይችላሉ። እኛ ኢትዮጵያዊያን ወደ ብሔራዊ እርቅ ለመግባት መጀመሪያ ብሔራዊ እርቅ በኢትዮጵያ ሁኔታ (context) ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ካልተረዳን ብሔራዊ እርቁ ግቡን ላይመታ ይችላል። ወይም ደግሞ ለብሔራዊ እርቁ ሁሉን ማሳተፍ አንችልም። በመሆኑም ብሔራዊ እርቅ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጉዳይ አንስተን በሚገባ እንወያይ። ሃሳባችንን ለማፋፋት ብሔራዊ እርቅን ከአንዳንድ አገሮች ታሪክ አንጻር በመጀመሪያ እንመልከት።

ለምሳሌ ያህል በአውስትራሊያ ውስጥ የብሔራዊ እርቅ ጉዳይ ተነስቷል። እንደሚታወቀው ከታላቋ ብሪታኒያ የአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ሰፈራ ፕሮግራም በፊት አውስትራሊያ በነባር (indiginious) ሕዝቦች የተያዘች አገር እንደነበረች ይታወቃል። በሰፈራው ጊዜ በነባሮቹ ሕዝቦች ላይ የመፈናቀል፣ የማንገላታት ወንጀሎች ተፈጽመዋል። ዛሬ የአውስትራሊያ መንግሥት ያን የተፈጸመ ታሪካዊ ስህተት አመርቅዞ እንዳይቆይ የወሰደው ርምጃ ብሔራዊ እርቅ ማድረግ ሲሆን ከ 1998 ዓ.ም ጀምሮ መንግሥት የብሔራዊ እርቅ ወይም (National sorry day) አውጆ በየዓመቱ እየታሰበ ይገኛል። የዚህ የይቅርታ ቀን አዋጅ የሚያሳየው ነገር ላለፉት ስህተቶች ሃላፊነት የሚወስድ አካል መገኘቱንና የነበረውን ግፍ እውቅና መስጠት መቻላቸውን ለወደፊቱም እንደዚያ አይነት ግፍ እንዳይፈጸም ዋስትና መስጠታቸውን ነው። የአውስትራሊያ ችግር እንደኛ ላይታይ ይችላል። ይቅርታው ግን ለስንት አመት እንደሚደረግ አይታወቅም። ዋናው ግን በነባሩ ሕዝብ ዘንድ የነፍስ ጽዳት ለማምጣት የታሰበ በመሆኑ ብሔራዊ እርቁ ለአውስትራሊያውያን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። የነበረውን ታሪካዊ ችግር እውቅና ሰጥቶ ይቅርታ ማወጁ የአውስትራሊያን ሕዝብና መንግሥት ልበሰፊነትና አርቆ አሳቢነት ያሳያል። ነባር ሕዝቦችም በዚህ የሚረኩ ይመስለኛል። ከዛ ውጭ አፈታሪክ እንደሚናገረው ራሳቸው ነባር ሕዝቦችም ከሌላ ክፍለ ዓለም መጥተው የሰፈሩ

ናቸው። ለዚህ ነው በዓለም ላይ ያልተነቃነቀ ሕዝብ የለም የሚያስብለን። ርጋታና ወሰን የመጣው የተባበሩት መንግሥታት ከተቋቋመ ወዲህ የዓለም አገራት ድንበር ጉዳይ ዓለማቀፋዊ ጉዳይ እየሆነ ከመጣ ወዲህ ከቅርብ አስርታት ወዲህ ነው። የነዚህ ነባር የተባሉ ሕዝቦች ጥያቄ መሆን ያለበት በሰፈራው ወቅት የነበረው ግፍና በደል ሲሆን ለዛ ደግሞ መንግሥት አዘኑን ገልጿል። ይህ ደግሞ የነባሩን ወይም ቀደም ብሎ ወደ አውስታራሊያ ያቀናውን ሕዝብ ልብ የሚያሳርፍ ጉዳይ ነው። ችግሮች ተንከባለው እንዳይቀጥሉ ደግሞ እነሆ ዛሬ ተባብረው ዴሞክራሲያዊ መንግሥት አቋቁመዋል። ይቅርታው ግን አንዴ የሚበቃ ይመስላል። ከሁሉ በላይ ግን አሁን የገባኝ ነገር ቢኖር የአውስትራሊያ መንግሥት ርህሩህ በመሆኑ እንጂ ባለማችን ታሪክ ውስጥ ባለፈው ሥርዓት የተፈጸሙ ሁሉ በወቅቱ የነበሩ ስርዓቶች ችግሮች ነበሩ። ይሄ አለማቀፍ ክስተት ነው። ዓለም በንቅናቄ ወቅት በነበረችበት ጊዜ አጠቃላይ ከባቢው፣ የሰው ልጆች መረዳትና የኮሙኒከሽን ጉዳዮች ተደማምረው ለግፍ አጋልጠዋል። አሁን ያ ጊዜ አልፎ እነሆ የዴሞክራሲና የሰባዊ መብት ዘመን መጥቷል። ደቡብ አፍሪካን ደግሞ እንይ። በደቡብ አፍሪካም እንደዚሁ ታሪካዊ የሆነ ብሔራዊ እርቅ የተካሄደባት አገር ስትሆን ከአፓርታይድ አገዛዝ ለመላቀቅም ሆነ ከተላቀቀች በሁዋላ ደቡብ አፍሪካን በከፍተኛ የመንፈስ ልእልና ሲመራ የነበረው የብሔራዊ እርቅ ስሜት ነው። በደቡብ አፍሪካ ብሔራዊ እርቅ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት መካከል ኔልሰን ማንዴላ አውራ ናቸው። በኔልሰን ማንዴላ የተመራው ደቡብ አፍሪካን እንደገና የማነጽ ስራ ሲጀመር አገሪቱ ያለፈችበትን መራራ ችግር ለመፍታት የተጠቀመችው ዘዴ በሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ (Restorative justice) እና ቀስ እያለ በሚያድግ ዴሞክራሲ ቁስልን ማከምና የወደፊቷን የሁሉም የምትሆንን ደቡብ አፍሪካን መገንባት ይመስላል።

ደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ እንደተላቀቀች ወደ ሪትሪቢዩቲቭ ጀስቲስ (Retributive juctice) አተኩራ ቢሆን ምናልባትም ውጤታማ አትሆንም ነበር። ዋናው ጉዳይ ግን ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የአፓርታይድ ገዢዎች ለነበረው ችግር ሃላፊነት የመውሰድና ብሔራዊ እርቅን በሪስቶሬቲቭ ጀስቲስና በዝግ እያለ በሚያድግ ዴሞክራሲ ለመፍታት ፈቃደኛ በመሆናቸው የጥፋትና የሞት መላእክን ከደቡብ አፍሪካ ሊያባርሩት ችለዋል። ታላቁ የብሔራዊ እርቅ መሪ ኔልሰን ማንዴላም በዚህ ረገድ የተጫወቱት ሚና ታሪክ ሁሌ ሲዘክረው ይኖራል። የደቡብ አፍሪካን ችግርም ስናይ በወቅቱ የነበረው ችግር አፓርታይድ ነበር። ጽንፈኞች ይህን ያራምዱ ነበር። ይሁን እንጂ በአብዛኛው የነጩ ማኅበረሰብ ልብና ነፍስ ውስጥ ግን አፓርታይድ የተጠላ ነበር። አፓርታይድ ለመውደቁ አንዱ ምክንያትም ከጥቁሮቹ ትግል ጎን ነጩ ሕዝብ ለአፓርታይድ ድጋፍ ባለመስጠቱና በመቃወሙ ነው። ስርዓቱና የስርዓቱ አራማጆች ችግር ነበር ዋናው ችግር። ኔልሰን ማንዴላ በቅርብ ይህን በሚገባ የተረዱ ነበሩ። ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነጩ ማኅበረሰብ በአፓርታይድ አልተጎዳም ወይም አልተሰቃየም ማለት ደጋፊ ነበር ወይም አባሪ ነበር ማለት አይደለም። አሁን ላይ ሆነው ሲያዩ የሁዋላ ትውስታቸውን ሲያዩ ነጩም ጥቁሩም ያን ጊዜ ይኮንኑት ነው የሚመስለኝ።

የሩዋንዳን ጉዳይም እናንሳ። ሩዋንዳ በዚህኛው ክፍለ ዘመን የዓለምን ሕዝብ ያስደነገጠ ወንጀልን ካስተናገደች በሁዋላ ወንጀሉ ጋብ ሲል የወደፊት አቅጣጫዋ ግራ ያጋባት አገር ነበረች። ለአንድ መቶ ቀናት በየቀኑ ስምንት ሺህ ሰዎች፣ በየሰዓቱ ከሶስት መቶ ሰላሳ ሰዎች በላይ ያለቁባት አገር የወደፊት እጣ ፈንታዋን ለማሰብ በርግጥም እጅግ እጅግ ከባድ ስራ ነበር። ችግሩ እንዴት ይፈታ? በጎሳ ፖለቲካ ወይም ፌደራሊዝም? እንዴት ይፈታ? ምን ይሻላል? በጣም ፈተና ነበረባት።

በርግጥ ሩዋንዳ ያ ወንጀል ጋብ ሲል ለወደፊት እጣፈንታዋ ወዲያው አዋጭ መስመር መስሎ የታያት ብሔራዊ እርቅ ማውረድ ቢሆንም ብሔራዊ እርቁ በሩዋንዳ ሁኔታ ምን መልክ ይያዝ? በምን መልኩ ይፈጸም? የሚሉት ጥያቄዎች ግን በጣም ሊከብዷት የሚችሉ ጉዳዩች ነበሩ። በአንዳንዶች ዘንድ አጥብቆ ይቀነቀን የነበረው ጉዳይ ብሔራዊ እርቁ በሪትሪቢዩቲቭ ጀስቲስ አማካኝነት ሊፈጸም ይገባዋል የሚል ነበር። ሁላችን እንደምናውቀው ሪትሪቢዩቲቭ ጀስቲስ ማለት ለወንጀለኛው ተገቢውን ቅጣት በመስጠት የተበዳይን ነፍስ ማጽዳት ወይም ማርካት ማለት ሲሆን ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ደግሞ የሚያተኩረው ወንጀለኛውን በመቅጣት ላይ ሳይሆን ተበዳዩን በመካስ ላይ ያተኮረ የፍትህና የእርቅ ማውረጃ ዘዴ ነው። ታዲያ አንዳንድ ሩዋንዳዊያን ሪትሪቢዩቲቭ ጀስቲስ ነው ፈውስ የሚያመጣልን ሲሉ በርግጥ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ሳያገኙ አልቀሩም። ምክንያቱም ወንጀሉ የተፈጸመው በአጭር ጊዜ በመሆኑ፣ ወንጀሉ ግድያ በመሆኑ፣ ገዳይና የሟች ቤተሰብ ጎረቤት በመሆናቸው፣ አሰቃቂ ወንጀል በመሆኑ ሪትሪቢዮቲቭ ጀስቲስ ተገቢነው እንዲሉ የገፋፋቸው ይመስላል። ይሁን እንጂ በአንድ መቶ ቀናት ላለቀው ስምንት መቶ ሺህ ሕዝብ ገዳዩችና ለገዳዩቹ ተባባሪዎች ፍርድ ለመስጠት ሩዋንዳ አቅም አልነበራትም። ሩዋንዳ በዚያን ወቅት ላለቁት ስምንት መቶ ሺህ ቱትሲዎችና ለዘብተኞች ወደ አንድ መቶ ሺህ ወንጀለኞችን ለፍርድ አቅርባ መቅጣት ከፈለገች አጠቃላይ የፍርዱ ሂደት ወደ አንድ መቶ አመት ይፈጅባት ነበር የሚሉ ወገኖች አሉ። ያን ያህል ፍርድቤትም፣ ዳኛም ኢኮኖሚውም የላትም። በድህነት ላይ ነው ይህ ነገር የወደቀባት።

ሪስቶረቲቭ ጀስቲስን ተጠቅማ ችግሯን ለመፍታት ብትሞክር ደግሞ ገዳይና ሟች ጎረቤታም በመሆናቸው፣ የሟች ደም ገና ስላልደረቀ በርግጥ የአገሪቱ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ሌላ ችግር ውስጥ መውደቁ ሌላ አሳብን ያመጣባት ትመስላለች። ሩዋንዳ የነበረችበት መስቀለኛ መንገድ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የጣላት በመሆኑ ሁለቱንም የፍትህ አሰጣጥ ዘዴዎች አደባልቃ እንድትሄድ ሳያስገድዳት አልቀረም። በመሆኑም ባህላዊ የጋካካ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም የተወሰነውን ችግር በዚህ በሪትሪቢዩቲቭ ጀስቲስ የተወሰነውን ደግሞ ዝግ እያለ በሚያድግ ዴሞክራሲና በሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ይፈታል እያለች እየደለለች ማርገብ ችላለች። ከሁሉ በላይ ግን ሩዋንዳ ወደ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ክርስቲያን በመሆኑና አብያተ ክርስቲያናት የሚሰብኩት የይቅርታና የምህረት ትምህርት የሩዋንዳን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ አስተዋጾ ሳያደርግ አልቀረም። የነዚህ አብያተክርስቲያናት የይቅርታ ስብከት ለሩዋንዳ ሃዘንተኞች መጽናናትን ሰጥቷል። በአጠቃላይ የሩዋንዳ ችግር ውስብስብና አስቸጋሪ በመሆኑ ሁለቱም የፍትህ አሰጣጥ ዘዴዎች ተግባር ላይ የዋሉ ይመስላሉ።

ለአብነት በየሃገሩ የተፈጸመውን ወንጀል እያነሳን የተወያየነው ችግር በየቤቱ አለ፣ ይሁን እንጂ ሁሉም አገር ችግሩን ለመፍታት ጥረት እያደረገ ነው አገር የቆመው ለማለት ነው። ወደኛው አገር እንመለስና ብሔራዊ እርቅ በኢትዮጵያ ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት።

በኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የብሔራዊ እርቅ ይዘት ለማየት መጀመሪያ ስለ አለፈው ታሪካዊ ግድፈቶች ማንሳት ተገቢ ነው። ከፍ ሲል እንዳልነው በአውስትራሊያ ውስጥ ለነበረው ግፍ ሃላፊነት የሚወስድ እውቅና የሚሰጥ አካል ተገኝቱዋል። ወደኛ አገር ስንመጣ ላለፉት በደሎች እውቅና ለመስጠትም ሆነ አንድ አካል ለጥፋቱ ሃላፊነት ለመውሰድ የምንችልበት ሁኔታ ጠፍቷል። ይህ የሆነበት ምክንያት ሁሉም የባህል ቡድን በየፊናው ባለፉት ስርዓቶች ተጎድቻለሁ ባይ በመሆኑ ነው።

በአጼ ምኒልክ ጊዜ የጠፉ ጥፋቶች ካሉ ለነዚያ ጥፋቶች የአማራውን ሕዝብ ሃላፊነት ውሰድና ይቅርታ በል የሚል አካል ቢነሳ አማራው ለራሱ ተበድያለሁ ባይ ነው። በፊውዳሉ ሥርዓት በጭሰኝነት፣ በባርነት መከራየን አይቻለሁ።  በወቅቱ የተጠቀሙት ጥቂት ፊውዳሎች ናቸው። ተውኝ እባካችሁ ይላል።  በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመንም ቢሆን የወሎ ርሃብ ሲመጣ ኃይለሥላሴ ዓለም እንዳይሰማ አድርገው በዚያ ደረጃ ጨክነው አስጨርሰውኝ የለም ወይ? ደርግ አማራ ነው ካላችሁ ደግሞ የጎንደርንና የወሎን ወላድ እምባ አታዩም ወይ? ወዘተ. እያለ እያነባ ባለፉት ስርዓቶች የተጎዳውን ይቆጥራል። ኦሮሞው በበኩሉ በዚህኛውም ባለፈውም መንግሥት ተነጥየ ተጎዳሁ፣ ባህሌ፣ ማንነቴ ተጎዳ ብሎ እያነባ ይናገራል፣ ትግሬው በበኩሉ ባለፈውም ሆነ አሁን የተመቸኝ ነገር የለም፣ የውስጥ ችግሬን እኔ ነኝ የማውቀው ተለይቼ ተበድያለሁ እያለ ያነባል፣ የደቡብ ሕዝቡ ተበድያለሁ የኔን መከራ ማን ባየው እያለ እያነባ ይናገራል፣ ሱማሌው የኔ መከራ መቼ ነው የሚያቆመው? መከራየን እያየሁ ነው እያለ ያነባል። ጋምቤላው፣ አፋሩ ሁሉም በተናጠልም በቡድንም ተጎድቻለሁ እያለ ያነባል። ታዲያ እንዲህ በሆነባት አገር ብሔራዊ እርቅ ምን መልክ ይኖረዋል የሚለው ጥያቄ ላይ ነው በጥልቀት መወያየት ያለብን።

በመጀመሪያ ግን እኛ ኢትዮጵያዊያን ያለፉ ታሪካዊ ችግሮች አጥንተን መፍትሄ ለመስጠት የታሪክ ተዓማኒነት ችግርም ገጥሞናል። በተለይ በአሁኑ ወቅት ፖለቲካው ከፋፍሎ የመግዛት ዘዴን የሚጠቀም በመሆኑ አንዳንድ በፈጠራ የሚጻፉ ታሪኮች ያለፈውን ታሪካችንን በሚገባ አይተን ብሔራዊ እርቅ ለማምጣት እንቅፋት ነው። የሆነ ሆኖ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ላለፈውም ሆነ አሁን ላለው ግፍና በደል አንድ ቡድን እንደ ቡድን ሃላፊነት ወስዶ ይቅርታ የሚልበት ሁኔታ የለም። በደቡብ አፍሪካም ሆነ በአውስትራሊያ ወይም በሌሎች አገሮች እንደተፈጠረው አይነት ሃላፊነት ወስዶ የቡድኖችን እንባ የሚያብስ ጠፋ። በመሆኑም የኢትዮጵያ ምሁራን በዚህ አስቸጋሪ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራዊ እርቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ሁላችንን የሚፈውስ አሳብ በግድ አምጠው ሊወልዱ ይገባል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳየው ቡድኖች እንደቡድንም በጅምላም ባለፈው ጊዜ ለደረሰባቸው በደል ሁሉ ያለፈውንና አሁን ያለውን ሥርዓት የታሪክ ተጠያቂ ማድረጉ አንዱ የስምምነቱ አሳብ ወለል ቢሆን መልካም ነው። ይሁን እንጂ ላለፉት ችግሮቻችን ቡድኖች እንደ ቡድን ተጎዳሁ የሚሉት ካለ ለዚያ ቡድን ጉዳት እውቅና መስጠት አንዱ የስምምነቱ አካል ሊሆን ይገባል። አንድ ቡድን ተጎዳሁ ተጎድቼ ነበር ሲል የለም ያንተ ጉዳት ትንሽ ነው የኔ ይበልጣል ማለቱ ብሔራዊ ፈውስን አያመጣም። ሰው ህመሙን የሚያውቀው ራሱ ነው። በመሆኑም ቡድኖች የተጎዳነው አለ ሲሉ ማዳመጥና ሃዘንን መጋራት ለችግር እውቅና መስጠት ነው የኢትዮጵያ እርቅ መሰረቱ። ኦሮሞው አጼ ምኒሊክ ጎድተውኛል ካለ ሌላው ብሔር ልክ አይደለም አልጎዱህም ማለቱ ለብሔራዊ እርቁ አይጠቅመንም። አንዱ ዜጋ አጼ ምኒሊክ ካጠፉት ጥፋት ይልቅ የሰሩት ጀብዱ በተለይም ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪ ለመመከት ያደረጉት ተጋድሎ ከበለጠበት ቢወዳቸው ቢፎክርላቸው ሌላው ኢትዮጵያዊ መበሳጨትና ጥል ውስጥ መግባት የለበትም። አንድ መሪ ለአንዱ ኢትዮጵያዊ ተወዶ ለሌላው የሚጠላ ቢሆንም ከዚህ ልዩነታችን ጋር አብረን መኖር እንችላለን። ኢትዮጵያዊ ለመሆን ሁሉ ሰው አጼ ምኒሊክን መውደድ አለበት ማለት አይደለም። ፕሬዚደንት ኦባማንና ፕሬዚደንት ቡሽን የሚወድም የሚጠላም በሰላም እንደሚኖረው እኛም ከልዩነት ጋር መኖርን መልመድ ያስፈልገናል።

አሁን እኛ ጋር ያለው የኮሙኒኬሽን ችግር ይመስላል። የኮሙኒኬሽን ችግሮች ምንጫቸው የእውነት መዛነፍ (distortion of truth) እንዲሁም የማንነት ፖለቲካ ውጤቶች ስለሆኑ ለነዚህ ችግሮች ራስን ሰለባ አለማድረግ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ እርቅ ዋናው መሰረት እርስ በርስ መረዳዳት (understanding eachother) ነው ማለት ነው። ያለፈውን ህመማችንን በመደማመጥ ነው ልንፈታው የምንችለው። ችግራችንን ስንገልጥ የለም ያንተ ቁስል ትንሽ ነው የኔ ነው ትልቁና አንተ ስለ ብሶትህ አታንሳ አይባልም። ቢሆን ቢሆን ራስን ከውጭ ወደ ውስጥ ከውስጥ ወደ ውጭ የማየት ልብ ቢኖረን እሱ ነው ያለፈውንና አሁን ድረስ የቀጠለውን ችግራችንን የሚፈታው። በአሁኑ ሰዓት እኔ ኦሮሞ መሆኔ ቀርቶ ትግራይ ሆኘ ብፈጠር ምን ይሰማኝ ነበር? ምን እሆን ነበር? ብሎ ቢያስብ በአንጻሩ የትግራይ ሕዝብ ኦሮሞው አማራው ተለይቼ ተጎዳሁ ሲል በአሁኑ ሰዓት እኔ ኦሮሞ ሆኘ ተፈጥሬ ቢሆን ምን ይሰማኝ ነበር? የሚል ከፍ ያለ መረዳት(understanding eachother’s pain and understanding each other’s feelings) በተለይ በሌሂቁ በኩል ቢታይ ነው የብሔራዊ እርቁ መሰረቱ የሚጠብቀው። አንድ ሰው ጉዳቴ ከፍተኛ ነው ሲል የለም ያንተ ትንሽ ነው የኔ ነው ትልቁ ጉዳት ወደ ማለት ማዘንበላችን የኮሙኒኬሽን ችግር ያመጣብናል። እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እኛ ኢትዮጵያዊያን ያለፈውን ችግር በብሔራዊ ይቅርታ ለመዝጋት የገጠመን ችግር ይሄው የኮሙኒኬሽን ችግር ነው። ያለመደማመጥና ህመምን ለመካፈል መድረክ ማጣት ትልቅ ችግሮች ሆነዋል። ሌላው ደግሞ ቅድም እንዳልኩት ያለፈውን ችግራችንን በብሔራዊ እርቅ ለመፍታት የነበሩትን በደሎች ወደ መድረክ አምጥቶ እውነትን ለመግለጥ አሁን ያለው መንግሥት ታሪክን ስላቆራፈደውና ብርታትንም ሆነ ድካምን ከቡድን ማንነት ጋር እንድናያይዝ የሚገፋ ነገር በመኖሩ በከፍተኛ ሁኔታ እውነትን የማግኘት ችግር ይገጥመናል። በተጨማሪም ኢትዮጵያዊያን አዳዲስ በሚወለዱ ታሪኮች ሳንደነብር ከስሜት በላይ ሆነን እርስ በርስ በመረዳዳትና አለ ለተባለው ችግር እውቅና በመስጠት ነገሩን ማርገብ ይጠበቅብናል። ከሁሉ በላይ ግን ኢትዮጵያ ያለፈውን ችግር ልታይበት የምትችልበት አንድ ሌላ ትልቅ ነገር የዛሬው ይዞታዋ ነው። በፊት

የነበሩ ማኅበራዊና ፓለቲካዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አሁን ድረስ እየተንከባለሉ መጥተው ስለሚገኙ አሁን ያለውን በቡድኖች መካከል ያለውን ክፍተት በሪስቶሬቲቭ ፍትህ ልትፈታው ይገባታል። በትምህርት፣ በፖለቲካ ተሳትፎ በባህልና በቋንቋ አካባቢ ያለውን ችግር ኢትዩጵያ ለመፍታት ስምምነት ውስጥ መግባት አለባት። ይህ ስምምነት ነው አንዱ የብሔራዊ እርቁ ይዘት። ሪስቶሬቲቭ ፍትህ ስንል በማኅበራዊ ተቋማት ግንባታ ይሁን ከፍ ሲል በገለጽናቸው ሁኔታዎች የተጎዱ አካባቢዎችን በአፌርማቲቭ አክሽን ዘዴዎች ለመፍታት ስምምነት ላይ መጀመሪያ መድረስ አለብን። ሌላው ጉዳይ ደግሞ ቅድም እንዳልነው ትውስታዎቻችንን የጋራ አድርጎ ማሰቡን አለመርሳት ነው። ክፉውንም ደጉንም የጋራ ታሪክ አድርጎ መቁጠር በጣም ከፍ ያለ መረዳት ነው። በአጼ ምኒሊክ ዘመን የተፈጠሩ መልካም ነገሮችን ስንዘረዝር በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የነበሩትን ቡድኖች ሁሉ ይመለከታል። ቀረጥ የከፈሉና ለመንግሥት የገበሩ ሁሉ ታሪካቸው ነው። ልክ እንደዚሁ የተፈጠሩ ስህተቶች ሲታወሱን ደግሞ ቀረጥ የከፈለው ግብር የከፈለው ሕዝብ ሁሉ የጋራ ታሪኩ መሆኑን ማሰብ ነው። ጥሩ ጥሩውን እየነቀስን አውጥተን የጋራ ታሪካቸን ነው እያልን መጥፎውን አውጥተን ለአንድ ቡድን ማሸከም ሚዛናዊነት የጎደለው ነው። ለብሔራዊ እርቅ እነዚህ መረዳቶች መሰረት ይሆኑናል። ከሁሉ በላይ ለኮሙኒኬሽን መጠልቀቅ ነው እርቁን ወይም መግባባቱን የሚያፋጥነው። ለኮሙኒኬሽ መጠንቀቅ ማለት አንድ የኦሮሞ ሰው ባለፈው ሥርዓት ባህሌ ተጎዳ ብሎ ተክዞ ሲነግረኝ የተጎዳኸው አንተ ብቻ መሰለህ እኔም ነኝ። የኦሮሞ ባህል በመጎዳቱ እኔም ነኝ ያጣሁት አገራችን በዚህ ሁኔታ ውስጥ አለፈች ያሳዝናል። አሁን እንዳይደገም መጣር አለብን ብለው አለቀ ማለት ነው።

በመሆኑም ኢትዮጵያ በስምምነቱዋ ወቅት የምታካትታቸው ጉዳዩች በግልጽ መጀመሪያ መቀመጥ አለባቸው። ቡድኖች እንደ ቡድን ሁሉም ተበድለዋልና ብሔራዊ እርቁ ሁሉንም ሊክስ የሚችልና ኮሙኒኬሽንን የሚያዳብር መሆን አለበት። በዓለማችን የሚነሱ ጦርነቶች አብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል ምክንያታዊነት ያላቸው አይደሉም አብዛኛዎቹ ከኮሙኒኬሽን ችግር ጋር የተያያዙ ናቸው መሰለኝ። አንዳንዴ ቡድኖች የተጣሉበትን ሁኔታ በውል ሳያውቁት ብዙ ይዋጉና ብዙ ሰው ካለቀ በሁዋላ ይታረቃሉ። የሚገርመው ሲታረቁና ስሜታቸው ሲረጋ የከፈሉት ዋጋ እንዲሁ ሜዳ ላይ ሆኖ የሚያገኙበት ጊዜ ይኖራል። የባድሜው ጦርነት ምሳሌ ነው። በመሆኑም ብሔራዊ እርቁ በቡድኖች መካከል ያለን ኮሙኒኬሽን ለማስተካከል መላ ሊወልድ ይገባዋል።

ከፍ ሲል እንዳልነው ብሔራዊ እርቅ በኢትዮጵያ የሚኖረው መልክ ሁሉንም በመካስ ላይ ሁሉንም ችግሮች እውቅና በመስጠት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። በተለይ ያለፈውን ችግራችንን ለመፍታት ችግሩ ከኮሙኒኬሽንና ከስሜት ሃያልነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በረጋና በሰከነ መንፈስ ዜጎች ያለፈውን ችግራቸውን በጋራ እውቅና ሰጥተው ሲንከባለል ለመጣው ችግር ደግሞ አፈርማቲቭ አክሽንስና ሌሎች የርስበርስ የመካካሻ ዘዴ ተጠቅመው ፈውስን ማውረድ አለባቸው። ያለፉት ጨቋኞች በግልም በቡድንም እየለዩ ሲጨቁኑን መኖራቸውን የጋራ መረዳት ላይ መድረስ አለብን ።

ስለ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ስናወራ ለተበደሉ ቡድኖች ሁሉ ትልቁ ካሳ አዲስ የሚፈጠረው የማኅበራዊ ፖለቲካ ሲስተም ነው። ይህ ሲስተም ካሳቸው ከሆነ የብሔራዊ እርቁ መሰረት እሱ ነው። CCU አንዱ ትልቁ ፍላጎቱ ሁሉንም የሚክስ ሲስተም ለመፍጠር ነው። በባህል ማንነት የተጎዳነውን ባህላዊ ማንነታችንን የሚንከባከብ ጠገግ መፍጠር፣ የቋንቋ አጠቃቀም ፖሊሲን አውጥቶ ሁሉን ቋንቋዎች አፊሺያል ማድረግ፣ ሁሉን ቋንቋዎች ብሔራዊ ቋንቋ ማድረግ ትልቁ ካሳ ነው። በፖለቲካው መስክ ዴሞክራሲን መሰረት አድርገን ጥራት ያላቸውን ተቋማት መገንባት ስንችል ያ ነው የሁሉም ቡድኖች ካሳ።

በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ ውህደት ብሔራዊ እርቅን በኢትዮጵያ የሚያየው እንደዚህ ነው። በዚህ ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ብሔራዊ እርቁ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስን መሰረት ያደረገና በሚያድግ ዴሞክራሲ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል ስምምነት ማለት ነው። ይህ ማለት ግን ሪትሪቢዩቲቭ ጀስቲስ ቦታ የለውም ማለት አይደለም። በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ሙስናና ከፍተኛ ወንጀል እየፈጸሙ ያሉ ሰዎች ይህንን አሳባችንን እያዩ እንደ ጅልነት አይተው ከሥልጣን እስኪወርዱ በግፋቸው እንዲቀጥሉ በር አይከፍትም። የብሔራዊ እርቅ ሰነዱ እንደነዚህ አይነት ሰዎችን በቡድን እያየ ሳይሆን በግለሰብ ደረጃ ወደ ፍርድ ሊያመጣቸው መቻሉ አያጠያይቅም። እንደ ቡድን እንደ አገር ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻችንን ዝግ እያለ ሊሰራጭ በሚችል የሪዲስትሪቢዩሽን ዘዴ ተመጣጣኝ እድገት ለማምጣት መስማማት፣ ፖለቲካዊ ተሳትፎን ከባህላዊ ውህደት ስምምነት አንጻር አይቶ ከብሔር ፖለቲካ አውጥቶ በአንድ ብሔራዊ ማንነት ስር ለመገንባት መስማማት ፈውስን ለማምጣት ይጠቅማል። ኢትዮጵያ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ላይ እንድታተኩር የሚያደርጋት ለዘላቂ ሰላምና ልማት አንድነት የሚረዳት ሲሆን ይህ የፍትህ አሰጣጥ ዘዴ በኢትዮጵያ ቡድኖች ዘንድ የተባረከና የሚበረታታ ነው። የኦሮሞ ሥርዓትን ብናይ ለሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ትልቅ ቦታ አለው። ይቅር ማለትን፣ በዳዩን ከመቅጣት ይልቅ ተበዳዩን መካስን ያበረታታል። አማራው አካባቢ ያለውን የሽምግልና ሥርዓት ስናይ በአብዛኛው ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ የሚበረታታበት ሁኔታ አለ። በደቡብ፣ በምሥራቅ በተለይም በሶማሌ ክልል ይህ የፍትህ ሥርዓት ከፍተኛ ተጽእኖ አለው።

የሃይማኖት ዳራችንም ቢሆን ወደ መቶ ፐርሰንት የሚጠጋው ሕዝብ ሃይማኖተኛ በሆነበት አገርም ይህ የፍትህ ሥርዓት ሊሸከመው የሚችል በተፈጥሮው የተደራጀ ተቋም በመኖሩ ተመራጭ እንዲሆን ያደርገዋል።

ሌላው ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ባለፈው ጊዜ በግድ በሆነ ምስለት ጠፉ የሚባሉ ባህሎች ካሉ እነሱን የማስመለስ (Restoration and revival of cultural heritages) ስራ ለመስራት መስማማቱ ነው አንዱ የእርቁና የካሳው ሰነድ የሚይዘው ጉዳይ። የጠፉና በመጥፋት ላይ ያሉ ጠቃሚ ባህሎች ካሉና ቡድኖች የሚቆጩባቸው ከሆነ የማስመለስ ፖሊሲ

አውጥቶ ቡድኖችን ሁሉ አስተባብሮ ለመካስ ኪዳን መግባት። ቡድኖች አጣናቸው የሚሉዋቸውን በሙሉ ለማስመለስ ባይቻልም አብዛኛውን በመመለስ የቡድኖችን ልብ ማሳረፍ ይቻላል።

ሌላው የብሔራዊ እርቁ ሰነድ ሊይዘው የሚገባው ጉዳይ ለወደፊቱዋ ኢትዮጵያ የሚሆን አስተዳደራዊ ባህልን የመገንባት ስምምነት ሲሆን ይህም ዴሞክራሲ ነው። ቡድኖች በመጀመሪያ ዴሞክራሲ ከአሁን በሁዋላ ያስተዳድረን መንግሥታት ቢቀያየሩም ዴሞክራሲ ግን የጋራ ባህላችን ይሁን የሚል ስምምነት ውስጥ ሊገቡ ይገባል። ይህ አስተዳደራዊ ባህል የጋራ የሁላቸው በመሆኑ ወደፊት ለሕይወታቸው መሪ ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው መስመር ያለበትና የስምምነቱ አንዱ አካል ሊሆን የሚገባው ለመልካም ታሪኮቻችንም እውቅና መስጠት ነው። ኢትዮጵያን የመከራ ቤት ብቻ አድርጎ ከማየት የአፍሪካ መቀመጫ ያደረጋትን የነጻነት ታጋይነቱዋን ማስታወስና ለነዚህ ታሪኮቻችን ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ አስተዋጾ በማድረጋቸው እውቅና ሊሰጡት ይገባል። ይህ አይነቱ ስሜት ሚዛናዊ የሆነ ስሜትን ከመፍጠሩም በላይ አገር አለን ስንል የምንመካባቸው ብዙ አኩሪ ታሪኮች እንዳሉንም ስለሚያደርግ ነው።

በአጠቃላይ ብሔራዊ እርቅን በኢትዮጵያ ጨምቀን ካየነው በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነትን መፍጠር ማለት ነው። ስለዚህ CCU ብሔራዊ እርቅን የሚያየው ለአዲሲቱ የተባበረችው ኢትዮጵያ የምናደርገው የጋራ ስራ ነው።

ስለ ብሔራዊ እርቅ ስናወራ አብዛኛው ጉዳይ ከስሜት ጋር የተያያዘ በመሆኑ አንዱ ሌላው ያለፈውን ጥሩ ያልሆነ ትውስታ ያመጣውን ችግር ለመፍታትና አሁን ያለውን የቅሬታ ችግሮች ለመፍታት ዜጎችና ለሂቃን ከላይ ሆነው እንዲያዩ ነው የሚያስፈልገው። ከላይ ሆነን ስናይ ችግሮቻችን ገዝፈው አይታዩንም። ከላይ ከዓለም ታሪክ፣ ከላይ ከግሎባላይዜሼንና ከዓለም ስላጣኔ፣ ከላይ ከአፍሪካ ህብረት፣ ከላይ ከአፍሪካ ቀንድ ላይ ቆመን ስናይ ነው የሰከነ መፍትሄ የምናመጣው። ይሄ ጉዳይ በተለይ ለሂቁን ይመለከታል። ትልቁ ችግር ችግሮቻችንን ከስር ከስሩ ስናይ ነው። ከስር ስናይ ገዝፈው ይታዩናል። የብሔር ፖለቲካ አንዱ ትልቁ ችግር ይሄ ነው። ራሱ ተፈጥሮው ከታች ከ DNA እንድንነሳ ከዚያም ቤተሰብ ከዚያም ዘመድ አዝማድ ከዚያም ጎሳ ከዚያ መጨረሻ ላይ ነው አገር ብለን እንድናስብ የሚያደርገን። በብሔር ፖለቲካ ጊዜ የመጨረሻው ታሳቢ አገር ሲሆን የመጀመሪያው ጉዳይ ራስ(self) ነው። ለዚህም ነው እኔ እኔ እኔ (Me... Me.... Me....) የሚበዛበት። የፖለቲካው ተፈጥሮ ከደም ጋር ለተያያዘው ከፍተኛ ዋጋ ሲሰጥ ከደም ብዙ ርቆ ለሚገኘው አገር ለሚባለው ጽንሰ ሃሳብ የሚሰጠው ዋጋ ዝቅ ይላል።

ከላይ ሆነን እንይ ስንል ስለ ፖለቲካ ስናስብ ስለ የፖለቲካ ተሳትፎ ስናወራ ወይም የፖለቲካ ቤት ስንሰራ ከላይ ከብሔራዊ ማንነት ነው መጀመር ያለብን። ከላይ ከኢትዮጵያዊነት የምንጀምረውና በዚህ ጥላ ስር የምናደርገው መሰባሰብ ፍትህን ለማምጣት ዴሞክራሲን ለማምጣት ይረዳናል። በብሔር ፖለቲካ ጊዜ ፍትህን ከሚያቀጭጩ መንስዔዎች መካከል አንዱ የፖለቲካው እምነት በDNA ላይ የቆመ በመሆኑ ነው። ይህ ነገር ሥነ- ሕይወታዊ የሆነ ነገር ቢሆንም በዚህ ሥነ- -ሕይወት ላይ የፖለቲካ ቤት እንድንሰራበት አይደለም የሚያስፈልገው። የሚያስፈልገው የቤተዘመድ ማህበር ማቋቋም ነው። ወይም ማኅበራዊ የሆነ ስራን ለመስራት ነው። የደም ሐረግን ፈልጎ በጎሳ ላይ የሚቆም ፖለቲካ ከዴሞክራሲና ከፍትህ ጋር የማይሄደው ዴምክራሲ በተፈጥሮው የሚያየው ከላይ ስለሆነ ነው። ዴሞክራሲ የመርህ ጉዳይ ነው መሰረቱ። የጎሳ ፖለቲካ ደግሞ በደም ሐረግ ላይ ቆሚያለሁ ለሚለው ቡድን ነው መሰረቱ። ይህ ተፈጥሮው ነው ከዴሞክራሲ የሚያለያየው። ዴሞክራሲ ልክ እንደ ንስር ነው። ከላይ ሆኖ ወደ ታች ያሉትን የልዩነት ቅንጣቶች ሁሉ አብጠርጥሮ እያየ ይጠብቃል። ንስር በተፈጥሮው ከፍ ብሎ የሚበር ፈጣን ሲሆን ከብዙ ከፍታ ወደ ታች ጥቃቅን ቅንጣቶችን ሁሉ ያያል። ራሱን እያደሰም የሚኖር ልዩ ፍጡር ነው። ዴሞክራሲ እንዲህ ነው። በመርሆዎች ላይ ቆሞ ራሱን እያደሰ ግን ደግሞ ታች ግለሰቦችን እያየ ይጠብቃል። በአንጻሩ የጎሳ ፖለቲካ ደግሞ በመሬት ላይ የሚንደባለል ሲሆን ከፍ ሲል እንዳልኩት ወደ ላይ የሚያየው አገርና ዴሞክራሲ ሩቅ ናቸው። አበሾች ከላይ ሆነን ነው ማየት ያለብን። በዴሞክራሲ ጊዜ ነው ብዙህነት ተግባራዊ የሚሆነው። ዴሞክራሲ ሲገዛ፣በመሰረቱ የልዩነት የመጨረሻ ቅንጣት ያለውም በግለሰብ ደረጃ ሲሆን ከዚያ ከፍ እያለ በቡድን እስከ መለያየት ይደርሳል። ዴሞክራሲ የሚቆመው በዚህ በግለሰቦች በዜግነት መብት ላይ ሲሆን ቤቱን የሚሰራው ከላይ ከብሔራዊ ማንነት ከመርህ አንጻር ነው። በአንጻሩ የብሔር ፖለቲካ ደግሞ በቡድን ላይ ቆሞ እነዚያን የቡድኑን አባላት የሚያያይዝበት ሙጫ የደም ሀረግ ነው። ዴሞክራሲ በአንጻሩ ግለሰቦቹን የሚያያይዘውና የሚያደራጀው በእሴቶች ላይ ነው። ዴሞክራሲ ለእሴቶች ትልቅ ዋጋ ያለው ሲሆን በፍትህ ፊት በዴሞክራሲ ጊዜ የስጋ ወንድሜና ሌላው ኢትዮጵያዊ እኩል ናቸው። ዴሞክራሲ የሚመክረኝ የስጋ ዘመዴን በጓዳ በግል ሕይወቴ እንድንከባከብ ሲሆን በአደባባይ በፖለቲካ ጊዜ ግን በብሔራዊ ማንነት ጥላ ስር የተዛመደኝ ሁሉ ወንድሜ እንዲሆን ነው። ይህ ሥነ- ሕይወታዊ ያልሆነ ነገር ግን የኪዳን ጉዳይ ነው። ዴሞክራሲ ከዝምድና ኪዳን ይበልጥበታል።

በደም ሐረግ Genealogical DNA ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ በተለይ በድህነት ለምንታወቅ ለኛ፣ ረሃብ ለሚያጠቃን ለኛ ከፍተኛ ችግር ነው። አንድ የፖለቲካ አሳላፊ አንድ የሱ ብሔር አባልና አንድ ከሱ ብሔር ውጭ የሆነ ሰው ተርበው ሲለምኑ ሲያይ ቀድሞ ልቡ የሚነካው ለዚያ ደም አለኝ ለሚለው ሰው ነው። ይህ በራሱ ሳይሆን ችግሩ ይህ ልቡ ያደላለትን ሰው ለመርዳት የሚያስችል የፖለቲካ ሥልጣን ሲይዝ ይችላል። በዚህ ጊዜ ይህን ሥልጣን መጠቀሚያ አድርጎ አድልዎ እንዲፈጽም የማድረግ ልዩ ጉልበት ስላለው ነው የብሔር ፖለቲካ የሚጠላው። የብሔር ፖለቲካ አድልዎ ለመፈጸም ምቹ ሲስተም ስለሚዘረጋ ነው የምንጠላው። ጨክነን ከላይ እንውጣ፣ ከላይ እንይ እኛ እዚህ ስለ ብሔር ፖለቲካ ስለ ዞንና ቀበሌ መገንጠል ስናወራ የአፍሪካ

ህብረት እውን ቢሆንስ? አፍሪካ ብትዋሃድስ። አሁንም ሲዳማን ነጻ ለማውጣት እንታገላለን? አሁንም ጋምቤላን ነጻ ለማውጣት ልንታገል ነው?

አሁንም አፋርን ወይም ኦጋዴንን ነጻ ለማውጣት ልንታገል ነው? የአፍሪካ ቀንድ የሆነ ጥምረት ውስጥ ቢገባስ? በዚህ ከፍታ ላይ ሆነን በዚህ ጉልህ መነጽር ስናይ የኛ የመንደር ፖለቲካ ምን ያህል አንሳ እንደምትታይ ማሰብ ይጠበቅብናል። መገንጠልን መፍትሄ ያደረግን ዞኖችና ክልሎች መገንጠል እውን ቢሆን ተገንጥለን የት ነው የምንሄደው? እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ክፍላተ አገራት ይቅርና የአፍሪካ ቀንድ ራሱ በሆነ መንገድ ካልተቀናጀ ከችግር አይወጣም። ለኢኮኖሚ እድገትና ከዚያ ክልል ረሃብን ለማጥፋት መልካም አስተዳደር ለመገንባት ተደጋግፎ ነው ማደግ የሚቻለው። አንዱ አካባቢ ግንጥል ብሎ ብቻውን የተሻለ ሕይወት ለመግፋት የሚያስችል ከባቢ የለንም። ይህንን ነው ማሳብ ያለብን። ከሁሉ በላይ አሁን ያለው ትልቅ ችግር የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቱ ያልተሟላባት አገር ናት አገራችን። የከፋ ችግር አለ። በፐላኔት ላይ የመጨረሻ ድሃ ነን። ስለዚህ እባካችን ይህንን ነው ማየት ያለብን። ስለነዚህ ስለ ተቸገሩ ሰዎች ሲባል የፖለቲካ ሰዎች በሆነ ህብረት ውስጥ ገብተውና ተቻችለው ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። አለበለዚያ ውጭ ያለው ሰው በርገሩን እየገመጠ፣ አገር ቤት ያለው ባለሥልጣን በሕዝብ ሀብት እየደነሰ የምናደርገው የእልህ ፖለቲካ በመሃል ደሃውን እንጀራ ስላሳጣው ቢያንስ ሃላፊነት የሚሰማው ተቃዋሚ በፍጥነት ወደ አንድ የጋራ አጀንዳ መምጣት አለበት። ኢትዮጵያውያን ለሂቃን ይህን እንደሚያደርጉና የሁላችንን የዜጎችን ጥያቄ እንደሚመልሱ አምናለሁ።

እነዚህ የብሔር ኢንተርፕሩነርስ የሚባሉት በቀላሉ ወደሚፈልጉት ሥልጣን የሚያሳልፍ ብቃት ሳይኖራቸው ሲቀር፣ አንዳንድ ጊዜም ለተጠናወታቸው የሥልጣን ጥማት ሁኔታዎች አልመች ሲሉ በፍጥነት የሚታያቸው በብሔር ተቆርቋሪነት ስም ብቅ ማለት ነው። ይሄ በጣም አደገኛ ነገር ነው። እነዚህ ሰዎች አንዳንዴም የብሄራቸውን ብዛት እየያዙ ያንን የሥልጣን ጥያቄ ማቅረቢያ ያደርጉና በዚያ ትከሻ ላይ የሚፈልጉትን የግል ጥቅም ማግኘት ይሻሉ። የብሄሩ ብዛት አነስተኛ ሲሆን ደግሞ የመገንጠል ጥያቄን ይዘው የሚፈልጉትን ሥልጣን ለመያዝ ይሞክራሉ። ግለሰቦች ሥልጣን ሲሹ በብዙ መንገድ ይመጣሉ። አንዳንዶች በኀይል፣ በጠብ መንጃ ሥልጣን መያዝ ይሻሉ ሁዋላም ዲክቴተር ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ራእያቸውን አሳይተው ሕዝብ መርቋቸው እንዲመጡ ይሻሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ብሔርን፣ ደምን ታከው ወደ ሥልጣን መምጣት ይሻሉ። ከነዚህ ሁሉ አደገኛው ጎሳን ለሥልጣንና ለግል ፍላጎት መጠቀም ነው። ኢትዮጵያውያን ከእነዚህ መጠበቅ አለባቸው። በጣም አደገኞች ናቸው። ለብሔራዊ መግባባትና እርቁም እንቅፋት ናቸውና መንቃት አለበን።

## የፖለቲካ ድርጅቶች

እርግጥ ነው አዲስ ኪዳን የሚገቡት ፓርቲዎች አይደሉም። የመጀመሪያውን የኢትዮጵያውያን ኪዳን የሚያቆሙት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ናቸው። የፖለቲካ ቤት የምንሰራው ከዚህ ኪዳን በሁዋላ በዚህ

ኪዳን መሰረት ነው። የፖሊሲ የርእዩት ልዩነት ቢኖርም ከኢትዮጵያውያን ኪዳን ስሜት ግን ፈቀቅ ሊል አይችልም። ይሁን እንጂ ስለአዲስ ኪዳን ስናወራ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ሁሉ ወደዚህ መሰረታዊ ኪድን እንዲያዘነብሉ ጥሪ የማደግ ታሪካዊ ሃላፊነት ይኖርባቸዋል። ይሁን እንጂ በአዲሱ ኪዳን ጊዜ እንደ እንቅፋት ሆነው የሚነሱ አንዳንድ የፖለቲካ ኀይላት ይኖራሉ። በተለይም አክራሪ የብሔር እርበኞች አካባቢ ያሉ ኀይላት የኪዳኑ ዋና ተግዳሮት ሆነው የሚታዩ ናቸው በአጠቃላይ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አሰላለፍ ስናይ አጠማመዱ ወጥነት የሌለው የብሔርና ብሔራዊ ፓርቲ አንድ ላይ የሚተራመሱበት እርሻ ነው። በዚህ እርሻ ላይ የፖለቲካውን ሜዳ በበላይነት የተቆጣጠረው ብሔር ተኮሩ ኀይል ነው። በአገሪቱ ውስጥ ካሉት ከመቶ በላይ የሚሆኑ ድርጅቶች መካከል 70% የሚሆኑት በዘውጋቸው የተደራጁ ኀይላት ሲሆኑ 30% የሚሆኑት ደግሞ አገራዊ ፓርቲዎች ናቸው። በርግጥ የዘውጉ ፖለቲካ በኀይል በዚህ ደረጃ የበላይ ቢሆንም በኮንስትቲየንሲ ግን ውጤቱ የተገላቢጦሽ እንደሆነ ይታመናል። የአስራ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባቱ ምርጫ፣ በቅርቡ ኦሮምያና ዓማራ አካባቢ የተነሳው ተቃውሞ ማሳያዎች ናቸው። በቅርቡ በነበረው ተቃውሞ ጊዜ ጎንደር የሚፈሰው የኦሮሞ ደም የእኔም ነው ሲል ናዝሬትና ሌሎች የኦሮምያ አካባቢ ዓጸፋውን ሲመልሱ የሚያሳየው ሃቅ የደም ፖለቲካ (bloodline politics) መሰረት እንደሌለው ነው። የሆነ ሆኖ እነዚህ በዘውግ ላይ የተደራጁ ኀይላት አገሪቱ ወደ አዲስ ኪዳን ስትገባ ከሚኖራቸው ተጽእኖ አንጻር በ 3 ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ።

አንዳንድ የዘውግ ድርጅቶች ብሄራቸው ከኢትዮጵያ ጥላ ስር ሳይጠፋ ነገር ግን ራስን በራስ ማስተዳደር እንዲከበር የሚሹ ናቸው። እነዚህ ኀይላት መስዋእትነትንና መዋጮን ይፈራሉና ለአዲሱ ኪዳን ተግዳሮት ናቸው። ሕዝቡ ወደ ኪዳን እንዳይገባ ለማድረግ ከመጣር አልፈው ራሳቸውም እንደዜጋ ወደዚህ ኪዳን ለመግባት የሚደፍሩ አይደሉም ፣ሁለተኛው ኀይል አክራሪ ሲሆን እስከ መገንጠል የሚንቀሳቀስ ነው። ይህ ኀይል በከፍተኛ ሁኔታ የአዲስ ኪዳን እንቅፋት ነው። አዲስ ኪዳንን እንደ ጦር ይፈራል። መስዋእትነትን አንድነትን ዓይቀበልም። በቁጥር ግን እጅግ አናሳ ነው።

ሶስተኛው የብሔር ተኮር ኀይል ደግሞ ለዘብተኛ ሲሆን ቀን እስኪያልፍ በብሔር ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስና ኢትዮጵያውያን ወደ አዲስ ኪዳን ለመግባት ቢነሱ ስጋት የመሆን ደረጃው ዝቅ ያለ ነው። ይህ ኀይል የሚሻው ነገር ዘውጉ ተለይቶ የሚጠቃበት ሁኔታ እንዳይፈጠር እንጂ መገንጠልን አይደግፍም። አሁን ያለው የዘውግ ፖለቲካ አሳሰቦት ለዘውጉ ከለላና ድምጽ ለመሆን ቢደራጅም ኢትዮጵያውያን የኔ የኔ የሚለውን ትተው አዲስ ኪድን ገብተው ከብሔር ፖለቲካ ወጥተው ወደ እኛ የማኅበረ ፖለቲካ ምህዳር ቢገቡ አይከፋውም።

የአንድነት ኀይል

አንደኛው ኀይል ጽንፈኛ የሆነ በመሆኑ ምንም እንኳን ስለኢትዮጵያ አንድነት የሚያወራ ቢሆንም ነገር ግን በቡድኖች መብት ላይ ያለው ግንዛቤ በጣም ዝቅ ያለ ነው። ሊያያት የሚፈልጋት ኢትዮጵያ በአንድነት ያበደች አገር ሆኖ ነገር ግን የብሔርን ጥያቄ ዝቅ አድርጎ የሚያይ በመሆኑ አዲስ ኪዳን ደግሞ የግልንም የቡድንንም መብት ለማስከበር የተነሳ በመሆኑ በዚህ ጽንሰ ሃሳብ አካባቢ የከረረ ተቃዋሚ ይሆናል ተብሎ ባይታሰብም የተወሰኑ ማንገራገሮችን በማስሳየት ተግዳሮት ሊሆን ይችላል።

ሌላው የአንድነት ኀይል ደግሞ ምክኛታዊ የሆነ ዴሞክራሲን አጥብቆ የሚሻ፣ ብዝሃነትን የሚቀበል የማንነት ጉዳይም የሚያሳስበው ኀይል የዚህ ኪዳን ኸርሊ አዳፐተር ነው። ጎታች አይሆንም።

## የብሔር ኢንተርፐሩነርስ

ባላፉት ሃያ ስድስት ዓመታት አገራችን ያለማቋረጥ የምታመርተው ኀይል ይሄ ነው። የብሔር ኢንተርፐሩነርስ እየበዙ ሲሄዱ ይታያል። እነዚህ ኀይላት እድል ፈላጊዎች ናቸው። የብሔር ፖለቲካን ተገን እያደረጉ በዚያ ዙሪያ እየተደራጁ ተቀርቋሪ ነን እያሉ ለግል ሕይወታቸው ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ይጠቀሙበታል። በአንድነት ጊዜ እንዋጣለን ብለው ያምናሉ። ይህ የብሔር ፖለቲካ እርሻ ግን እነዚህን አረሞች ብዙ አፍርቷልና እነዚህ ኀይላት የኪዳኑ እንቅፋት ናቸው። በቻሉት ሁሉ ሕዝቡ ወደ አዲስ ኪዳን እንዳይገባ የሚቀሰቅሱ ኀይላት ናቸው። መንግሥት ደግሞ ምንም እንኳን ፍላጎታቸውን ቢረዳም የመከፋፈሉን ስራ ስለሚይዙለት ይጠብቃቸዋል። እስካሁንም የሚያድጉት የመንግሥትን ከፋፍለህ ግዛ ሲስተም ስለሚሰሩለት ነው። ኢንተርፐሩነርስ ፍላጎታቸው ይህን የብሔር ፖለቲካ ተጠቅመው ተሰሚነት ማግኘትና የሚፈልጉትን ሀብት ማጋበስ እንጂ ስለብሄራቸውም ሆነ ስለ ብሔራዊ አንድነት የሚገዳቸው አይደሉም።

## የሲቪክ ማኀበራት

ኢትዮጵያ ዓ ም የዓለም ዓቀፍ የሲቪክና የፖለቲካ መብትን ለማክበር ፈርማለች ። ይሁን እንጂ የሲቪክ ማኀበራት በኢትዮጵያ ደስተኞች አይሆኑም። ከዚህ በፊት ወደ አራት ሺህ የሚጠጉ ማኀበራት የነበሩ ሲሆን መንግሥት የተለያየ ጫና እያሳደረባቸው ብዙዎች ተዘግተዋል። ብዙዎች ደግሞ እንዳይንቀሳቀሱ ተደርገዋል ወይም እንቅስቃሴያቸው ተገድቦ የስጋት ኑሮ ይኖራሉ። በዴሞክራሲና በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የሚሰሩት ናቸው ዋና የመንግሥት ዱላ ሰለባዎች። እነዚህ ኀይላት የአዲስ ኪዳን ጥሪ ሲመጣ ያንሰራራሉ። አብዛኞቹ በአንድም በሌላም መንገድ አንድነትንና ዴሞክራሲን የሚሰብኩ የሚደግፉ በመሆናቸው ለአዲስ ኪዳን ኀይል ናቸው። በርግጥ አንዳንድ የብሔር ፖለቲካ ተቀጥላ የሆኑ ኀይላት የመንግሥትን ፖለቲካ አስፈጻሚ ስለሆኑ እነሱ የተወሰነ እክል ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ማጆሪቲ የሆነው የሲቪክ ድርጅት ግን የአዲስ ኪዳን ደጋፊ የሚሆን ኀይል ነው።

## ሃያላን አገራት

በብዙ መልኩ ኢትዮጵያን ሲረዱ የቆዩ የኢትዮጵያ ወዳጅ አገራት እንደ እስራኤል፣ የተባበረችው አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትሬሊያ፣ የአውሮፓ አገራት ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ኪዳን ብትገባ በከፍተኛ ደረጃ ይደግፋሉ። የብሔር ፖለቲካ ጦስ እያሳሰባቸው ስጋት ላይ ስለሆኑ ይህ ኪዳን ለነዚህ አገራት ደስታን ይሰጣል። በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ላላቸው የጸጥታ ጉዳይ የኢትዮጵያ የውስጥ ሰላምና አንድነት ወሳኝ በመሆኑ አዲስ ኪዳን በጣም ቅቡል አሳብ ነው። ሌላው የሚነሳው ጥያቄ የቻይና ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ኪዳን የመግባት ሃሳብ ስታመጣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዓለም አቀፍ ተጽእኖዋ እየጎላ

የመጣውና በተለይ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጅ ናት የምትባል አገር በመሆኗ በአዲስ ኪዳን ንቅናቄ ሰዓት የቻይና ሃሳብ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ጥያቄ መነሳት አለበት። ቻይና የውጭ ፖሊሲየ በሰው አገር ፖለቲካ ጣልቃ መግባትን አይደግፍም ትላለች። በርግጥ ይህ ሃሳብ በመርህ ደረጃ ይደገፋል። ይሁን እንጂ ዓንድ አምባ ገነን መንግሥት ሕዝቡን ሲጨርስ ዝም ብሎ ማየት ከሞራልም፣ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶችም አንጻር ቅቡል አይደለምና ቻይና በዚህ ትተቻለች። የሆነ ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ኪዳን ብትገባ ከሆነላት ቻይና አትቃወምም። ይልቁን ለአዲስ ኪዳን ምስረታ ቀናችን እንኳን ለዚህ አበቃች ሁ ብላ ደብዳቤ የምትጽፍ አገር ነው የምት ሆነው። ሆኖልን ወደ አዲስ ምእራፍ ብንሻገር የውጭ ተግዳሮት አት ሆንም። ቀጣይ ያለውን የንግድና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ስትራተጂዎቿን ነድፋ ወዳጅነቷን የምታጠናክር ነው የምት ሆነው።

ከውጭ ኀይል የአዲስ ኪዳን ተግዳሮት አሸባሪ ቡድን ነው። እንደ አልቃይዳ፣ አልሸባብ፣ አይ ሲ ስ የመሳሰሉ አሸባሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ የዚህ ሃሳብ ተጋፊዎች ናቸው። የጠነከረች፣ አንድነቷ በኪዳን የጸና ኢትዮጵያን ማየት አይፈልጉም። በአሸባሪነት ላይ ኢትዮጵያ የጸና አቋም ስለሚኖራት የውስጥ ሰላሟን አይሹም። በቀይ ባህር አካባቢ የተለየ ዝንባሌ ያላቸው ኀይሎችም እንዲሁ የኢትዮጵያን መጠናከርና ኪዳን አይደግፉምና እንደውጭ ተግዳሮት ይታያሉ።

## የባህልና የሃይማኖት ተቋማት

እነዚህ ኀይሎች የአዲስ ኪዳኑ ደጋፊዎች ተደርገው የሚታሰቡ ናቸው። ኪዳኑ ፖለቲካዊ ባለመሆኑ በሂደቱም አክቲቭ ይሆናሉ። የኪዳናችን ሃሳብ የያዘው እሴት ከነዚህ ተቋማት ጋር የሚዛመድ በመሆኑ ደስታቸው ነው። በተለይ የባህል ተቋማት ከፖለቲካ መጫወቻነት ነጻ ወጥተው የራሳቸውን መንግሥት መስርተው እንዲኖሩ የሚያደርግ ስለሆነ ኪዳኑን በኀይል ይደግፋሉ። በርግጥ በባህል የማስመለስ ሂደት ወቅት የባህልና ታሪክ ንጥቂያና ቅርምት እንዳይኖር ከላይ የምንገባው ኪዳን የሁላችን እንደሆነ ስለሚያሳይ ይሄን ያህል ተግዳሮት አይጠበቅም።

## የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና አለም አቀፍ ተቋማት

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዚህ ኪዳን ዋና ኀይል ደጋፊ ይሆናል። እንዴውም ይህ የኛ ሞዴል ለብዙ አገሮች ትምህርት ሊሰጥ ስለሚችል ድጋፉን ከፍ ያደርጋል። ከዚህ ግዙፍ ተቋም ውስጥ ያሉት እንደ UNHCR, UNDP, OHRC, UNICEF, etc. ያሉት ተቋማት ደግሞ ኢትዮጵያ ኪዳን ስትገባላቸው ሻማ እያበሩ ደስታቸውን ይገልጻሉ። እንደ IOM ያሉ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ችግር በቅርብ ስለሚያውቁ አንድነትን ኪዳንን በሙሉ ሃይላቸው ይደግፋሉ። የአፍሪቃ ህብረትም ቢሆን ይህን ሲስተም መደገፉ አይቀርም። ኢትዮጵያ አሁን የምትከተለውን የብሔር ፖለቲካ የማይደግፉ ብዙ የአፍሪካ አገራት ይኖራሉ። ኔልሰን ማንዴላ ወደ ኢትዮጵያ ተጋብዘው ጉዞ የሰረዙት በዚሁ በዘር ፖለቲካ ባለመደሰታቸው ነበር።

## ሕዝባዊ መሰረት

በአጠቃላይ ወደ ኪዳኑ ስንሄድ ያሉት ተግዳሮቶች እንዳሉ ሆነው ነገር ግን በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ይኖረዋል። በኪዳኑ ንቅናቄ ሰዓት ቀዳሚ ተቀባይ (early adaptors and innovetors) ቀጣይ ተቀባይ (late adaptors) እንዲሁም ጎታች (laggers) ይኖራሉ። አዲስ ራእይ ሲመጣና ያንን ራእይ ለማስረጽ ስንነሳ እነዚ ኀይላት ሁሌም ይኖራሉ። ቀዳሚ ተቀባዮች ፈጣን ሲሆኑ የመጣውን ሃሳብ ወዲያው በፍጥነት ተረድተው ወዲያው ወደ ተግባር ይገባሉ። በኢትዮጵያ ሁኔታ በየብሄሩ ማጀሪቲ የሚሆነው አንድነትን የሚናፍቀው ሕዝብ ይህን ኪዳን ለመቀበል ፈጣን ነው። ሌሎች ቀጣይ ተቀባይ ይኖራሉ። እነዚህ ኀይላት ደግሞ ውጤት ያያሉ ወይም ውጤት ይሻሉ። አይተው ቀምሰው ነው እጅ የሚሰጡት። በመሆኑም የአዲስ ኪዳኑን ውጤት እስኪያዩ ፈጣን ተቀባይ ላይሆኑ ቢችሉም እንቅፋት ግን አይሆኑም። ሌሎች በቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ ግን (laggers) (ጎታች) የምንላቸው እነሱ የኪዳኑ ተግዳሮት ናቸው። አንዳንዶቹ ከፍ ሲል ያነሳናቸው ጽንፈኞች የብሔር ፖለቲከኞች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የተዋለደው ሕዝብ ደግሞ ይህ ያለፈው የብሔር ፖለቲካ ስላስቆጣው አዲስ ኪዳን ሲመጣ ለመቀበል ፈጣን አካል ነው። ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ ከሁሉ በላይ ድህነት ያጠቃቸው ናቸው። እነዚህ ወገኖች በፍጥነት ወደ አዲስ ኪዳን ገብተን ከረሃብ ቢወጡ ይመርጣሉ። ሌሎች የብሔር ፖለቲካ ሄዶ ሄዶ የዘር ፍጅት እንዳያመጣብን ብለው የሚጸልዩ የሚሰጉ ኀይሎች አዲስ ኪዳን ተስፋን ሰጪ ነውና በደስታ ይቀበላሉ። በአጠቃላይ አዲስ ኪዳን ከውስጥና ከውጭ ያሉበት ተግዳሮቶችና ድጋፎች ያሉ ሲሆን ድጋፉ ከፍ ያለ ነው።

## VI. መደምደሚያ

በእስካሁኑ ውይይታችን ውስጥ አስር ጊዜ የብሔር ፖለቲካን እያነሳን ጣልን። ዴሞክራሲን፣ ፕሉራሊዝምን መረቅን። ለዚህ ደግሞ የሚሻለው በስምምነት ላይ የተመሰረተ ባህላዊ አንድነት ውስጥ መግባት ነው ለማለት ሞክረን። የ CCU አጀንዳ ከዚህ በፊት በዘውግ ፖለቲካና በግድ በሆነ ውህደት ፖለቲካ ልንፈጥረው ያልቻልነውን ሲነርጂ ወይም የህብረት ስሜትና ክንድ ለመፍጠር ስለሚረዳን ነው። አገር የሚሻው ዋና ነገር ህብረት ነው። ይህን ህብረት ለመፍጠር ደግሞ የምንገባው ኪዳን የሚፈጥረው የማኅበረሰብ ሲነርጂ ወሳኝ ነውና ይህ የሚፈጠረው ኤነርጂ ለኢትዮጵያ ህልውና እንደ መልህቅ ይሆነናል።

በርግጥ ይህ አማራጭ አሳብም ሆነ ሌላ አማራጭ አሳብ ወደ ተግባር የሚለወጠው ቁርጠኛ የሆነ ትውልድ ሲመጣ ነው። ቁርጠኛ ትውልድ ተነስቶ ለውጥ ሲያመጣ ያን ጊዜ አዲስ የተሻለ ሲስተም ለመዘርጋት ይቻላል። አሁን ያለው ትውልድ አንድ ነገር ማድረግ ያለበት ይመስለኛል። አገሩን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እየመራ ያለውን አምባገነናዊና ዘረኛ ሥርዓት ለመለወጥ ቆርጦ መነሳት አለበት። መንግሥትን መጣል ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት፣ ሲነርጂ ለመፍጠር ጥርመሳ ውስጥ ለመግባት መነሳት አለበት። ይህ ሲሆን ነው የተባበረችውን ኢትዮጵያን የምንገነባው። አሳብ ማምጣታችን የወደፊቷን ኢትዮጵያን እንዴት አድርገን ልናስተዳድር እንደምንችል መወያየታችን ተገቢ ሆኖ ነገር ግን ዴሞክራሲን ከሚያዘገይ ኢዴሞክራሲያዊ ኀይል ጋር መታገል ይኖርብናል። ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተባበረችውን ኢትዮጵያን ለመገንባት መነሳት ያለበት ሲሆን በተለይ የሚከተሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ትልቁን ሃላፊነት የያዙ ይመስለኛል።

ለአንድ አገር ፖለቲካ አለመረጋጋት ትልቁን ሚና የሚጫወተውና የዜጎች መከራ የሚረዝመው ዲክቴተር የሆነ መንግሥት ስለሚገጥማቸው አይደለም። የትኛውም አምባገነን መንግሥት ከሕዝብ ክንድ በላይ አይሆንም። የመከራው ጊዜ የሚረዝመውና ዲክቴተርስ ትንፋሽ የሚያገኙት የሌሂቁ ክፍፍል ሲጨምርላቸው ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም የማንነት ፖለቲካ ከመጣ ወዲህ የማይቀንስ እንደውም እያደገ የሚሄድ የሌሁቁ ልዩነት ይታያል። የጎዳው ልዩነት መኖሩ ሳይሆን ልዩነቱ ጽንፈኛ መሆኑና የሚያገናኝ አንድ የጋራ መድረክ አለመኖሩም ነው።

እነዚህ አካላት በቅንነት ለአገራቸው ዴሞክራቲክ ለውጥ የሚታገሉ ቢሆንም መበታተናቸው ግን በተቃራኒው መንግሥትን እየጠቀመ ትግሉን እያዳከመ በመምጣቱ ችግርቻችን እንዳሉ እንዲቆዩ አድርጓል። በመሆኑም ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ለሂቃኖቻችን አንድ ሚኒመም የመስማሚያ አጀንዳ በማስቀመጥ በዚያ ላይ ለመስራት መቁረጥ ያስፈልጋል። ይህ መሰረት ደግሞ በጣም ግልጽ በሆነና ቀላል በሆነ መንገድ መቀመጥ ያለበት ሲሆን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር የአስቸጋሪ መንግሥት ጉዳይ ሳይሆን በጣም መሰረታዊ የሆነ የዴሞክራሲና የነጻነት ጥያቄን የያዘ በመሆኑ እነዚህ ሌሂቃን በትግል ስልትና በፖለቲካ አስተሳሰብ ከመለያየት ይልቅ ኢትዮጵያ በሽግግር ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲ መግባት አለባት በሚለው ላይ መግባባት ያስፈልግ ይመስለኛል። ይህ የሽግግር ጊዜ እንዲፈጠርና ይህ የሽግግር ጊዜ ከፖለቲካ ኀይላት በተውጣጡ ሰዎች እንዲመሰረትና በዚህ የሽግግር ጊዜ ብሔራዊ እርቅ እንዲመጣና ኢትዮጵያን ለባህላዊ አንድነት የሚያመቻች ቢሆን መልካም ነው።

ሌሎች የአመለካከት ጉዳዩች መሬቱ ከተደለደለ በሁዋላ በሽግግሩ ጊዜ ቢነሱ መልካም ነው። ኢትዮጵያ ካለፈችበት ጎዳና አንጻር በዚህ በብሔራዊ ስምምነት ጎዳና ውስጥ ማለፍ ስላለባት ወደዚህ ጎዳና ለመግባት የሚያስችላት ላይ ብቻ አጥብቦ መግባባት ቢቻል የተሻለ ነው። ይህ የስምምነት ደረጃ በሽግግር መልክ መጀመሩ ዴሞክራቲክ ኀይላትን ሁሉ የሚያሰባስብ ሰፊ ጥላ ይመስላል። ሌሎች የፖለቲካ አስተሳሰቦች ክርክሮችና ልዩነቶች መነሳት ያለባቸው በመጀመሪያ ጥላት ፎርሙ ሲኖር ስለሆነ ኢትዮጵያዊያን ለሂቃንና የፖለቲካ ፓርቲዎች አሸንፎ ሥልጣን ለመያዝ መንግሥት ለመመስረት ከሚያደርጉት ትግል ይልቅ ሁሉን አቀፍ የሆነ የስምምነትና የጽሞና ጊዜ ለአገሪቱ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ለዚህም መታገል አለባቸው። ለጊዜው የፖለቲካ አጀንዳቻውን ያስቀምጡትና ወደዚህ ጥላ ገብተው ኀይላቸውን ያሰባስቡ። ይህን በማድረጋቸው የሕዝብ ልብ የሚያርፍ ከመሆኑም በላይ ለእዝ ይጠቅማል። በአሁኑ ሰዓት የነጻነት ትግሉ የገጠመው ፈተና የእዙ ሁኔታ እዚያም እዚያም መሆኑ ነው። ሰልፎችን የሚጠራው ቡድን በዛ፣ የትግል ስልቱ በዛ፣ ለትግል ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ትእዛዝ የሚሰጥ ጠፋ፣ በዚህ መሰረት ትግሉ አልራመድ አለ። በመሆኑም ሌሂቃኑ ሕዝቡን ለስምምነት ለሽግግር ጊዜ እንዲታገል መጥራት ይቻላል። ይህ ህብርት ሲፈጠር የሚመጣው ጥያቄ የትግል ስልት ጉዳይ ነው። አንዱ የሚያለያይ ጉዳይ ሆኖ የሚታየው ይሄ ጉዳይ ነው። በእኔ እምነት የትግል ስልቱ ምርጫ የሚያለያይ አይመስለኝም። እነዚህ ነፍጥ አንስተው የሚታገሉ ኀይሎች ይህን ምርጫ ስለወደዱት አይደለም። ሁኔታዎች ስለተዘጉ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የለውጡን የመጀመሪያ ምእራፍ ለመክፈት ሁሉም የትግል ስልቶች ውጤታማ ናቸው። ብሔራዊ እርቅ፣ ሰላማዊ ትግል፣ የትጥቅ ትግል፣ የዲፐሎማሲ ትግል እነዚህ ሁሉ በተናጠልም በጋራም መንግሥትን የመቀየር ኀይል አላቸው። ችግሩ ያለው እነዚህን የትግል ስልቶች በተናጠል ወይም በጋራ ያላቸውን ኀይል አሟጦ አለመጠቀም ነው። የኀይል መበታተን እነዚህ ትግሎች ውስጥ ያለውን እምቅ ኀይል ተጠቅመን ሕዝባዊ ትግሉን ወደፊት እንዳናራምድ አድርጎናል። ለዚህ ነው ወደ አንድ አቅጣጫ ሰብሰብ ማለቱና በአንዱ የትግል ስልት ዙሪያ ጠንከር ያለ ትግል ማካሄድ የሚያሻው። የትግል ስልት መምረጡን እንደ ትልቅ ልዩነት አንየው የምንለውም ለዚህ ነው። ሁሉም የትግል ስልቶች ለውጥ እስከሚያመጡ ድረስ መሰባሰብ ከቻልን በቀላል መስዋእትነት ለውጥ የሚያመጣውን የትግል ስልት መምረጥ እንችላለን።

ወደ ወጣቱ ልመለስና ይህ ትውልድ በተለይ አገሩን ወደ ተሻለ ማኅበራዊ ፖለቲካ ለማሻገር ግዙፍ ታሪካዊ ሃላፊነት ትከሻው ላይ ወድቋል። ይህን ሃላፊነት ለመወጣት የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት፣ ወደ አዲስ ኪዳን መሻገር ያስፈልጋል።

ጎልማሶችና አባቶች የካበተ እውቀት ስለሚኖራቸው አቅጣጫ በማሳየት በምክር ይረዳሉ። ነገር ግን ሁል ጊዜም ቢሆን የለውጥ ኀይል በእጁ ያለው ወጣቱ ጋር ነው።  ወጣቱ ነው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ አክቲቭ የሚሆነው፣ ወጣቱ ነው አምጾ ለውጥ የሚያመጣው፣ ወጣቱ ነው የማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀምና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም አምባገነኖችን ወጥሮ የሚይዘው። በማንኛውም የትግል ስልት ውስጥ ኀይል ያለው ከወጣቱ ጋር ነው። ስለዚህ ወጣቱ በተለይም በከፍተኛ ትምህርት አካባቢ ያለው በአገራችን ውስጥ ተፈላጊ ለውጥ ይመጣ ዘንድ በግንባር ቀደምነት ሊመራ ይገባል። ከሁሉ በላይ ከዘር ፖለቲካ ራሱን አጽድቶ ሊቆም ይገባዋል። በሌሎች መስዋእትነት ውጤት ጠባቂ ከሆንን ለውጥ አናመጣም። የተባበረችውን ኢትዮጵያን ለመገንባት መነሳት አለብን። ሌላው ወታደሩ፣ ፖሊሱና የፍትህ አካሉ በቃ ሊል ይገባል። ሳይማር ያስተማረውን ሕዝብ እያሰበ ለለውጥ መነሳት አለበት። አስተማሪዎች ሰፊ ሃላፊነት አለባቸው። ያልገቡበት የአገሪቱ ክፍል የለምና ባሉበት አካባቢ ሕዝቡን ማንቃት አገሪቱን ወደ ተሻለ ሥርዓት ለማሻገር ማስተማር ያስፈልጋል።  ገበሬው፣ ሴቶች ወንዶች ሁሉ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ግንባታ መነሳት አለብን።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምንም በላይ የፖለቲካ ጨዋታ መጀመሪያ ሜዳውን ለመደልደል መነሳት አለባቸው። ኢትዮጵያውያን ሁሉ ወደ አዲስ ኪዳን ይገቡ ዘንድ የሁሉ ፓርቲዎች ፍላጎት ሊሆን ያስፈልጋል። ይህ የኪዳኑ ሃሳብም የጋራ መሰባሰቢያ ጥላን ይፈጥራልና በዚህ ጥሪ ስር ተሰባስበው ለአዲስ ኪዳን መዘጋጀት ያሰፈልጋል። ከኪዳኑ ማግስት ጀምሮ የፖለቲካ ራእይ ያላቸው ሁሉ ሜዳውም ያው ፈረሱም ያው እንደሚባለው በዚያን ጊዜ ለፍክክሩ ይደርሳሉ። አሁን ለኪዳኑ አሳላፊዎች

አስተባባሪዎች ቀስቃሾች ሊሆኑ ይገባል።

ውድ ወገኖቼ ቅን የሆናችሁ የገዢው መንግሥት ባለሥልጣናትና ተራ የፖለቲካ ሰዎች፣ ውድ ወገኖቼ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና አባላት። መቼስ የፖለቲካ ፓርቲ የምንመሰርተው የወገን ቅንዓት ስለሚይዘን ነው። ወገንን ከችግር ለማውጣት። የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ነው። ነገር ግን አሁን እኛ እርስ በርስ በዘውግና በብሔራዊ ማንነት ስንነታረክ ብዙዎች ረሃብ ላይ ወድቀውብናል። ዛሬ ሚሊዩን የሚጠጉ ለጋ ህጻናት ጎዳና ወጥተውብናል። በምግብ እጥረት የሚሰቃዩትን ህጻናት ቤታቸው ይቁጠራቸው። ብታገኝ በልታ ብታጣ ተደፍታ የምታድር እህት እንባ ዝም ብሎ በኢትዮጵያ ምድር ይፈሳል። በእርሻ ስራ ከአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነችው ኢትዮጵያ በ21ኛው ክፍለዘመን የእርሻ ቴክኖሎጂ በመጠቀበት ዘመን አፈርና ውሃ ለውሰን በምግብ ራሳችንን መቻል አቅቶናል። በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ 76 በመቶ የሚሆነው አምራቹ ክፍል ወጣቱ ድንገት ከአገር ብን ብሎ መጥፋትን ይመኛል። ዛሬ በአገር ቤት አትሰደድ የሚል የለም። እንዴውም የመሰደድ እድል ያገጠመው ሰው ሲገኝ ድግስ ይደገስለታል። እንኳን ደስ አለህ ተብሎ ስደት የሚመረቅበት ዘመን ላይ ነን። የአቶ እከሌ ልጅ ወደ ውጭ

ሄደ መባል ክብር ሆነ። ወጣት ኢትዮጵያውያን በየቀኑ በአራቱም አቅጣጭ ተዘልሎ ለመኖር ይፈልሳሉ። የአገራችንን የስደት አስከፊ ደረጃ ለማወቅ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጥገኞች ድርጅትን(UNHCR) እንደ IOM የመሳሰሉትን ድርጅቶች መጠየቅ ይቻላል። እነሱ የስደት ሕይወታችንን ተረድተዋልና የኢትዮጵያን ሁኔታ ይገልጻሉ። ዛሬ ወጣት አምራች ወገኖቻችን በአንዳንድ አፍሪካ አገራት በሕገ ወጥ ተጓዥነት እየታሰሩ መከራ ያያሉ። እስራታቸውን ጨርሰው ወደ አገር ቤት እንዲመለሱ ፍርድ ቤት ሲወስንባቸው ፈላጊ ተቀባይ እያጡ ሲንከራተቱ እንደማየት ምን የሚያሳዝን ነገር አለ? አንዳንዶቹን የሰሃራ ምድረበዳ በላቸው። አንዳንዶቹ በባህር ሰጠሙብን። የሰሃራን በረሃ አቋርጠው እንጀራ ፍለጋ የሚንከራተቱ ወንድሞቻችንን አሸባሪው አይሲስ አረዳቸው። ወላድ አነባች። ያልገባንበት ምድር፣ ያልተበተንበት ያልተዘለልንበት የዓለም ክፍል ጠፋ። ሴት እህቶቻችን በታሪክ እንዲህ የተሰደዱበት የተዋረዱበት ዘመን የለም። ቢያንስ 15 ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን የለጋሾችን የምግብ ርዳታ ተስፋ አድርገው ዛሬም ይኖራሉ። መንግሥት ራሱ ከአመታዊ ባጀቱ ውስጥ ከሃምሳ እስከ ስልሳ በመቶ የሚሆነውን ባጀት የሚሸፍነው በእርዳታ ነው። በራሱ የሚቆም መንግሥት እንኳን የለንም። ዛሬም የእናቶች የአባቶች እምባ እንደወንዝ ይፈሳል። በውነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ አይበቃውምን? በአንድ ወቅት ታላቅ ታሪክ ያለን ሰዎች ለአፍሪካውያን ሁሉ ኩራት የሆንን ሰዎች እነሆ ዛሬ በምግብ እርዳታ ልመና ስማችን ጠፍቷል። ከቶ ይህ ያልቆጨን ምን ሊቆጨን ይችላል? ስናሰለጥናቸው የነበሩ የአፍሪካ አገራት ዛሬ በዚህ ስማቸው ፈጽሞ አይነሳም። ዓለም ሁሉ አላምጦ የጣለውን የዘውግ ፌደራሊዝም መስርተን ታይቶ በማይታወቅ የብሔር ግጭት ውስጥ ተዘፍቀናል። ዛሬ ኢትዮጵያውያን በአገር በምድራቸው በማንነታቸው የሚፈናቀሉባት አገር ናት። በአንድ የአገር ጥላ ስር የሆነ ሕዝብ በብሄሩ ማንነት ምክን ያት ሲፈናቀል እንደማየት ምን የሚያሳዝን ምን የሚያሳፍር ነገር አለ? ከሁሉ በላይ ደግሞ ይህ የብሔር ፖለቲካ እርስ በርስ ያለንን መተማመን እንደ ምስጥ በላብን። ከዚህ ስስታም የኔ የኔ ... ከሚል የፌደራል ሥርዓት ወጥተን ወደ እኛ ካላደግን ያቺን ታላቅ አገራችንን ያለማቋረጥ ወደ ኋላ እየነዳት ነው። ከቶ ይህ ያልቆጨን ምን ሊቆጨን ይችላል?። ይበቃል!። ስለዚህ ፓርቲዎች ሁሉ ተቆጭተው በፍጥነት ወደ አዲስ ኪዳን መግባት አለባቸው። በግድ መግባት አለባቸው። ስለ ሕዝቡ ብሶት ሲሉ ብዙ ዋጋ መክፈል አለባቸው። ለዘውግ ፖለቲከኛ ወገኖቼ አንድ መልእክት አለኝ። በቅርቡ ኦሮምያ ውስጥ በተነሳው ዓመጽ ሳቢያ ብዙ ኦሮሞ ወገኖቻችን ሲያልቁ የጎንደሩ አማራ ተነስቶ በየጎዳናው የሚፈሰው የኦሮሞው ወገኔ ደም የእኔም ደም ነው ሲል፣ ናዝሬት፣ ጊንጪ ያለው ኦሮሞ ጎንደር ላይ የሚፈሰው የአማራው ደም የእኔም ነው ብሎ ተነሳ። አዋሳ ላይ ያሉ የደቡብ ወገኖች ጎንደር ላይ የሚፈሰው የአማራው ደም፣ አምቦ ላይ የሚፈሰው የኦሮሞው ደም የእኔም ደም ነው ሲሉ ተነሱ። ይህ ምን ማለት ነው? It shows that bloodline politics in Ethiopia has been rejected by the Ethiopian people. Ethiopians are saying No bloodline politics! No bloodline federalism! Period. (የደም ሐረግ የዘውግ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ውስጥ ቦታ የለህም ማለት ነው።) በቅርብ ቀን በቅማንትና በዓማራ ሕዝብ ሪፈረንደም ላይ የታየው አንለያይም አንድ ነን መልእክት በኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር የደም ፌደራሊዝም እንዳከተመለት ነው። አማራም ሆነ ቅማንት ባህሎቻቸው ተጠብቆ ቢኖሩ ደስታውን

አይችሉትም። ይሁን እንጂ ይህ ልዩነታቸው ግን የተከፋፈለ የፖለቲካ የመሬት የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ እንዲያደርጋቸው አይፈቅዱም። ሕዝቡ በልቡ የያዘው ቃል ኪዳን ይህ ነው። በኢትዮጵያውያን ኪዳን ላይ ተመስርቶ የሚራመድ ፓርቲ ነው ፓርቲ ማለት። ስለዚህ ሕዝቡን እንዲህ በልቡ ጠብቆ ወደያዘው ኪዳን መሃላ እንውሰደውና መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ኪዳን ከገባ በኋላ በዚያ የማእዘን ራስ ላይ የፖለቲካ ቤታችንን እየሰራን ፍክክር እናደርጋለን። በመሆኑም ፓርቲዎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይህን ኪዳን ያደርጉ ዘንድ ታጠቀው የሚቆሙ የለውጥ ሃዋርያት መሆን አለባቸው። ይህን በማድረግ የኢትዮጵያውያንን የእምባ ዘመን እንዲያበቃ ሊያደርጉ ይችላሉ። አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች፣ የመንግሥት ሰራተኞች፣ የጥበብ ሰዎች፣ ነጋዴዎች፣ ገበሬው ሴቶችና ወንዶች ሁሉ ኪዳን አድሰው ተማምለው አገሪቱን ከገባችበት ሁለንተናዊ ቀውስ የማውጣት ታሪካዊ ሃላፊነት ትከሻቸው ላይ ወድቋል። ያለፈው አልፎ **አሁን ወደ አዲስ ኪዳን የምንሻገርበት ዘመን ይሁንልን።** ዘ ጸዓት ለኢትዮጵያ እመኛለሁ። **የተባበረችውን ኢትዮጵያን በጋራ** እንገንባ!

ያለፈው አልፎ አሁን ወደ አዲስ ኪዳን የምንሻገርበት ዘመን ይሁንልን። የተባበረችውን ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ።

**እግዚአብሔር ይርዳን!!!**